# የቤተክርስቲያን
# ቅድሜ መከራ መነጠቅና ትርክቱ

እድሉ ዮሐንስ ጋምሳ

# የቤተክርስቲያን ቅድሜ መከራ መነጠቅና ትርክቱ

ማውጫ

መግቢያ

1. የራዕይ መጽሐፍ ይዘት

2. ለንጥቀት አስተምህሮ ስባል የተጨነገፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

3.የክርስቶስ ስውር ዳግም መምጣትና ስውር ንጥቀት

4.ከመከራው በስውር የተነጠቁ ቅዱሳን ሰርግ

ማጠቃለያ

መግቢያ

የትኛውም ዶክተር ክርስቲያን ከኾነ የጌታ ተማሪ ነው፤ ፍደል ያልቆጠረውም የጌታ ውዱና ምርጥ ተማሪው ነው። ጌታን የእኛ የትምህርት ወረቀት ልህቀት አይረዳውም ፤ አለመማርም አያግደውም ። እርሱ የእውቀት ሙላት ነው። ስሰጥ የማያልቅበት ነው ፤ ባዶውን ብቻውን የሚሞላ ነው ። በባዶ ሸለቆ ምንም በሌለበት ውኂ የሚያሞላ፤ ባዶ ጋኖችን ንፁህ ውኂ[ቃል] ብቻ ሳይኾን ጣፋጭና ማራኪ የሚጥም የሚያደርግ ድንቅ አምላክ ነው። ያለ መሄንዲስና እውቀት ትልቁና ብርቱውን መርከብ ለዚያውም ከአንድ በረዶ ግግር ጋ ተጋጭቶ የሚገለባብጥ ሳይኾን፣ ከሰማይም በሚወርድ አስድ ዝናብና ምድርን በሞላው ውኃ የሚሳፈፍ መርከብ የሚሠራ ጌታ ነው፤ ያውም በጥቂቶቹ የሚሠራ ። ታዲያ ይኽ ጌታ "ሹሞን" በእኛ ላይ ባለው እውቀት እየተደገፈ "ይሠራል" ከሚል ቅዠት መውጣት የለብንም? በፊደል ከመራቀቅ ብቻውን ወደሚሠራ አምላክ ፊታችን ማዞር የለብንም ?ከተናገርኩት ዋናው ነገር; እንዲህ የሚል ነው፦ እንደ ሳውል በታዋቂ አስተማሪ ፣አንቱ በተባለ ሰው ተምሬ ልኾን ይችላል ፤ዕድሜ ልክህን ስታጠናና ስትማር አድጌ ልኾን ይችላል ። ይኽ ግን ለጌታ ሥራ አስተማማኝነት አስረጂ አይኾንም። ሳውል እንዲህ ያለ ብኾንም ፣ እዝግባ በማይባል አስተዳደግ ወዳደገው ወደ ሐናንያ ተልኳል ። ሳውልም አልናቀውም። አንተም አንባቢ ኾይ ሳታውቅ የክብርን ጌታ እያሳደድክ እንዳይሆን ከገባህበት አዘቅት፣ ከያዘህ ጭፍን ፈረሳውነት ተላቀቅ ወደ ጳውሎስነት በእግዚአብሔር እውቀት እንዲትሻገር እመክራለሁ ።

የራዕይ መጽሐፍ ደብቀን ሸሽገን እንዲንጠብቀው ሳይኾን፣ ጌታ ለትውልዱ ያስተላለፈውን መልእክት እንድናነበው የተሰጠ ነው። ይኽንን መጽሐፍ እንደ ሌሎቹ የእግዚአብሔር መልእክታት በማንበብ በማጥናት በምሪቱ የመልእክቱ ተጠቃሚ ልንኾን ስገባን ከመግለጥ ይልቅ መደበቅ አማራጭ መደረጉ ከፍርድ የማያስመልጥ ተግባር ነው። ጌታ የሾመህ እረኛ ከኾንክ ትውልዱን ለመመገብ ተዘጋጅ ።እስካሁን በማህተም ያልተዘጋውን መጽሐፍ በመዝጋትህም ንስሓ ግባ ።

ደግሞም በእውቀታቸው አንቱታን ያተረፉ አስተማሪዎች ፣አንዷንና ወጧን መልእክት ፤ እንዲህም እንዲያም ልኾን ይችላል በማለት ፣ ትክክለኛውን የእግዚአብሔርን መልእክት ባለመናገር መንጋውን ከመጥቀም ይልቅ፤ እንዲያነቡ ከመቀስቀስ ይልቅ እንዲፈሩና እንዳይጠጉ በማድረግ ግራ አጋብተዋል።ነገርግን የእግዚአብሔር መልእክት አንድና አንድና ነው። አልገባኝም ማለት እየተቻለ እንዴት "በ ልኾን ይችላል" በግምት እንዘብታለን?እንተረጉመዋለን?

አስተማሪዎች ለአንዲት መልእክት ሁለትና ከዚያ በላይ የኾነ የአማራጭ ትርጓሜ በመስጠት፤ ማፈርና መሸማቀቅ ስጋባቸው እንዴ ባለአዕምሮ እንደ ልቤ ሰፊነት መቆጠሩ ይደንቃል ። እንዴት ሁሉም ሃሳብና የተለያየ መልእክቶች ትክክል ልኾኑና እውነት ልኾኑ ይችላሉ? አይችልም ።ይኽ የሚያሳየው ለአስተማሪዎችም መለኮታዊ ግልጥት አለመኖሩን ነው፤ በጉድለታቸው ሳያፍሩ እንዴ አዋቂ እንደ እግዚአብሔር ቃል መጋቢ መናገራቸው ይደንቃል ። ትውልዱ ስወዛገቡ ከፍደል ብቻ ያልኾነ በቃልም በመንፈስ በሥልጣን የሚናገሩና የሚያስተምሩ የሚዘልፉ ብኾን መልካም ነበር።ግን ምን ያደርጋል አያደርጉትም በአብዘኛው፤ እነዚህ ዝናብ አልባ ደመናዎች ናቸው ። ትርፉ መንታ ልብ መስጠት ብቻ ነው። ደግሞም እንዚህን አስተማሪዎችን የሚያወዛግቡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከፍ ያለውን የራሳቸውን ሃሳብ የሚናገሩ ዕውራን ሃሰተኞች አስተማሪዎች አሉ።

የራዕይ መጽሐፍ ምዕራፍ አራትን ስመለከቱ "እኛን አይወክልም" ለእስራኤል ዘሥጋ ነው፥ "እኛ ቀድመን በስውር ከመከራው እንነጠቃለን" በሚል የእግዚአብሔርን ቃል የሸቀጡና የመረዙ አስተማሪዎችም አሉ። ራዕይ መጽሐፍ ለአማኞች ኹሉ ዘወትር እያስተዋሉ እንድኖሩ የተሰጠ ትንቢታዊ መጽሐፍ መልእክት እንጂ በሥጋ እስራኤላውያን ለኾኑ የተነገረ አይደለም ። እነዚህ የጌታን መምጣትን ቤተክርስቲያን አስተውላ ተገቢውን ዝግጅትና ምላሽ እንዳትሰጥ ለማድረግ ጭፍን ፈረሳውያን [ለራሳቸው ወግና ዕሳቤ የሚቀኑ] የፈጠሩት ስብከት ነው፤የሥጋ አይሁዳዊነትን የሚሰብኩ; ትውልዱ ዘመኑን አውቀው፣ የትንቢቱን ቃል ጠብቀው፣ ድል እንዳይነሱ ድንዛዜ በመርጨት እንዲህ እንዲያንቀላፉ የሚያደርጉ ዕውራን መምህራን ናቸው ።እነዚህ ያልተጻፈውን የሚያነቡና የሚያስተምሩ የእግዚአብሔርን ቃል ለግል ጥቅማቸው እንዳዋሉት በግልጽ በጽሑፍ አሳያለሁ ። የራዕይ መጽሐፍ አጠቃላይ መልእክቱ ፦ ..አሁንም_ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን..።" [ራእይ 1፥19] ፣ በሚመለከት የተጻፈ ነው።

ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው; ለዓለም አቢያተ ክርስቲያናት የተጻፈ ነው፤ ወደፊት ልኾን ያለውን የሚገልጽ ትንቢታዊ መልእክት ነው። ዮሐንስ ለተመለከተው ራዕይ እኛ ፍጻሜው ላይ ነን ። ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለውን"ከቤተክርስቲያን መነጠቅ በኋላ ያለና ለአይሁዳዊያን የተነገረ ነው " በማለት በጭፍን ፈረሳውያን ተሸቅጧል፤እንዲያ እንደሚያስተምሩት ግን የሚተረጎም አይደለም። በራሳቸው ዕሳቤ ውስጥ ተወጥረው አዝም

## የቤተክርስቲያን  ቅድሜ መከራ መነጠቅና ትርክቱ

በመርጨት ፣ለእግዚአብሔር ድምጽ ትውልዱ በቂ ምላሽ እንዳይሰጥና  እንዳይዘጋጅ አድርገዋል ። ቃሉ በግልጽ "ከዚያ በኋላም አየሁ፥ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ፦ ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ።"[ራእይ 4፥1]፣ ይለናል ።

ዮሐንስ ራዕዩን ከምመለከትበት ስፍራ ወደ ከፍታ ቦታ ወጥቶ [ኾኖ] ራዕዩን የወደፊቱን እንዲመለከት " "ወደዚህ ውጣና " ተባለ እንጂ፣ "መነጠቅ" አይደለም ።ለመነጠቅ ብያንስ አካላዊ ለውጥ ያስፈልጋልና ። ዮሐንስ ከፍ ወዳለበት ቦታ ኾኖ ኹሉንም " ከዚህ በኋላ ሊሆን ያለውን" ተመለከተ እንጂ ቤተክርስቲያን አልተነጠቀችም። ክፍሉ ከተነጠቀችም በኋላ ያለውን የሚገልጽም አይደለም ። "መነጠቅ" ነው ብንል እንኳን ለዮሐንስ እንጂ ለቤተክርስቲያን  አይኾንም ፤አይደለምም ።ምክንያቱም ዮሐንስ ብቻው ነው የወጣው ፤ ብቻውን ነበር የወጣሁ ። ደግሞም የሚኾነውን "ተመልከት" ተባለ እንጂ የትንቢቱ ፈጻሚም የመጨረሻው [ትውልድ] አይደለም። ስለዚህም በብልሃት በተፈጠረ ትምህርት "እኛን መከራ አይደርስም" ብላችሁ በሰይጣን ማደንዘዣ ያንቀላፋችኹ ተነሱ፣ ኃይልን ታጠቁ፤ ቃሉን በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ብቻ አንብቡ። አኹን በመጨረሻው በትንቢቱ ፍጻሜ ሰዓት ላይ ነንና ድል ለመንሳት ተዘጋጁ፤ ኃይልን ታጠቁ ። በመከራው እናልፋለንና። አንቦዝን፤ እንነሳ።

ስለዚህም ወዳጆች ደግሞም ላሳስብላችኹ እፈልጋለሁ፥ በረከት፣ሰላም፣ብልጽግና፣ ..ወ.ዘ.ተ. ይኾናል እያሉ፥ ኃይልን እንዳንታጠቅ በምድራዊ ሃብት ምኞት ልባችን እያከበዱ እለት ተእለት እየገደሉ ካሉት ሃሰተኞች እረኞች ተለዩ፣ "ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም ።" 1ኛ ተሰ 5፥3፣ እንደሚል እንዳይሆን!። ስለዚህም በዚህ በመጨረሻው ዘመን"ቃል አውጣብኝ" እያልክ ከመኾነለል ሳይኾን፣የወጣውን ቃሉን ለመጠበቅ ተዘጋጅ፤ አልያ ሃይል አታገኝም፤ ድል ነሺም አትኾንም፤ ወስን፤ እግዚአብሔር ልያሳድግህ አዕምሮን ልከፍትል ይፈልጋልና ወደጓዳ እንድትገባ አበረታታለሁ!

በመጨረሻም ትውልዱ እንዳይነቃ ለዘመናት የበጉን ታላቁን  መልእክቱን የገድል መጽሐፍ አድርገው ፤እውነተኛ ገድል ብኾን ምን ጎድቶን!፤ ቅጥል በጥብጠው "እንዲያ  በይኾናል ትርጓሜ" አንዷን ጫፍ ይዘው ያለ ልክ እየተቀደዱ ያመጡት ቅዥት መኾኑ ያስከፋል ። አውሬው ትኩረት ያደረጋት የሴቷን ማንነት በተጠንቀቅ ማወቅ ዋነኛው ነገር ኾኖ ሳለ ያለፈውን ታርክ ትረካ አድርገው በማስተማር ስንቱን መረዙ ። ከዚህ በፊት የሰማነውን ኹሉንም ትተን "ሴትቱ ማን ናት?" የሚለውን ለማወቅና የመልእክቱን ጭብጥ ለመያዝ እንዘጋጅ ። ታዲያ በራዕይ መጽሐፍ ምዕራፍ 12 ስደርስ መልእክቱን የታርክ የተረትና የገድል መጽሐፍ ያለፈውን የሚዘክር አድርጎ ሰይጣን ለምን ልጆቹን አዳከመ? ሴቷ ማናት ምንድናት? በውኑ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ብፅዕት ማርያም ነች? አይደለችም ።በዚህ መልእክት ዮሐንስ "ማርያምና ኢየሱስ ዮሴፍ" ኾነው ወደ ግብጽ የተሰደዱትን ታርክ ይዘግባል ብለው ይላሉ። ይመስላል እንጂ አይደለም ። መጽሐፉ ከመሠረቱ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ **ወደፊታዊ ትንቢት** ስኾን፣ አጠቃላይ የመጽሐፉም መልእክት ከታርክ ዘገባ ጋር የሚገናኝ አይደለም ።በፍጹም ።እንደዚህ ነው እንጂ ከዚህ በፊት የኾነውን ታርክን የሚተርክ መልእክት አይደለም ።የሰውን ታርክ የሚዘክር ብኾን የትንቢት መጽሐፍ ባልኾነ ነበር። ሙሴ ወደኋላ በመንፈስ ሄዶ ተመልክቶ እንደጻፈ [ዘፍጥረትን] ፤ ዮሐንስም ወደፊት ገና የሚኾነውን [ልኾን ያለውን] በመንፈስ ተመልክቶ [ሄዶ] ጽፏል። ጭፍን ፈረሳዊ አትኹኑ ። የትኛውም የእምነት ድርጅት ኾነ [ዕሳቤ] አባል ስለኾንክ አታመልጥም። ታርክን ይዘክራል ለማለት የሚጠቀሰው በራሱ በውሸት ተረት የታጨቀና የማይኾን ነው።ለምሳሌ ፦

ማርያምና ኢየሱስ ደግሞም ዮሴፍ ወደ ግብፅ ተሰድደው እስከ አኹኗ ኢትዮጵያ [አቐሹም]ድረስ እንደመጡ ልክ አፍቃሬ አይሁዳውያን እንደሚስቡት አፍቃሬ ምድራዊ  ሥጋዊያን ኢትዮጵያውያን ይተርታሉ ።ብዙዎችንም በተረታቸው አስረዋል ። ትውልዱ ሴቷን አውቀው እንዳይነቃ ሰይጣን አዝም ረጭቷል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅሱት ታርክም ለተረታቸው አይኾንም ።በፍጹም ወደ ኢትዮጵያ ስለመምጣታቸው ፍንጭ አይሰጥም፤ ይልቁንም የመጽሐፉ እውነት ያሳፍራቸዋል። "እነርሱም ከሄዱ በኋላ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ፦ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ፥ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው።"ማቴ 2፥13። **ትዕዛዝ አንድ**; ወደ ግብፅ ሽሽ ፣ **ትዕዛዝ ሁለት**; በዚያ[በግብፅ] ተቀመጥ የሚል ነው ።መልአኩ ለነገረው የዮሴፍ ምላሽ፣ "እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢይ፦ ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈጸም ወደ ግብፅ ሄደ፥ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ።" ማቴ 2፥14-15። **የዮሴፍ ተገቢ ምላሽ  አንድ; ወደ ግብፅ ሄደ፣ተገቢ ምላሽ ኹለት; በዚያ ኖረ እንደሚል በሄደበት በግብፅ ኖረ።** ከግብፅ የምልስ ትዕዛዝ በመላአኩ፥ " ሄሮድስም ከሞተ በኋላ፥ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ፦ የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለ።" ማቴ 2፥20]። የመልአኩ ትዕዛዝ ዮሴፍ ባለቤት ሄዶ; ተነሣ ከገብፅ ተመለስ፣ ወደ እስራኤል ሃገር ሂድ የሚል ስኾን ፥ የዮሴፍ ተግባራዊ ምላሽ ደግሞ ፦ ""እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን ያዘና ወደ እስራኤል አገር ገባ።" ማቴዎስ 2፥21። ጭፍን ፈረሳዊያን መጽሐፍ ቅዱሳችን በግልጽ ወደ ግብፅ እንዲሰደዱና በግብፅ እንዲቆዩ የነገረውን፣ ዮሴፍም ተግባራዊ ያደረገውን ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ሄዷል በማለት በእውነት ላይ ያለ ሃፍረት ጭምረው ትውልዱን ያውም ብዙ ሚሊዮኖቹን፣ የተማረውንም ያልተማረውንም

አደንዝዘዋል ። ታዲያ በድፍረት በእግዚአብሔር ቃል ግና የሚፈጸመውን ትንቢታው መልእክትን የተረተ መጽሐፍ አድርገው ማስተማራቸው ምን ይደንቅ? በኢየሱስ ደም ላይ ዘለው ለመርገጥ ያለፈሩ አይደሉምን ? እውነታውን ግን ወዲህ ነው። ይቺ ሴትቱ የተባለችው የኢየሱስን እናት ብፅት ማርያም አለመኾኗ ነው። ዮሐንስ ራዕይ ያለፈውን ታርክ በሚተርክ መልኩ መቅረቡ መጽሐፉን ትረካ አያስብለውም።ከላይ ያለውን በልባችን ይዘን እንደሚከተለው እናጠን ለምሳሌ ራእይ [ም.12 ፥1-6]፣ ያለውን እንመልከት ፦

“ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች።”– ራእይ 12፥1

* ገና ስጀምር ዮሐንስ የተመለከተው "ታላቅ ምልክት ነው" ማለትም **ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ነው**።

* ስለ ሴትቱ ስገልጽ ፀሃይ የለበሰች እና ጨረቃ ከእግሯ በታች ያላት በማለት ነው።ዮሴፍ ያየው ራዕይ ይመስላል ዘፍ 37፥9። እነዚህ ግን በክርስቶስ ደም የዳኑቱ ፣ የበሩቱ ምዕመናንን ናቸው ።

“እርስዋም ፀንሳ ነበር፥ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች።” - ራእይ 12፥2

* ካጋጠማት ብርቱ መከራ የተነሳ መጨነቋን ይገልጻል ። ይህች ብዙ ያሉ አማኞችና የአማኞች ታዳጊ አዳኝ እንዲመጣ ፣እንድደርስላት ከመከራው ናዳ የተነሳ ተጨንቃ ትጮኻለች ።

* አንዳንድ ሰዎች "የማርያም ታርክ ይተርካል" ብሉም ግን ውዳሴ ማርያም ከሚባለው መጽሐፋቸው "..ከድንግል ያለ ሕማም ተወለደ" ከሚለው ትምህርት ጋር ማርያም ያለ ጭንቅ ወለደች ስለሚል ይቃረናል።

“ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥”ራእይ 12፥3

* "ሴትቱ ማርያም ናት" የሚሉ ዘንዶው ፦ " ሄርድስ ነው" ይላሉ። ግን መጽሐፉ በ12፥1 ስጀምር "ምልክት" ብሎ ነው፤አሁንም በቁ.3 ላይ አድስ "ምልክት ታየ"ነው የሚለው ፤ ከዚህ በፊት ያልታየውን ማየቱን ይገልጻል ።ከዚህ በፊት የተከሰተ ክስተት ምልክት አይባልምና ።

* ዘንደው ግን ቀንድ ያለው ፤"ጠብብ መሆኑ" እና ራስ ያለው "ሃይል ያለው መሆኑን" ዲያብሎስ በግልጥ መገለጡን ይገልጻል ።

“ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው። ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ።” – ራእይ 12፥4

* ዘንደው ሄሮድስ ሳይሆን ጭራ ያለው ነው።በጭራው እየተወራጭ የሚያሳድድም ነው ፤ምዕመናትን ።

“አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።”– ራእይ 12፥5

*በብረት ብትር የሚገዛቸው ኢየሱስ ብሆንም ግን ያለፈ የተፈፀመ ታርክ አይደለም፤ገና የሚፈፀም ነው።አዎ አሕዛብ አሁን ለኢየሱስ እየሰገዱ አይደሉምና፤ገና የሚፈፀም ትንቢት ነው ። ከመከራው ጭንቀት የተነሳ በመጣራቷ የራሷን አካል የኾኑ ብርቶች ታዲጊ እንዲገኙ ታደርጋለች።

“ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።”– ራእይ 12፥6

* ሴትቱ መከራ የተቀበለችው ለ3 ዓመት ከ 6 ወር ነው።የሸሸችው ብቻዋን ነው ።ማለትም ከላይ "የማርያም፣ የኢየሱስና ዮሴፍ ጭምር የተሰደደው ስደት ነው ማቴ 2፥16" ለማለት የሚያስደፍር አይደለም ። ምክንያቱም ሃሳቡ ለየቅል ነው።

፨ምንም እንኳን ኢየሱስን እና እናቱን ብፅዕት ድንግል ማርያምን ብንወዳትም የመሰለውን መለጠፍ አይገባንም።እኔ ያልኩት ስህተት ሆኖ ፣ መጽሐፍ ሁሌም ያርመኝ ፣ያስተምረኝ ፣ይገስጸኝ። ለማሳየት የጣሪኩት ወደፊት ገና የሚፈጸም መሆኑን የሚናገር እንጂ የተፈፀመ ታርክ ትረካ እንዳልሆነ ነው።ነፃ ሆናችሁ ለማንበብ የሚትጥሩ መረዳታችኹ አይቀርም ። ስለዚህም እንደ ሐዋርያት በሥልጣን ቃሉን የሚያጸና ፤ መንታ ልብ ላይ የማይጥል፤ በመንፈስና በቃሉ የታጠቀ መልእክት ያስፈልጋልና እነኾ ጆሮ ላሉት ብያለሁ።

## የቤተክርስቲያን ቅድሜ መከራ መነጠቅና ትርክቱ

በትውልዱ ላይ በሃሰተኞች እረኞች የሚሰካው ቀስት በዚህ ብቻ አያበቃም ። እጅግ በጣም ልዩ ልዩና ብዙ ነው። ሁሉንም መዘርዘር ያደክማል ።የከበረውንም መልእክት የመግለጥን ጊዜን ይሻማል ። እረኞች ሃሰተኞች ስለኾኑ የተንቆጠቆጠ ሕንፃ እያስገነቡ ትውልዱን አድክመው ፣ አኹንም ጌታ ከድል በኋላ የሚወስደው የሚነጥቀው ሕንፃ ቤተክርስቲያን ነው በማለት ያጃጅላሉ። እነዚህ የድንዛዘ መርፌ ከመውጋት ሌላ ምርጫ የሌላቸው ክፉዎች ሰራተኞች ጨካኞች ናቸው ። ይኽንን አጭር ጽሑፍ የእግዚአብሔርን እውቀት በቃሉ በላይነት እያስረገጥ[ክ] ከየትኛውም እሳቤና ተቋም ነፃ ኾነ የማታነብ ከኾነ አትጀምር፤ አልተመረጥክም ማለት ነው። ለለውጥ ለእድገት የተዘጋጀ የእግዚአብሔርን እውቀት፣ ሃይልን ፣ጥበብን የሚሻ ብቻ ይብላ።ሰሚ ጆሮ ያለው ብቻ ።

በዚህ አጭር ጽሑፍ ላይ ፥ የራዕይ መጽሐፍ ይዘት፣ ለንጥቀት አስተምህሮ ስባል የተጨነገፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ የክርስቶስ ስውር ዳግም ምጽአት ፣የቤተክርስቲያን ስውር ንጥቀት ፣ከመከራው በስውር የተነጠቁ ቅዱሳን ሰርግ ፥ ይዳሰሳሉ ።በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተነሳውን የሰውን ሃሳብ ስውሩን የሰይጣን ሥራ በቃሉ አስረጂነት አፈርሳለሁ ።

ዳግም በስውር ሳይኾን በግልጥ በሚመጣ ፣

ኹሌተ ሳይኾን አንድ ጊዜ ብቻ ልወስደን በሚመጣ፣

ከመከራው በፊት ሳይኾን ከመከራው በኋላ

ድል ነሺዎችን ለመቀበል በሚመጣ፣

በመምጣቱም ለሙታን ትንሳኤ በሚሰጥ፣

ጌታ አምናለሁ ። በሕይወት ያሉትን ደግሞ ከመቅጽበት

በሚለውጥ መነጠቅ አምናለሁ፤ በክብር ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ በግልጽ እንደተቀመጠው አምናለሁ ።

## 1. የራዕይ መጽሐፍ ይዘት

ይኸንን መጽሐፍ ለማስተማር ኾነ ለማወቅ አብዛኛው አማኝ አይፈልግም ፤ ከመፍራታቸው የተነሳ ልታወቅ የማይችል አድርገው ያስባሉ ።ለዚህ ተጠያቂ የሚኾኑት ደግሞ መንፈስ አልባ የኾኑ በይመስለኛል ትርጓሜ የሚያስተምሩ አስተማሪዎቻቸው ናቸው ። ካላወቅን ካልበላነው እንዴትስ የትንቢቱን ቃል እንጠብቃለን ? እንዴትስ ለመልእክቱ ተገቢውን ምላሽ እንሰጣለን ? የዮሐንስ ራዕይ ጥናት የማታደርግና የማታስተምር ቤተክርስቲያን ያንቀላፋች ናት፤ ልቧ በሌላ የተያዘና በዚህ ዓለም ነገር የከበደችባት፣ ከመቆሸሿም የተነሳ ከላይ በሚያማምሩ ሕንፃዎች [መቃብሮች] ውስጥ ያለች የሚገባ ሬሳ የሞተች ናት ብንል ማጋነን አይኾንብንም። እስካሁን አባል ኾናችኹ ባደጋችኹበት አጥቢያ የዮሐንስ ራዕይ መልእክት በተከታታይ ተምራችኹ ታውቃላችኹ ? ወይም በሕብረት አጥንታችኹ ታውቃላችኹ? ምናልባት ብትማሩም በቀለም ዕውቀት ብቻ እንዲያ ነው ወይም እንዲህ ነው እያሉ በይመስለኛል በግምት የሚታስተምሩ ከኾኑ ፣ የመልእክቱ ተጠቃሚ አትኾኑም።አወዛግበው አወናብደው ይጥሉሃል። ስለዚህም ንቃ እልሃለሁ! የመልእክቱን ቀጥተኛውን ሃሳቡን ለመረዳት ድል ለመንሳት።

የዮሐንስ ራዕይ እንደሌሎቹ መጽሐፍት ብቻው ልጠና ልንማረው የሚገባ መጽሐፍ ነው። ምንም እንኳን በራዕዩ ከዚህ በፊት ያልተገለጠ ዐዲስ ዕውነት የሚገለጥ ባይኾንም። ምክንያቱም ራዕዩ እንዲነገረ የተፈለገው ስላስፈለገው ነው።ለምሳሌ ስለመጨረሻው ዘመን የብሉይ ነቢያትም ተናግረዋል ፤ኢየሱስም ሐዋሪያቱም። ምክንያቱም ስለመጨረሻው ዘመን በተለያየ አቅጣጫ መመልከት ግልጽ የተደላደለ መረዳትና ዝግጅት እንድኖረን ያደርገናል ። ራዕዩን ከዓለም ተነስተን ሳይኾን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማዕከላዊ ሃሳብ ተነስተን በተለይ የዐዲስ ኪዳን መጽሐፍ ስለኾነ በዐዲስ ኪዳን መንፈስ ለመተርጎም ለመረዳት ፈቃደኛ መኾን ያስፈልጋል ።አልያ እንኳር ሃሳቡን አንጠብቅም ። የመልእክቱ ተጠቃሚም አንኾንም።

መጽሐፉ የተጻፈበት ጊዜ የተለያ ሃሳብ ይኖራል ፤"በርካታ ሊቃውንት ግን በ95 ዓ.ም ገደማ እንደኾነ ያምናሉ"[1]። መጽሐፉ በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተገለጡ እውነቶችን በልዩ አቀራረብ በሥዕላዊ መልክ እንደ ትይንት እያዋዛ ያብራራል ። ቍጥሮች ፣ እንስሳት ፣ ተፈጥሮዎች፣ ከተማዎች ፣ስሞች ..በምሳሌያዊ መንገድ የተብራሩ ናቸው ።በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጡ ስለኾኑ ከመጽሐፉ ቅዱስ በመነሳት እንረዳዋለን ። [ከዋክብት መላእክት ናቸው ፣መቅረዞች አብያተክርስቲያናት ናቸው ፤ታላቂቷ ጋለሞታ ባቢሎን የተባለች ሃያል ሀገር፤ሙሽርት የበጉ ሚስት ቤተክርስቲያን በመባል፣ በቍጥሮችም በ7 ቁጥር የሙሉነት የፍጹምነት፣ 4 ቍጥር የዓለምን አራቱን [አቅጣጫ]፣12 ቍጥር ነገድ ለማመልከት የዋለ ስኾን፣ ቀስት አዕምሮ የሚይዝ የሚቆጣጠር ሃይል በማመልከት ውሏል። ፈረሶችም የነገሮችን ፍጥነትና በመልካቸው የያዙትን መልእክት ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል ..። ወደ ውስጥ እየገባን ስለምንመለከት ከመጽሐፍ በቀጥታ ለጥናት አፈታይት እንዲከፈት በወፍ በረር ለማየት እንሞክራለን ።

“ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥” ራእይ 1፥1

ከዚህ ቃል በግልጽ እንደምንረዳው ለዮሐንስ የመጣው መልእክት "ቶሎ ይኾን ዘንድ የሚገባ" እንደኾነ ነው። ራዕዩ አፋጣኝ ምላሽ የሚሻ ነው። ይኸንን መልእክት የተቀበለና የሰማ ኹሉ መልእክቱን ወደ መፈጸም እንዲገባ የሚያሳስብ ነው። ከዚህ በፊት የኾነውን ለመተረክ የቀረበ መልእክት አይደለም ። አባቶችም መጽሐፉን ራዕይ ነው ያሉት ገና የሚፈጸም በመኾኑ ነው። ደግሞም የመልእክቱ ምንጭ እግዚአብሔር [አብ] ስኾን መልእክቱን ለማድረስ የመጀመሪያው ተቀባዩም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ከመኾኑ በፊትም እንደሚላክና ሰው ከኾነ በኋላም እንደሚላክ ደግሞም ከትንሳኤው በኋላም እንደሚላክ እንገነዘባለን ።ይኽ የሚያሳየው የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይነት ፤ የአብ ደስታ መኾን ሰው ስኾን አለመጀመሩን ነው። (በይበልጥ ለመረዳት ትምህርተ ሦስትነት-በአንድነት pdf ይመ)። መልእክቱ ከእግዚአብሔር ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀጥታ ብመጣም ኹሉም መልእክቶች ግን በቀጥታ ከኢየሱስ ወደ ዮሐንስ አልወረዱም ።ኢየሱስ በፋጡር መላአክ በኵል ወደ ዮሐንስ መልእክቱን እንዳስተላለፈ "ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ.." ከሚለው ቃል ተነስተን መረዳት እንችላለን ።

ዮሐንስ በስደት በፈጽሞ ደሰት ላይ ኾኖ [ራዕ1፥9]፣ራዕዩን ከተመለከተበት ግዜ አንስቶ ገና እና ቶሎ የሚኾነው [ከዚህ በፊት የኾነው ሳይኾን] ተመለከተ ።“እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ።” ራእይ 1፥19። በዚህ ቃል "አኹንም ያለውን" የሚለው በሰዓቱ ለነበሩት አብያተክርስቲያናት በቀጥታ የተሰጠ አስቸኳይ ምላሽ የሚያስፈልግ መልእክት ስኾን፣ ለቀሩት ዓለም አብያተክርስቲያናት ግን የየዕለት እራስን መመልከቻና መፈተሻ መማርያ የእግዚአብሔር መልእክት ነው። በሰዓቱ የነበሩት 7ቱ አብያተክርስቲያናት የመጀመሪያው ተደራስያን ናቸው ። “..፥ ሰባቱም መቅረዞች ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።” ራእይ 1፥20።

ስለዚህም ራዕይ መጽሐፍ ዓላማው ይዘት ኹለት ነው ማለት ይቻላል፦ 1ኛው. "አኹን ያለው" የተባለው የ7ቱ አብያተክርስቲያናት ወቅታዊ ሁኔታና መልእክት የያዘ ስኾን፣ ከምዕራፍ ኹለት እስከ ሦስት የተገለጠው መልእክት ነው፣ 2ኛው. "..ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ" እንደሚል ወደፊታዊ ተፈጻሚነት መልእክት ያዘለ እንደኾነ እንረዳለን ።ይኽም ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ነው።

ይኽንን መጽሐፍ ዮሐንስ ራዕዩን በተመለከተበት መንገድ መረዳት ማየት መቻል ያስፈልጋል ።ዮሐንስ የተመለከተው በመንፈስ ኾኖ ነው፤ ስለዚህም እኛም ካለመንፈስ ቅዱስ ምሪት በያዝናቸው አመለካከቶች ተይዘን ለመረዳት ከሞከርን የመልእክቱ ተጠቃሚ አንኾንም፤ በትክክል አለማወቃችንም ከፍርድ ነፃ አያደርገንም ።እንድናውቅ በልግስና የሚሰጠውን፣ መጻሕፍትን እንድናስተውል አዕምሮን የሚከፍተውን ጌታን አጥብቀን ልንለምነው ያስፈልጋል ። የመረዳት ባለጠግነት እንድበዛ ጸጋ እንድጨመረልን፤ ማንም በሠራው ዕሳቤና አስተምህሮ መሠረት ሳይኾን መጽሐፍ ልገልጽ በወደደው መንፈስ ፣ የጥበብ የእውቀት መንፈስ እንድረዳን ሙሉ እገዛ ልንቀበለው ይገባናል ። ምክንያቱም ይኽንን መጽሐፍ አማኞች አገልጋዮች ከራሳቸው መረዳት እውቀት በግምት ኾነው ስለምተረጉሙ ብዙዎች ፣ በትክክል ማወቅ አይቻልም በማለት ተስፋ እንድቆርጡ አድርጓል ። አንድ ልብ አንድ መንፈስ አንድ ሃሳብ ያለው እንዴት የተለያዩ የማይገናኙ ትርጓሜዎችን ይሰጣል ? ይኽ አገልጋዮች አለመግባባት ለሰይጣን ትልቁን በር ከፍቷል ። አዎን ቋንቋን መደበላለቅ ለሥራ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። ኹሉም ትክክል ነው፤ ይኽም ትክክል ነው፤ያም ትክክል ነው የሚሉ 'አዋቂ' አስተማሪዎች እንዲበረካቱ አድርጓል ። ምዕመናትንም አወናብዶ አወዛግቦ እንዳያነቡ አድርጓል ። አንባቢ ኾይ በተወሰነ ደረጃ፣ የተገለጡ ምሳሌዎች ፍንጭ ይዘህ ከዚህ በኋላም በሚጨመረው አፐታይዘር ተመርኩዘህ በእግዚአብሔር መንፈስ ብቻህ ይኽንን የራዕይ መጽሐፍ እንዲትበላ፤ ደግሞም በሕብረትም በቃሉ በላይነት በመሸነፍ እንድታጠና አበረታታለሁ ።

ከላይ በምዕራፍ አራት ላይ ዮሐንስ ራዕዩን ከተመለከተ በኋላ የሚኾኑ የሚከሰቱ የሚፈጸሙ ነገሮችን እንደሚገልጽ ገልጬ ነበር። “ከዚያ በኋላም አየሁ፥ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ፦ **ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያስፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ**።” ራእይ 4፥1።

ዮሐንስ መጀመሪያ ድምጹን ሰምቶ ደንግጦ እንደሞተ ሰው የኾነለት [ራዕ1፥12]፣ "ያ" የፊተኛው ድምጽ ኢየሱስ ክርስቶስ "ከዚያ በኋላ ሊኾን የሚያስፈልገውን አሳያለሁ" አለው። ስለዚህም ከዚህ በኋላ ያሉት መልእክቶች የተፈጸሙትን ሳይኾን የሚፈጸሙትን ዮሐንስ እንደተመለከተ በቀላሉ እንገነዘባለን ። አንባቢ ጭፍን ፈረሳዊ ኾነው ነፍሳቸውን ለሚያጠፉት ሃሰተኞች አስተማሪዎች ጆሮ እንዳይሰጡ በክርስቶስ መንፈስ ኾኜ እመክራለሁ ። ማንም ምንም ስላንተ ነፍስ አይቆምምና። ራስህን ከወደድክ እንዲታመልጥ አሳስባለሁ ።

ዮሐንስ የሰማይ ደጅ ተከፍቶ ኹሉንም በግልጽ ተገልጦለት ማየቱን ፣በዚህ ዓለም ላይ የሚኾነው ኹሉንም ፣አንድንም ሳያስቀር ወገግ ብሎለት ፣ ያለ ድንግዝግዝታ በማያጠራጥር መልኩ በግልጥ እንደተመለከተ ይገልጻል ። ስለዚህም ለዮሐንስ የተገለጠው መንፈስ በእኛም ላይ ያደረው ነውና እንድገልጥልን አዕምሮአችን ይክፈትልን ።በእውነት ማስዋወሉን ይስጠን። በብልሃት በተፈጠረ ፍልስፍና ተረት እንዳንያዝ ይጠብቀን ። ለእግዚአብሔር እራሳችንን አሳልፌን እየሰጠን ዮሐንስ ራዕዩን በጻፈበት መንፈስ ኾነን ለመረዳት ልባችንን እንክፈት ። የሰማይ ደጅ ተከፍቶ [እግዚአብሔር ያለበት] የልባችን ደጅ ተዘግቶ ጠማማ አደግ ኍርንችት እንዳናፈራ።

በመልኩ የሰው ልጅ የሚመስለው ፣ በምድር በነበረበት ግዜ ወደ ደረቱ ተጠግቶ ቀርቦ ይነጋገር የነበረው፣ አኹን ዮሐንስ ተመልክቶ እንደሞተ ሰው የኾነለት ፣ የፊተኛው ደምጽ ሞቶ የነበረ የተነሳ አምላክ፣ ዮሐንስ ከነበረበት ስፍራ ከፈጽሞ ደሴት ወጥቶ እንዲመለከት አመለከተው ፤ወደዚህ ውጣና በማለት ። ዮሐንስ ከፍ ወዳለበት ስፍራ በግልጽ ተገልጦለት እንደተመለከተ እንረዳለን ። ያልተጻፈውን የሚያነቡ ፣በግምት እየፈጠሩ ውሸትን የሚያስተምሩ ሃሰተኛ አስተማሪዎች ይኽንን ቃል በመያዝ "ቤተክርስቲያን የለችም፣ተነጥቃለች ፣ ይኽ ከዚህ በኋላ ያለው የሚያመለክተው እስራኤል ዘሥጋ የኾኑትንና ያልተዘጋጁ አማኞች ብቻ ነው በማለት የውሸት የፈጠራ ስብከታቸውን ፣ትውልዱ እግዚአብሔር ከመኖሪያው የገለጠውን መልእክት ሰዎች ተቀብለው እንዳይለወጡ አስተኝተዋል። እነዚህ ከእንቅልፍ እየቃዡ እየተነሱ በግምትና በድፍረት በይመስለኛል ያለ ሃፍረት ፣በግልጥ የመጣውን የእግዚአብሔርን መልእክትን ያጣምማሉ።

የራዕይ ዮሐንስ መጽሐፍ ምዕራፍ 4-22 ያለው ሙሉ.. ቤተክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ ያለውን ያመለክታል [2] የሚሉ ደፍሮች በቤተክርስቲያን ላይ አዝም የሚረጩ መተተኞችና ውሸተኞች፥ ከእግዚአብሔር ሳይኾን ከሰው የተማሩ ሥጋውያን መኾናቸው በዚህ የተገለጠ ነው። << "ከዚህ በኋላም" ስል ከቤተክርስቲያን መነጠቅ በኋላ ያለውን ያመለክታል >>[3] በማለት የክፍሉ ሃሳብ ዮሐንስ ከተመለከተው ራዕይ እየቀጠለ በተከታታይ ሌላ ራዕይ እየተመለከተ የቀጠለውን ለማመልከት "ከዚህ በኋላም" የተባለው ከአውዱ በመነጠል ፣በመገንጠል የክፍሉን ሃሳብ በማስጨነቅ መነጠቅ ያመለክታል ይላሉ ። ከላይ እንዳልሁት ራዕዩ የያዘው ዓላማ ከይዘቱ ስንመለከት ኹለት ነው ብዬ ነበር። በሰዓቱ ለነበሩት ለ7ቱ አብያተክርስቲያናት ልክ እንደ ገላትያ መልእክት ፣እንደ ቆሮንቶስ

መልእክት ..በሰዓቱ የነበሩበትን ኹኔታ ጌታ አሳይቶ በመልእክቱ አኹን [በሰዓቱ] እየኾነ ያለውን ከገለጠ በኋላ ፣ ወደፊት ደግሞ ገና ልኾን ያለውን መግለጥ ስጀምር [የ7ቱ አብያተክርስቲያናት አኹናዊ መልእክት እንደጨረሰ] ፣ "ከዚህ በኋላ" በማለት በቀጣይ የወደፊቱን ቀድመው ብዙ ዓመታት ወደፊት በመንፈስ መጥቶ የተመለከተውን ፣ መነጠቅ ነው ይላሉ ። እነዚህ ወሸቀው ለያዙት ውሸት አስተምህሮ እንዲመች ብለው ፣ ለወጋቸው ቀንተው የእግዚአብሔርን ልጅ በድፍረት የሰቀሉ ያንገላቱ ፣ ሥጋውያን የኾኑ ምሪት የሌለባቸው ባዶ ደመናዎች ናቸው ። ማነኛውም ሰው ከፍም ዝቅም ብሎ መጽሐፉን በአግባቡ የሚያነብ ማስተዋሉ አይቀርም ። የሰውን ትምህርት ከሰው ሃሳብ የኾነውን ጌታ እንዲንጠብቀው የሰጠው በማለዘብ ለሥጋ እስራኤላውያን ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለውን በመስጠት ፣ "እኛ እንነጠቃለን ከመከራው በፊት" በማለት ብዙዎችን አስተኝተዋል። እነዚህ ዕውር ፈረሳዊያን የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው የሚሸቃቀጡ ወንበዴዎች ውሾች ናቸው ።

<<"ወደዚህ ውጣና"ስል ዮሐንስ ወደሰማይ የወጣው በዚህ አካሉ አይደለም፤በመንፈስ ነው። በመንፈስ ከኾነ ይኽ ለምን ተፈጸመ ስንል የቤተክርስቲያንን የቅዱሳንን ወደ ሰማይ መሻገር የሚተነብይን[የሚገልጽ] እውነት በውስጡ እንደያዘ እናገኛለን ።>>[4] ይላሉ ፤በራሳቸው በሥጋዊ አዕምሮ እየተወዛገቡ ጥያቄ እየፈጠሩ እራሳቸው መልሰው እየመለሱ ፣ በሡሩት ግንብ ታጥረው እየተረገሙ ለራሳቸውም ለሚሰሙት ጠንቅ የኾኑ፣ መጥፍያዎች ናቸው ። በይመስለኛል በግምት ስለንጥቀት የማይናገረውን አውዱን በማስጨነቅ ለማስኬድ ከጅለው የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው ስንቱን ሃይል አልባ አደረጉት ? በዚህ ክፍል ላይ ምንም የጠለቀ ነገር የምጠይቀው ነገር የለም።በግድ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተማርን ፊደል የቈጠርን ነን በማለት ለመራቀቅ ካልደፈሩ በስተቀር ። ምክንያቱም በግልጽ ክብር ምስጋና ይግባውና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ዮሐንስ ራዕዩን ካለበት ከፍ ብሎ ቀርቦ በግልጥ እንድመለከት ስለፈለገው ከነበረበት ፊጽሞ ደሰት ወደዚህ ውጣ በማለት በከፍታ ኾኖ እንድመለከት መናገሩን እንጂ የቤተክርስቲያን መነጠቅ አይደለም ።ከመሠረቱ ወደዚህ ውጣ የተባለው ዮሐንስ እንጂ ቤተክርስቲያን አይደለችም ። ዮሐንስም ራዕዩን ብቻውን ነው የተመለከተው ።እንዲሁም እርሱ መልእክት ተቀባይና ለእኛ አስተላልፍ እንጂ የእኛ ተወካይ አይደለም በዚያ።ኃላፊነቱ በግልጽ በራዕይ መጽሐፍ እንደተቀመጠው በጽሑፉ ማስተላለፍ ነው። 1፥[11] .የምታየውን. በመጽሐፍ ጽፈህ .ላክ አለኝ።... [19] እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ። ራዕ 1፥11-19። የራዕዩን መልእክት እኛ ተደራስያኑ ደግሞ የተጻፈው እንድንጠብቀውና እንድናስፈጽመው የተጻፈ ነው።"ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።"ራእይ 1፥3።

እነዚህ እውራን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሚያደካክሙ ፣ መልእክቱን እየጠበቁ እንዳይኖሩ ሰላምና በረከት ነው የሚሉ ለሌላው መከራ መከራውን ለራሳቸው ሰርግ ነው የሚሉ የዘንደው መንገድ ጠራጊዎች ፤ትውልዱን አፍዝዘው አደንዝዘው የሚያስቀሩ ፣ አይደለም እኛ ዮሐንስ እራሱ ከመከራ ተካፋ አድርጎ በመግለጽ በመከራው በእግዚአብሔር ሃይል ማንም በሌለበት ደሴት ብቻው ታስሮ ፣ እኛ መከራውን እንደሚንቀበል በማመልከት ከእኛ ጋር የመከራው ተካፋ አድርጎ በመቁጠር እየመጣ ላለው ዓለማዊ አገዛዝ እጅን ሳንሰጥ ፤ድል በመንሳት እንድንሻገር **"እኔ ወንድማችሁ የሆንሁ ከእናንተም ጋር አብሬ መከራውንና መንግሥቱን የኢየሱስ ክርስቶስንም ትዕግሥት የምካፈል ዮሐንስ** ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ።" [ራእይ 1፥9]፣ በማለት በእሳቱ በመከራው ማለፋችንን በመግልጽ ስያዘጋጀን፣ የዘንደው መንገድ ጠራጊዎች ሃሰተኛ አስተማሪዎች ግን ብዙዎችን በሚያማምሩ ቃላትና ስብከት ፤በውሸት በማታለል መከራ አያገኛችኹ እንነጠቃለን በማለት ቀጣዩን መልእክት ትውልዱ አንብቦ ድል በመንሳት እንዳይነግስ፣ በዲያብሎስ እንድረግጥ ሃይል አልባ እያደረጉ ይገኛሉ ።ብዙዎችን ያስታሉ እንደተባለው አስተዋል።ጆሮ ያለው ይስማ።

ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ከቤተክርስቲያን መነጠቅ በኋላ ያለውን ያመለክታል ፣ ለማለት ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ከምዕ 6-19 የለም [5] የሚል ሙግት ያነሳሉ ። ይኽ ሃሳብ በትዝብት ላይ የሚጥል ነው። እንደው እንደው እናንተ ፍረዱ ፣ ከላይ ራዕይ መጽሐፍ ከምዕራፍ 4 እስከ 22 ያለው ሙሉ ቤተክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ ያለውን ያመለክታል ብለው ነበር፤ አኹን ደግሞ ለዚህ ቅዠታቸው እንድመች ብለው ከምዕራፍ 6 እስከ 19 አንድም ግዜ አልተጠቀሰም ይላሉ ። ለምን ከምዕራፍ 4 ጀምረው አጠቃላዩን አይሉም ? ቤተክርስቲያን የለችም ብለው ይለ። ለማነኛውም የግድ ቤተክርስቲያን በሚል ቃል ካልተጻፈ አያመለክትም ማለት ነው? እንዲያ ማለት እንችላለን ? ቤተክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ፣ በመንገዱ ያሉ ሐዋ9፤ የበጉ ሚስ፤አካሉ፤እስራኤል ፤ሴትቱ ፣ ሙሽሪት ወዘተረፈ ተብላለች ።ስለዚህም በዚህ ስም ብትጠራ አያመለክትም ማለት እንችላለን ? አንችልም ።አንገተ ደንዳናና ውኃውን ወተት ለማለት ካልቈረጥን በስተቀር ።

በሥጋ ሳይኾን በክርስቶስ መንፈስ "ወንድማችሁ የኾንኩ ከእናንተ ጋር መከራውን የሚቀበል " በማለት መልእክቱ የተጻፈው የኾነ የሥጋ ወገን ለኾኑት እንዳይደለ በግልጽ አስቀምጠው እያለ ፣ በፈሪሳዊያን እርሾ ተመርዘው ልዩ ወንጌል የሚሰብኩ፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ያፈረሰውን የጥልን ግድግዳ እንደገና የሚገነቡ ፣ የያዕቆብን እስራኤልን ሳይኾን በኢየሱስ በእምነት የተወለዱትን የክርስቶስን እስራኤልን ያልተረዱ፣ ጭፍን አንገተ ደንዳና ፈረሳዊያን የኾኑ መምህራን ትምህርት ይኽ ነው። መጽሐፉን በዐዲስ ኪዳን መንፈስ ኾነው ተምረተው ማንበብ

ስገባቸው፣ በፍደል እውቀት በቃላት ስንጠቃ ያወቁ የጨረሱ የሚመስሉ የሰው አዕምሮ ውጤቶች የኾኑ ይኽንን ቃል አይገነዘቡም ፦

"በዚህም *ሥርዓት በሚመላለሱ ሁሉ ላይ* **በእግዚአብሔር እስራኤልም** ላይ ሰላምና ምሕረት ይሁን።" *ገላትያ* 6፥16 ። *በራዕይ መጽሐፍ እስራኤል አይሁዳውያን የሚያመለክት አይደለም* ። በክርስቶስ የአብርሃምን በረከት ተካፋይ የኾኑትን ቤተክርስቲያንን እንጂ። "እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን እኛ የተገረዝን ነንና።" ፊልጵስዩስ 3፥3፣እንደሚል ። በዚህ ላይ በሰፊው እንሞግታለን። የሰውን ሃሳብ እናፈርሳለን ።

ኢየሱስ ክርስቶስ *የሥጋ* እስራኤላውያን አካል ሳይኾን የቤተክርስቲያን አካልና ራስ ነው። በእጁ በፍጹምነት ያለች ቤተክርስቲያን የኾኑቱ እንጂ እስራኤል ዘ*ሥጋ* አይደለችም ። *መጽሐፉ* ለእኛ ያለውን መልእክት በማጣመም *የሥጋ መገረዝን* አለመገረዝ በማድረግ በመንፈስ ከክርስቶስ በመወለድ ያለውን *መገረዝ* [አይሁዳውነት] ያወጀውን እውነት በማዳፈን ፣ በጭፍን ተነስተው የሚትረጉሙ *የሥጋ* ልእልና የሚሰብኩ ፣ በ7ቱ አብያተክርስቲያናት *መካከልም* በሰምርየነስና በፊላደልፊያ ቤተክርስቲያን ተነስተው ነበር። አይሁዳውያን ሳይኾን አይሁዳውያን ነን የሚሉ ፤ የሚሳደቡና የሚዋሹ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ። እነዚህ *የሥጋ* አይሁዳውያን በመኾን አይሁዳውያን ነን ማለታቸው አይደለም ።እንዲያ ብኾን ትክክል ብኾን እንጂ ውሸት አይኾንም። "በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፥ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና፤ ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም። ሮሜ 2፥28-29። ጌታ በ*ሥጋ* በግልጥ አይሁዳውያን የኾኑትን አይሁዳዊ አይደሉም በማለት በመንፈስ *መገረዝ* አይሁዳውያን የኾኑት አይሁዳዊ አድርጎ ይቆጥራቸዋል።በእነዚህ ቤተክርስቲያን ላይ ያሉት በመንፈስ ሳይገረዙ የተገረዝን ነን የሚሉ የክርስቶስ አካል ሳይኾኑ ነን የሚሉ የእግዚአብሔር እስራኤል ያልኾኑ ፣ *መንፈሳዊ* ሽለፈታም የኾኑ ናቸው ። እግዚአብሔር አይሁዳውያን በክርስቶስ በኵል በግልጽ በ*ሥጋ* ዘራቸው የተመጻደቁትን በ*ሥራቸው* የዲያብሎስ ልጆች ናቸው በማለት ከአሕዛብ ለራሱ *መንፈሳዊ* አይሁዳውያን እስራኤላውያን እንደሚያስነሳ ገልጿል ። "በልባችሁም፦ አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ፤ እላችኋለሁና፦ ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር ይችላል።" ማቴዎስ 3፥9 ። እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው የእነርሱ በመቍረጥ ሌላ ልዩ ከእምነት የኾኑት ለመትከል ነው ። ማቴ 3፥10።

እነዚህ በግምት ተነሳስተው በፊደል በቃላት ፍልስፍና በመራቀቅ *መገለጥ* ያለው ይመስላቸዋል ። በግልጽ ለዓለም አብያተክርስቲያናት የተላከውን መልእክትን በመቃወም ፤ *ለሥጋ* እስራኤላውያን በማድረግ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የዋሹ ተንኮለኞች እረኞች ናቸው ።**"እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ። እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ**።"*ራእይ* 22፥16፣*እንደሚል መልእክቱ ለዮሐንስ ወንድሞች ለመከራው ተካፋዮች ለአለም አብያተክርስቲያናት የተላከ ነው። ይኽንን በግልጽ የተቀመጠውን በመቃወም ደብዳቤ ያውም አስቸኳይ መልእክት ያውም የመጨረሻው የትንቢቱ ቃል፣ እንድንጠብቀው የተላከውን ትውልዱ አንብቦ እንዳይጠቀምና እንዳይተርፍ በማደንዘዝ ፣እንዳያስተውል በማድረግ ስንቱ አሳቱ? አንባቢ ኾይ ከምዕራፍ አራት በኋላ ከተነጠኩ በኋላ ያለው ነው በማለት አኹንም ትቦዝናለህ ? የእግዚአብሔርን መልእክት ቸል ትላለህ ? እኔ የሚናገረው ለሚሰሙት ነው። ጆሮ ያለው ይስማ።*

እነዚህ ፈረሳዊያን በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተነሱ የዘንዶው መንገድ ጠራጊዎች ያልተጻፈውን የሚያነቡ የተጻፈውን የሚክዱ ፣ ትውልዱን በልዩ መርዝ በጥበብ የመረዙ ያስተኙ ናቸው ። ቤተክርስቲያን ሙሽሪት በምድር ላይ በዓለም ኹሉ ያለችው አካሉ ናት በማለት እንደሚትታጣ የሚገልጸው የዓለም አብያተክርስቲያናት መልእክትን በማጣመም፣ መርጠው የወደዱትን የሚቀበሉ መናፍቃን በስውር የሚሠሩ ፣ ከትበለጽጋለ ባላነሰ መንገድ ትውልዱን ያደነዘዙ ናቸው ። እነዚህ በአብዛኛው አንቱ የተባሉ ስለኾኑ እውነትን እያወቁ ብዙዎች ዝም እንዲሉ አድርጓል ። የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው። ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አልሠራም ። በነፍሴ ተወራርጀ እውነትን እናገራለሁ ። ከጥልቁ ከስውሩ ከሰይጣን ትምህርት እንዲታመልጡ አሳስባችኋለሁ ። ክርስቶስ ልመጣ ነው። "መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ። የሚሰማም፦ ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።" ራእይ 22፥17 ። ስለዚህም በምድር ያለችው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሙሽርት የበጉ ሚስት ተናፍቃ ውዷን ትጣራለች፤ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኾና። ምክንያቱም መልእክቱ ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ ያላት ለራሷ እንደኾነ ገብቷታል። ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ከቤተክርስቲያን ንጥቀት በኋላ ያለውን ሙሉው የሚያመለክት ነው ካልን፣ ቤተክርስቲያን ተነጥቃ እያለች ማራናታ ጌታ ኾይ ና እያለች ነው? በጌታ በኢየሱስም ። ውሸት ከእናንተ ይራቅ። በእግዚአብሔር ቃል ላይ መቀለድ መድፈር ከእናንተ ይራቅ ። ይኽንን የትንቢቱን ቃል ቤተክርስቲያን ተነጥቃ እያለች ነው የሚትጠብቀው ? በምድር በመከራው እያለች አይደለችምን ? ነው። ከእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ የመጣውን መልእክት ስትሰማ ፣ልትጠብቅ እንደሚገባት አውቃ፣ ባለችበት ቦታ ኾና በዓለም በምድር ላይ፣ ውዷን ትጣራለች ። ወዳጆቼ አትጥፉ። ነፍሳችኹን አሳልፋችሁ አትስጡ ። በቅዠት በቀልም በቃላት እውቀት ተራቀቅን ብለው የሚናገሩትን ባዶ ደመና የኾኑ መምህራንን አትስሙ። ወደ ቃሉ

ተመለሱ ::ክርስቶስም ውዴ ኸይ ጆሮሽን አዘንቢይ ይልሻል:: እንቢ አትበል መልእክቱ የተጻፈው ለአንተ/ለአንቺ ለእኛ ነውና::

ይኽንን እውነት እንድታነብ እንድታውቅ ጌታ ዕድል ሰጥቶሃል፤ ኹሉም በአፍህ ቀርቧል:: እያወቃችሁ ተራ መረዳት ነው ወይም ችግር የለም በማለት ቀለል እና ለዘብ አድርጋችሁ ፣አመለካከት ብቻ አድርጋችሁ ቄጥራችኹ የምታልፉ መምህራን ከማስመሰል እንድትወጡ የበጉን መልእክት በግልጽ እናገራለሁ ::ምክንያቱም የትንቢቱን ቃል ስመጣ ከሰው አዕምሮ የመጣ አይደለም ::እንደገዛ ፍላጎታችን እንድንተረጉመው እንድንራቀቅበት የተሰጠ አይደለም :: "በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል::" ራዕ 22 ፥18-19:: የራዕዩን መልእክት ለሚሰማ ለኹሉ እንዲሰማና እንዲጠብቀው የተሰጠ እንጂ ለእስራኤል ዘሥጋ ብቻ ለጥቅት አሕዛቦች የተላከ አይደለም ::ያለ ልዩነት ለሁሉ ለሰው ልጆች በሙሉ የተላከ የተሰጠ መልእክት ነው::ጌታም ለእስራኤል ዘሥጋ ብቻ ሳይኾን ለሰው ልጆች ኹሉም ምስክር እንደኾነ ገልጿል ::ምክንያቱም መልእክቱ ሁላችንም ሰምተን ተገቢውን ምላሽ እንድንሰጥ የተጻፈ ነው:: ጆሮ ያለው ይስማ::

ለእኛ በፍጻሜ ዘመን ላይ ላለነው አንብበን እንጠቀም ዘንድ፣ ከሺህ ዓመት በፊት በጌታ ቶሎ ልኾን የሚያስፈልገው የተገለጠውን በክርስቶስ መንፈስ በማንበብ በክርስቶስ ፊት በመኾን የበለጠ ለመረዳት እንድንረዳ ዘንድ በግልም በጽሞና እንድታነብ አበረታታለሁ:: መጋቢዬ ያስተምረኛል ብለህ አትቦዝን:: የኾነ እሳቤ ውስጥ ተጨቃይቶ ለሡራው አስተምህሮ በመጠንቀቅ እየተረጎመ እንዳያወዛግብህ በመንፈስ ምሪት ፣ ከኹሉም በላይ በኾነው አስተማሪ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እንድታነብ አበረታታለሁ :: የራዕይ መልእክት በነቢያት ኾነ በኢየሱስ ወይም በሐዋርያት ከተገለጠው ዘመን ፍጻሜ መልእክት ልዩና ዐዲስ የኾነ አይደለም :: ራዕዩ ራሱ ወደፊት የሚኾነው በተለያየ መንገድ በተለያየ አተያይ የሚያብራራ ነው:: ይኽንንም እንደ ካሜራ[6] ከተለያየ አቅጣጫ እንደተቀረጸ ክስተት ፣አንዷን ነገር በዝርዝር ሙሉ መረዳት እንድኖረን የተገለጠ መጽሐፍ እንደኾነ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ፍንጭ እንመለከታለን ::አንድን ሰው ከፊለፊት፣ ከወኂላ፣ ከላይ፣ ከጎን ፣ ከተለያየ አቅጣጫ በተቀረጸው ካሜራ ብንመለከት ፣ነገሩን ራሱን በሚሉአት መረዳትና ማየት እንደሚቻል የተገለጸ ነወ፤እንዲያ ያለም የትንቢት ቃል ነው::

ከምዕራፍም አራት ጀምሮ ያለው" የቤተክርስቲያን መከራ መቀበልን"የሚያመለክተውን መልእክት የያዘ ነው:: አስተውሉ ከላይ እንዳልሁት ዮሐንስ እየተመለከተ ያለው ያለፈውን የተፈጸመውን አይደለም ፤ገና መኾንና መመፈጸም ያለበትን ነው:: ዮሐንስ አብን በዙፋኑ ተቀምጦ ይመለከተዋል ::ራዕ 4፥2-3:: ደግሞም በዙፋኑ ዙሪያ 24 ሽማግሌዎች ነበሩ::ቊ.4:: እነዚህ ገማቾች እንደሚሉት ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ በስውር የተነጠቁ ሳይኾኑ፣ በብሉይ መሠረት 12 እስራኤል ዘሥጋ ነገድ ቅዱሳንና 12 የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳን በሐዋርያት መሠረት የተመሠረቱ ቅዱሳን የሚገልጹ ናቸው :: ደግሞም ግና የሚኾነው እየተመለከተ እንጂ የኾነውን የኾነ ዘመን የተከሰተውን ክስተት እንደሚመለከት ፣መፈላሰፍ አስፈላጊ አይደለም :: "እነዚህ 24 ሽማግሌዎች የመከራው ዘመንና 144,000 እስራኤላውያን ሳይነጠቁ በፊት የተነጠቁት ቅዱሳን አማኞች ጉባዔ ተወካዮች ልኾኑ ይችላሉ:: ኾኖም መቼና የት እንደነበሩ ፣እነማን እንደኾኑ ለማወቅ ይቸግራል ::"[7] እነዚህ ከመገመት ውጪ ምሪት የሌለባቸው በግምታቸው እንደ አዋቂ የሚቆጠሩ ፥ሰዎችን የሚያወዛግቡ ባዶ ደመናዎች ፣ ሰውን ኹለት መንታ ልብ ላይ በማድረግ በጥርጣሬ ላይ የሚጥሉ ፣ ከንቱ አስተማሪዎች፣ ገማችና ደፋር የኾኑ፣ በይመስለኛል የሚመሩ የመጽሐፉን መንፈስ ያልተገናዘቡ፣ በሰዎች ዘንድ የሚታወቁ አንቱ የተባሉ ስም ያላቸው ግን የሞቱ ናቸው :: ከወዴት እንደ ወደቁ ብመለከቱ መልካም ነበር:: ከሰው አዕምሮ የተወለደ ትምህርት ኹሌም እንዲህ ቅልምድምድ ያለ ነው:: እነዚህ በሰማይ የነበሩ ሳይኾኑ እንዲያ እንደሚኾን ዮሐንስ እንደተመለከተ ብገነዘቡ እኮ ፣ በዙፋኑ ዙሪያ ከብበን እርሱን ብቻውን እያመሰገንን እያመለክን እንደምንኖር የሚገልጽ መኾኑ ባልጠፋባቸው ነበር:: ገና ምዕራፍ አራት ስንጀምር ልኾን የሚገባውን ዮሐንስ እንደሚመለከት ገልጠን ነበር:: ታዲያ እንዴት ከዚህ በፊት የተነጠቁ 24 ቅዱሳንን በሕሳብ አሃዝ እንረዳለን? እንተረጉመዋለን? በመንፈስ ምሪት እርገጠኛ አለመኾኑ ያመጣው የተለያየ እሳቤ ተጠቂ መኾንን እንጂ ድል የነሱ ቅዱሳንን ያለ ሥጋ ዘር ልዩነት የሚያመለክት ነው:: ጆሮ ያለው ይስማ:: በነጭ ልብስና[በቅድስናና] በተጋድሎአቸው አክሊል ደፍተው ያሉት ደግሞም በክብር ለእርሱ ስለኾኑ የተቀመጡት ቅዱሳን የኾኑ ሁሉ ናቸው እንጂ መላእክት ኾነ፣ በስውር የተነጠቁ 24 ሰዎች ብቻ አይደለሁም ::

"በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙሪያ፥ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ።" ራእይ 4፥6 ።እነዚህ ቅዱሳን በቤተመቅደስ የነበሩ ያኔ እርሱ ስገለጥ፣ ተከፍሎ የነበረው ኹሉ እንደሚሻር፣ ሙሉ እውቀትና ሙሉ መረዳት እንደሚኖራቸው ሐዋርያው በመልእክቱ እንደገለጸው ፣ "ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤ ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።" 1ቆሮ 13፥9-12። የዓይኖች ትላልቅና በዓይኖች የተሞሉ መኾን፣ ኹሉም ነገር ግልጽ እንደኾነላቸው የተሰወረ ነገር እንደሌለባቸው የሚያሳይ ነው።እግዚአብሔርን ፊትለፍት በክብሩ እንደሚመለከቱ ፣ ጌታ በሐዋርያው ጳውሎስ የገለጠውን ተስፋ ዮሐንስ ተመልክቶ ትዕይንቱን በማብራራት በዝርዝር አስቀምጧል ። 24 ሰዎች ቅዱሳን ብኾኑ ጌታ የሚወደው አገልጋይ ከእነርሱ መሃል እንጂ ተመልካች አይኾንም።ነገርግን በደሴቲቱ ማንም በሌለበት ለሥቃይ ለመከራ ተሰጥቶ የተጣለ ብኾንም፣ ብዙ ወገንና ብዙ እረፍት ደስታ መኖሩን፣እንደሚጠብቀውም በመመልከት እየተጽናና ተቀምጧል ። አራት እንስሶች አራቱን የምድር ማዕዘን የሚያመለክቱ የፍጥረታት ወክል፣የማይታየው የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ የተገለጠባቸው ናቸው፤ሮሜ 1፥19-20። ፍጥረታትም መንፈሳዊ ዓይኖች የበራላቸው እግዚአብሔር ስያመልኩ፣ 24 ሽማግሌዎች ጥበብ የሞላባቸው [ቅዱሳንም]] ስያመሰግኑ እንመለከታለን ።

በምዕራፍ አምስት የዓለም እንቁቁልሽ የያዘውን መጽሐፍ እግዚአብሔር እንደያዘውና ቊ.1፤ የእንቁቅልሽ ፍቺ በመስጠት ልቆጣጠረው የሚችለው የታረደው በግ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኾነ ቊ.5 ያስገነዝበናል ። ስለዚህም ምክንያት በጉን መላእክቱ ፍጥረታቱ ቅዱሳኑ ኹሉም አመለኩ አወደሱ ።ቊ.8-12።

***1ኛው መግለጫ.** . ከምዕራፍ ስድስት ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 8፥1 ድረስ ያለው የመጀመሪያው የፊለፊት ካሜራ የተቀረጸውን ምስል ያሳየናል ።በዚህ እየመጣ ባለው ሥራዓት ቤተክርስቲያን በመከራው እንደሚታልፍ እንደሚትሻገር ይገልጻል ። በዓለም ላይ የሚኾኑ ክርስቶስ የገለጻቸው ምስጥራት!

#1. "አየሁም፥ እነሆም፥ #አምባላይ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ቀስት ነበረው፥ አክሊልም ተሰጠው፥ ድልም እየነሣ ወጣ ድል ለመንሣት።" ራእይ 6፥2

፨ ይኽ ፈረስ ገዳይ ቀስት አለው፣ አክሊልም ጥበብና እውቀት አለው፣ ድልም ያደርጋል ። በሃሰተኛ ትምህርት ወደ እልቂት ያመራል ።

#2. "ሌላም #ዳማ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ ለተቀመጠው ሰላምን ከምድር ይወስድ ዘንድ ሰዎችም #እርስ_በርሳቸው እንዲተራረዱ ሥልጣን ተሰጠው፥ ታላቅም ሰይፍ ተሰጠው።" ራእይ 6፥4

፨ ቀዩ ፈረስ የወንድማማቾች [የአንድ ወገን] ጦርነት ያመላክታል ። በዚህም ምክንያት ሰላም ይጠፋል ።

#3." ሦስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ሦስተኛው እንስሳ፦ መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ። አየሁም፥ እነሆም፥ ጕራቻ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው በእጁ #ሚዛን ያዘ። በአራቱም እንስሶች መካከል ድምፅ፦ #አንድ_እርቦ_ስንዴ_በዲናር ሦስት እርቦ ገብስም በዲናር፥ #ዘይትንና_ወይንንም አትጕዳ ሲል ሰማሁ።" [ራዕ 6፥5-6]

፨ ይኽ ጥቁር ፈረስ የኑሮ ውድነት በከባድ ሁኔታ እንደሚከሰት የሚገልጽልን ነው።ነገርግን በዘይትና በወይን ላይ የዋጋ ንረት እንዳይመጣ የተወሰነ ገደብ ከኢየሱስ ተጥሏል ።

#4. "አየሁም፥ እነሆም፥ ሐመር ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ስሙ ሞት ነበረ። ሲኦልም ተከተለው፤ በሰይፍና በራብም በሞትም በምድርም አራዊት ይገድሉ ዘንድ ከምድር በአራተኛዋ እጅ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው።" ራእይ 6፥8

፨ ይኽ ግራጫ ፈረስ ሞትን የሚያመጣ ነው። ከምድር አንድ አራተኛ (1/4) ያህልን ልያጠፋ የሚችል ነው።ሰዎችንም እንስሳትንም፤ በተፈጥሮ አደጋ ፣ በራብ ፣በጦርነት በተለያዩ ግዜ በተለያየ ሃገር ላይ የሚከሰት

ነው። [ይህ ጦርነት የእርስበርስ ጦርነት አይደለም] ። የዓለም ጦርነት ዓይነት ፥ ትልቅ እልቅት የሚያስከትል ነው ።

#5."አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ። በታላቅ ድምፅም እየጮኹ፦ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ #አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ #አትበቀልም? አሉ። ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፥ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር #እስኪፈጸም ድረስ፥ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው።

፨ በግፍ የተገደሉ አማኞች የእግዚአብሔር ፊትህ ይጠይቃሉ ፤ ጌታም እንደእርሱ ታምነው የሚሞቱ ስላሉ ትንሽ ግዜ ጠብቁ አላቸው ።

#6." ስድስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ፥ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጕር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፥... ሰማይም እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ፥ ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ።... ታላቁ የቍጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም ይችላል? አሉአቸው።" [ራዕ 12፥6-12]

፨ በመጨረሻም እግዚአብሔር ለዚህች ምድር ታላቅ እልቂትን ያደርጋል ። የትኛውም የቴክኖሎጂ ዋሻቸው አያስመልጥም። ለእኛ ለአማኞች ግን መሸሸጊያ አለ። ኖኅ በመርከብ እንደተረፈ በዚያን ሰዓት በኢየሱስ እንሸነፋለን። ይኽ ግዜ ለአማኞች ታላቅ የምስጋና ግዜ ነው። ታርደሃልና ይገባሃል ።

#7. “ሰባተኛውንም ኅተም በፈታ ጊዜ እኵል ሰዓት የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ።” ራእይ 8፥1

፨ ዝምታ ሆነ፣ ለቅሶም አብቅቷል።

*የውስጥ ሰላም ያገኛችችሁ ፣

የመጸለይ አቅም ይስጣችሁ ፣

ተስፋችን የታመነ ነው፣

ዘመኑን እወቁ፣

በእውቀት ኅልምሱ ፣

*በዚህ ፊልፊት ካሜራ የተቀረጸውን የዓለምን መጨረሻ ክስተት ተመልክተናል፤ ከዚህ በመቀጠል ያሉትንም ይኽንን ክስተት በዝርዝር ከተለየየ አቅጣጫ እንደተቀረጸ ካሜራ ያሳዩናል ።ስለዚህም ሙሉ መረዳት እንድኖረን ጌታ ከሚያሳየው አቅጣጫ እየተመለከትን እንቀጥላለን ።እነዚህ አራቱ ፈረሶች የጨለማ ሃይል ምሳሌ የኾኑ መቅሰፍትን የሚያመጡ ናቸው ። ቤተክርስቲያን በዚህ እየታረደች እየተሰቃየች ታልፋለች ። የተዘጋጀው ቤተክርስቲያን በመከራ ውስጥ በምድር ብትኾንም ጌታ ይሸሽጋታል፤ መቅሰፍት የሚያመጡ ጨለማ ሃይሎች በእግዚአብሔር መላእክት ቍጥጥር ውስጥ ናቸው ።“የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጕዱ አላቸው።” ራእይ 7፥3 ። ከዚህ በላይ ጉዳት እንዳይደርስ እግዚአብሔር የራሱ የኾኑትን ልለያቸው ፈልጓል።ልያትማቸው።ምክንያቱም በስድስተኛው ማህተም ዮሐንስ የተመለከተው መልእክት የዓለምን ፍጻሜ የሚሰጥ መቅሰፍት ስለኾነ፣ ጥያቄ ኾኖ በታል ማንስ ልድን ይችላል ብሏል ።“የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን ወይም ዛፎችን አትጕዱ አላቸው።” ራእይ 7፥3 ። በዚህ መከራ ውስጥ ቤተክርስቲያን ብትኾንም የመጨረሻው እልቅት እንዳያገኛት ጌታ ፣የእርሱ የኾኑት እስኪለዩ ድረስ እስኪሞሉ ድረስ የስድስተኛው ማህተም መቅሰፍቶች አይመጡም ፤አይደርስም ።

ለዮሐንስ ታላቁ ቊጣ "ማን ልድን ይችላል?" አስብሎታል። "ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም ይችላል? አሉአቸው።"ራእይ 6፥17 ። እግዚአብሔርም 144,000 እስራኤላውያን እንደዳኑ የእነዚህም ሃሰተኞች ፈረሳዊያን እንደሚሉት የሥጋ እስራኤላውያን እንዳይደሉ ፣ ከሕዝብ ኹሉ የወጡ መኾናቸውን ይገልጻል ፦"ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤" ራእይ 7፥9 ። እነዚህ የራዕይ መጽሐፍ ቊጥሮች በህሳብ አሃዝ ልንተረጉመው የተገባ አይደለም ። ምክንያቱም ሊቆጥራቸው የማይቻሉትን ተመልክቶ ቁጥር ደግሞ 144,000 ሺህ ብሎ መግለጹ አንድ አይደለም ።ምክንያቱም በሕሳባው አሃዝ አይደለም የቆጠረው ። በሕሳብ ሊቆጥራቸው አይችልም ከብዛታቸው የተነሳ ብኋል። በምሳሌያዊ ትርጓሜ ከኾነ ግን በቀላሉ 144,000 ሺህ ብሎ ገልጿል ። መላእኩ ቊጥራቸውን ነግሮለት አይደለም ። የመልእክቱን ሃሳብ ተረድቶ እንጂ። እነዚህ ጭፍን ፈረሳዊያን በግምት ተነሳስተው እንደሚሉት አይደለም ።ዮሐንስ ማንስ ይድናል ስል ራሱን ጭምር በጥያቄ ውስጥ አካትቶ ነው።ሺህ "አንድ ሺህ" የሕሳቡን ቊጥር የሚወክል ሳይኾን እጅግ በጣም ብዙ ብዙውን ለመግለጽ የዋለ ነው። እነዚህም እስራኤል ዘሥጋ ሳይኾኑ እስራኤል ዘነፍስ በመንፈስ የተገረዙ የእግዚአብሔር እስራኤሎች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሙሽሪት ናቸው ፤ ከነገድና ከቋንቋ የወጣች የአንድ ዘር ሥጋ ሕብረት ያይደለች፤ በጌታ መንፈስ ግን አንድ የኾነች ፤ አካሉና ሙላቱ ናት። እነዚህ የታተሙት በያዕቆብ እስራኤል ምሳሌ የቀረቡ በእምነት የተወለዱ የእግዚአብሔር እስራኤሎች ናቸው ።በዚህ ጉዳይ በቀጣይ ክፍል እንደ ጌታ ፈቃድ በሰፊው እናያለን ።የሰይጣንን የስውሩን ትምህርት አዝምን እንገልጣለን ። እናፈርሳለን ።

***2ኛው መግለጫ.** . ከምዕራፍ 8፥2 ጀምሮ እስከ 11፥17 ያለው ለዓለም በጌታ የሚሰጡ ማስጠንቀቂያዎች[8] ናቸው ። በዚህኛው ካሜራ በዓለም የሚኾኑ ነገሮችን በጎን እንደተቀረጸ ካሜራ ብንመለከት ለመረዳት ይረዳናል ። ዓለምን ከማጥፋቱ በፊት በተለያየ ጊዜ የተለያየ የማስጠንቀቂያዎችን እንደሚያስተላልፍ [እንደሚሰጥ] እንገነዘባለን ። "በእግዚአብሔርም ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን መላእክት አየሁ፥ ሰባትም መለከት ተሰጣቸው።" ራእይ 8፥2። ሰባቱ መለከቶች በእግዚአብሔር ለዓለም የቀረቡ ማስጠንቀቅያዎች ናቸው ። ማስጠንቀቂያ በራሱ የምህረት እድልን የሚያመለክቱ ናቸው ።ምክንያቱም እንዲመለሱ ስለሚፈልግ ነው የሚያስታውቀው ። እስኪ ለዓለም የቀረቡ 7 ማስጠንቀቅያዎችን እንመልከት ፦

፨ በፊተኛው መለከት "ፊተኛውም መልአክ ነፋ፤ ደምም የተቀላቀለበት በረዶና እሳት ሆነ፥ ወደ ምድርም ተጣለ፤ የምድርም ሲሶው ተቃጠለ የዛፎችም ሲሶው ተቃጠለ የለመለመም ሣር ሁሉ ተቃጠለ።" ራእይ 8፥7 ። ምድርን የሰውን አከባቢ የሚመታ መቅሰፍት ስኾን ከምድር አንድ ሦስተኛው ተጠቂ ይኾናል ።

በሁለተኛውም መልአክ ነፋ፤ በእሳት የሚቃጠል ታላቅ ተራራን የሚመስል ነገር በባሕር ተጣለ፤ የባሕርም ሲሶው ደም ሆነ ፣በባሕርም ከሚኖሩ ሕይወት ካላቸው ፍጥረቶች ሲሶው ሞተ የመርከቦችም ሲሶው ጠፋ። ራዕ 8፥8-9። የመርከቦች መመታት ዋናው የንግድ ትሥሥር በማጥቃት የኢኮኖሚያዊ ጥቃት የሚያመጣ እንደኾነ ስያመለክት፣ በዚህም ሲሶው[⅓]ይመታል። በባሕር ውስጥ ያሉ እንስሶች በከፍል ይመታል ።በዚህ መቅሰፍት ዋናው ጥቃት የሚያርፈው በንግድ ላይ ነው።

፨ ሦስተኛውም መልአክ ነፋ፤ እንደ ችቦም የሚቃጠል ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ፥ በወንዞችና በውኃም ምንጮች ሲሶ ላይ ወደቀ። የኮከቡም ስም እሬቶ ይባላል። የውኃውም ሲሶ መራራ ሆነ መራራም ስለተደረገ በውኃው ጠንቅ ብዙ ሰዎች ሞቱ። ራዕ 8፥10-11። ለመጠጥ የሚኾነው የተፈጥሮ ሃብትን ውኃውን በመመረዝ ጥቃት የሚያደርስ ስኾን፣በዚህም ⅓ኛው ብቻ ከምድር ይመታል ።

፨ "አራተኛውም መልአክ ነፋ፤ የፀሐይ ሲሶና የጨረቃ ሲሶ የከዋክብትም ሲሶ ተመታ፥ የእነዚህ ሲሶ ይጨልም ዘንድ፥ የቀንም ሲሶው እንዳያበራ፥ እንዲሁም የሌሊት።" ራእይ 8፥12 ። " እግዚአብሔርም ሙሴን፦ እጅህን ወደ ሰማይ ዘርጋ፥ በግብፅም አገር ላይ ሰው የሚዳስሰው ፅኑ ጨለማ ይሁን አለው። ... ማንም ወንድሙን አላየም፥ ሦስት ቀንም ሙሉ ከስፍራው ማንም አልተነሣም፤ ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ግን በተቀመጡበት ስፍራ ብርሃን ነበራቸው።" ዘጸ 10፥21-22። ልክ እንደዚሁ ከምድር ⅓ኛው በጨለማ ስዋጥ፣በሌሎች አከባቢዎች ብርሃን ይኖራል

:: ብርሃን ያለበት ቅዱሳን ስለኾኑ አይደለም ::ጌታ የዘመኑን ፍጻሜ ለማስታወቅ የሚጠቀመው ምልክት ስለኾነ እንጂ::

“አየሁም፥ አንድም ንስር በሰማይ መካከል እየበረረ በታላቅ ድምፅ፦ ሊነፉ ያላቸው የሦስቱ መላእክት መለከት ስለሚቀረው ድምፅ በምድር ላይ ለሚኖሩት ወዮላቸው፥ ወዮላቸው፥ ወዮላቸው ሲል ሰማሁ::”ራእይ 8፥13 :: ከአራቱ መለከቶች ማስጠንቀቅያዎች በኂላ የሚመጣው የቀረው 3ቱ ማስጠንቀቂያ ጥቃቶች አደገኞች ስለኾኑ፣ በምድር ላይ ለሚኖሩት የወዮታ ድምጽ ያሰማል ::

፨“አምስተኛውም መልአክ ነፋ፤ **ከሰማይም ወደ ምድር ወድቆ የነበረ ኮከብ** አየሁ፥ የጥልቁም ጉድጓድ መክፈቻ ተሰጠው::” ራእይ 9፥1 :: በዚህ መለከት ላይ ሰማይ በሰማያዊ ስፍራ የነበረ ኮከብ መውደቁ ፣ የሰይጣንን ከሰማያዊ ስፍራ መጣልን ያመለክታል :: በዚህም ከጥልቁ ያሉትን የራሱ ጭፍራዎችን ይዞ ታላቅ ስቃይ መከራ እንደሚያመጣ ያስረዳል ::ይኽንን መጽሐፉ የመጀመሪያው ወዮ ይለዋል ::ቍ.12:: በዚህም ሰዎች መሞት ብፈልጉም አይሞቱም አይገድልም ያሰቃያል ለ5ወራት ::“በዚያም ወራት ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ አያገኙትምም፥ ሊሞቱም ይመኛሉ ሞትም ከእነርሱ ይሸሻል::” ራእይ 9፥6 :: ምንም እንኳን ሰይጣን ከሰማይ በመውደቁ ስቃይ ለማብዛት ብታትርም የታተሙ ቅዱሳንን ድል የሚነሱ ኃይልን የተላበሱትን ልጎዳ አይችልም :: “የእግዚአብሔርም ማኅተም በግምባራቸው ከሌለባቸው ሰዎች በቀር በምድር ያለውን ሣር ቢሆንም ወይም ማናቸውንም የለመለመ ነገር ወይም ማናቸውንም ዛፍ እንዳይጐዱ ተባለላቸው::”ራእይ 9፥4:: ከላይ የሚታተሙት እንዳሉትና ለእነርሱ ተብሎ መቅሰፍቶች እንዳይመጡ መከልከሉን ተመልክተናል :: በምዕራፍ ሰባት :: የእነዚህ መንፈሳዊ ቍጥራቸው 144,000 ነው::በሕሳብ ቍጥር ግን ተቆጥረው የማያልቁ ናቸው ::በዚህ ክፍል ላይ ደግሞ የታተሙትን መከራው ታላቁ ስቃይ አያገኛቸውም ? እነዚህ እነማን ናቸው ? ወዳጄ ብዙ ዘመን በውሸት በፈጠራ ስብከት ተታልለህ ይኾናል:: እነዚህ የሚታተሙት እስራኤል ዘሥጋ ናቸው ብሉም መልእክቱ ለእነርሱ ነው ብሉም ፣ በመከራ ይድናሉ ብሉም ፣ በዚህ ክፍል ላይ ግን የሚታተሙ ልዩ ቅዱሳን መከራ የማያገኛቸው ፣ የዲያብሎስ ወደ ምድር መውረድ ምንም  ልያደርግባቸው ያልቻለባቸው፣ ከእርሱ ቍጥጥር በላይ የኾኑ ፣ እንዳሉ መጽሐፉ ይመሰክራል :: ስለዚህም እነማን ናቸው ? ሰይጣን እንዳታውቅ የደበቀ ምስጥር አለና ልገልጽ ነው:: ጆሮ ያለው ይስማ:: በሰፊው በቀጣይ ክፍል እንመለከታለን ::አንተ ግን ልብህን አዘጋጅ ፤ ከጠመጠሙ ጥምጣም ተላቀ ውጣ::ከመከራው በፊት  እነጠቃለሁ መልእክቱ ለእስራኤላዊያን ነው እንጂ እያልህ ተኝተህ በመከራው እንዳትነጠቅ እመክራለሁ ::

፨ ስድስተኛውም መልአክ ነፋ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ካለ በወርቅ ከተሠራ መሠዊያ ቀንዶች አንድ ድምፅ ሰማሁ፥መለከትም ያለውን ስድስተኛውን መልአክ፦ በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ የታሰሩትን አራቱን መላእክት ፍታቸው አለው:: …  ከአፋቸውም በወጡት በእሳቱና በጢሱ በዲኑም በእነዚህ ሦስት መቅሰፍቶች የሰዎቹ ሲሶ ተገደለ:: ራእ 9፥13-18:: የምድር ⅓ኛው በታላቅ ጥፋት ተመታ ::የሰው ልጅ ግን እስካሁን ንስሐ አልገባም :: ልገባም አልወደደም :: የመጨረሻው ማስጠንቀቂያና ነበር ::“ስለ መግደላቸውም ቢሆን ወይም ስለ አስማታቸው ወይም ስለ ዝሙታቸው ወይም ስለ ስርቆታቸው ንስሐ አልገቡም::” ራእይ 9፥21 ::

፨ ከስድስተኛው መለከት በኂላም የሰው ልጅ በደል እየባሰ በመሄዱ በዚያ ጊዜም ጌታ ሰባተኛ መለከት ከመነፋቱ በፊት የንስሐ እድል ይሰጣል:: “ወደ ፊት አይዘገይም፥ ዳሩ ግን ሰባተኛው መልአክ ሊነፋ ባለው ጊዜ ድምፁም በሚሰማበት ዘመን፥ **ለባሪያዎቹ ለነቢያት የምስራች እንደ ሰበከላቸው የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል** አለ::” ራእይ 10፥7 :: እስካሁን እየኾነ ያለውን የተረዱት ባሪያዎቹ ነቢያት ምስጢሩን ገልጠው እንዲያስተምሩ ጌታ ያደርጋል :: “በብዙ ወገኖችና በአሕዛብም በቋንቋዎችም በነገሥታትም ላይ እንደ ገና ትንቢት ትናገር ዘንድ ይገባሃል ተባለልኝ::” ራእይ 10፥11 :: ዮሐንስንም የትንቢቱን ቃል መግለጥና ማስተማር እንዳለበት ያዝዛል :: ይኽ እንዲኾን ለዮሐንስ የተሰጠው መልእክት ቃሉን በሥልጣን እንዲያስተምር ነው:: ለባሪያዎቹ ለእኛ አኹን በፍጻሜ ላለነው እንዴታ ?

ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ::እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው::ማንምም ሊጐዳቸው ቢወድ እሳት ከአፋቸው ይወጣል ጠላቶቻቸውንም ይበላል፤ ማንም ሊጐዳቸው ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል:: እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት

ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው፥ ውኃዎችንም ወደ ደም ሊለውጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው።ምስክራቸውን ከፈጸሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፋቸውማል ይገድላቸውማል። ራዕ 11፥3-7።

ሰይጣን ከሰማይ ከወደቀ በኋላ ያለውን እየተመለከትን እንገኛለን ።ሰዎች በበደል እየረከሱ እየባሰባቸው በመሄዳቸው ጌታ ምስጥሩን የተረዱትን ባሪያዎቹን ፣ በኃይል የተሞሉትን ክብሩን የሚገልጡ ነቢያትን ፣ እንደ ወይራ ጠንካራ እንደ መቅረዝ ብርሃን የኾኑትን በዚያ በታላቅ መከራ ዘመን እንዲያገለግሉ ያደርጋል ። እነዚህ ለሰይጣን በተሰጠው ጊዜ በስልጣን የሚመላለሱ ፣ ማንም ልቋቋማቸው የማይቻሉ ጌታ ምስጥሩን ያሳወቃቸው የፍጻሜው አገልጋዮች ናቸው ። ዮሐንስ መጥምቁ አገልግሎቱን ጨርሶ እንደ ሞተ አገልግሎታቸውን ስጨርሱ እነዚህ ባሪዮችም ያርፋሉ፤ ይሞታሉ። ዮሐንስ መጥምቁ የኢየሱስ በሥጋ ወደ ምድር መግባትን መንገድ ጠራጊ አገልጋይ ስኾን ፣ እነዚህ ደግሞም የኢየሱስ ዳግም መምጣት የሚያውጁ የሚሰብኩ የመምጣቱ ፣ የቤተክርስቲያን የመጨረሻ አገልጋዮች ሃይልን የታጠቁ ቅዱሳን ናቸው ።

እነዚህ ቅዱሳን ብርቱዎች የፍጻሜው አገልጋዮች ፣ ሰይጣን ሴትቱን በሚያሳድድበት ጊዜ [1260 ቀን] የሚያገለግሉ ፣እንደ ሙሴ በአሕዛብ ላይ እንደ አምላክ የሚኾኑ ፣በሥልጣን በአፋቸው ቃል መቅሰፍትን የሚያወርዱ በሰይጣን ጥቅት ጊዜ ሰይጣንን የሚያሸብሩ፣ የበላይ የኾኑ ብርቱ ወንድ ልጆች የጌታ ምርጦች ለዚህ አገልግሎት የለያቸው ወንዶች[ብርቱዎች] ልጆች ናቸው ።"ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ።"

ራእይ 11፥3 ። እነዚህ ወይራዎች መቅረዞች የአውሬው ሕዝብ ልቋቋማቸው ያልተቻሉ በአሕዛብ ላይ እንደ አምላክ የኾኑ ባልሥልጣኖች ናቸው ።"እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው፥ ውኃዎችንም ወደ ደም ሊለውጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው።" ራእይ 11፥6 ። እነዚህ የፍጻሜው ዘመን የገባቸው የተረዱ ምስጢርን ከጌታ የተማሩ ትላልቅ መንፈሳዊ ዓይኖች ያሏቸው ፣ ማንም ልቋቋምና ልጎዳቸው የማይቻሉ ፣ በአፋቸው ቃል መቅሰፍትን የሚያመጡ እንደ ኤልያስ ያሉ ብርቱዎች ናቸው ። "ማንምም ሊጐዳቸው ቢወድ እሳት **ከአፋቸው** ይወጣል ጠላቶቻቸውንም ይበላል፤ ማንም ሊጐዳቸው ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል።" ራእይ 11፥5። እነዚህ ከብዙዎቹ ለዚህ ክብር የተለዩ የተዘጋጁ የኖሩ ናቸው ።የዚህን መልእክት ትርጓሜ በቀጣይ ካሜራ ስንመለከት በይበልጥ ይገባናል ። እነዚህ ብርቱዎች በቍጥር ኹለት ብቻ እንዳይደሉና፣ ከክርስቶስ ባሪያዎች ከመቅደሱ ከቤቱ ከሚሰግዱት[ከሴትቱ] የተገኙ ናቸው ። ሰይጣን ይኽንን እንዲታውቅ አይፈልግም ።

እነዚህ ቅዱሳን ካገለገሉ በኋላ የሚሰው ናቸው፤"ምስክራቸውን ከፈጸሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፋቸውማል ይገድላቸውማል።" ራእይ 11፥7 ። እነዚህ የዲያብሎስ ልጆች እስራኤል ዘሥጋ የኾኑቱ፣ ኢየሱስን እንደሰቀሉ ብዙዎችን ነቢያትና አገልጋዮችን እንደገደሉ እነዚህ ቅዱሳንንም ያን ጊዜ ገድለው ይሰቅሏቸዋል። እነዚህን ከመስቀል አውርደው አይቀብሩም በመሞታቸው ብዙ ያሉ ስቃዮችን ስላመጡ ስጦታ እስከመሰጣጠት ይደሰታሉ ራዕ 11፥፥8-10። ይኹን እንጂ ከሦስት ቀን በኋላ ይነሳሉ ፣ ተነስተውም ይነጠቃሉ ።"ከሦስቱ ቀን ተኩልም በኋላ ከእግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው በእግሮቻቸውም ቆሙ፥ ታላቅም ፍርሃት በሚመለከቱት ላይ ወደቀባቸው።" ራእይ 11፥11 ። "በሰማይም፦ ወደዚህ ውጡ የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ሰሙ፤ **ጠላቶቻቸውም እየተመለከቱአቸው ወደ ሰማይ በደመና ወጡ**።" ራእይ 11፥12።

አስተውሉ ከመከራው በኋላ በሥልጣን ያገለገሉ ቅዱሳን በክብር ስነጠቁ ፣ የተደሰቱት አሕዛብ ጠላቶች ይመለከታሉ ። ንጥቀታቸውም በግልጽ ለኹሉም የሚታይ ነው። ንጥቀቱም ከመከራው በኋላ ነው። "በዚያም ሰዓት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፥ ከከተማይቱም አሥረኛው እጅ ወደቀ፥ በመናወጥም ሰባት ሺህ ሰዎች ተገደሉ፥ የቀሩትንም ፍርሃት ያዛቸው፥ ለሰማዩም አምላክ ክብር ሰጡ።" ራእይ 11፥13 ።አሕዛብ ሳይፈልጉ በግድ ንስሐ ሳይገቡ እነሱ ከፍ ከፍ ስሉ ይንበረከካሉ ፤ ለአምላክ ይገዛሉ። እነዚህ እነማን ናቸው አኹንም ግልጽ አልኾነም አይደለ ? የራዕይ መጽሐፍ በመንፈስ ከተረጎምን ጌታ እየመጣ ላለው ነገር ከሚያዘጋጁት አገልጋዮች አንዱ ትኾናለህ። ከምታተሙት በመከራው ውስጥ ኾነው መከራ ከሚያገኛቸው አንዱ ትኾናለህ። ሰይጣን እርሱን

የሚያስጨንቅ አገልግሎት የሚኖራቸውን ቅዱሳንን ማየት አይፈልግም ::መልእክቱ የእናንተ አይደለም ለእስራኤል ዘሥጋ ነው እያስባለ እያስተኛ ይገኛል::ምክንያቱም በቀላሉ ያደቅቃቸዋል:: ጆሮ ያለው ይስማ ::

፨ በእነዚህ መለከቶች የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያ ለዓለም እንደሚሰጥ እየተመለከትን ነበር:: የመጨረሻው የ7ኛው መለከትም "ወዮ" ታ ተብሏል:: ምክንያቱም የዓለምንና ዓለማዊያን የመጨረሻ ነው:: ለበጉ ታምነው የታረዱትና የታተሙት ደግሞ ቅዱሳን ኹሉም በእግዚአብሔር ፊትህ ፍርድ በዓለም ፍጻሜ መጠቅለልና ማለፏ ደስታቸውን ይገልፃሉ :: "ሰባተኛው መልአክ ነፋ፤ በሰማይም፦ የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ:: በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው የተቀመጡ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ፦ ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ **ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን፤ አሕዛብም ተቈጡ፥ ቍጣህም መጣ፥ በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ፥ ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ፥ ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ**::" ራእ 11፥15- 18 ::

በስድስተኛው መለከት እንደተመለከትነው የእግዚአብሔር ታላላቅ ቍጣዎችን የሚያመጡት ለክብር ለመጨረሻው አገልግሎት የተለዩት ቅዱሳን ናቸው :: በመለከቶች እንደተመለከትነው 1

⅓ኛው ብቻ በአንድ መቅሰፍት ከምድር መመታቱ እግዚአብሔር አኹንም ምህረት ለማድረግ ፈቃኛ መኾኑንና የማስጠንቀቂያዎች ዓላማ ንስሐ እንደኾነ የሚያስገነዝቡ ናቸው :: ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ትይንት ለመመልከት አንባቢ በእግዚአብሔር ፊት ልበዎን እንድመረመሩ አበረታታለሁ :: ለማን ነው የሚትቀናው ?ለሰው ወይስ ለእግዚአብሔር ቃል እውነት ? ለራስ ፅሳቤ ዶክትሪን ወይስ ለቃሉ ?

***3ኛው መግለጫ.** .ከምዕራፍ 11፥19 እስከ ምዕራፍ 15፥4 ያለው እስካሁን የተመለከትነው መልእክት በልዩ መንገድ ከላይ ወደ ታች እንደቀረጸ ካሜራ የሚያሳዩ ናቸው ::የፊለፊት እና የጎን ካሜራ የተቀረጸ በማለት በምሳሌ በኹለት መንገድ አይተናል ::አኹን ደግሞ ከላይ ወደ ታች በተቀረጸው ካሜራ እንመለከታለን ::"በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ::" ራእይ 11፥19 :: በዚህ ትይዕንት ከሰማይ ስፍራ ጀምረን የሚኾነውን እንመለከታለን ፤ እግዚአብሔር አኹን ኪዳኑን እንደሚጠብቅ የኪዳኑ ታቦት መታየቱ ያስገነዘበናል :: ይኽ ካሜራ የሚያሳየው ከላይ ከፍ ብሎ የተቀረጸውን ስለኾነ ስለ መጨረሻው ዘመን ተጨማሪ መረዳት በመስጠት ይረዳናል :: አንባቢ ይኽንን ስያነቡ በምዕራፍ አራት ልኾን የሚያስፈልገውን እንጂ የኾነውን ያለፈውን ክስተት እንዳይደለ እያስተዋሉ ፥ እንደ ታርክ እንደ ገድል ሳይኾን ዮሐንስ ራዕዩን ከተመለከተ ጊዜ ጀምሮ የሚፈጸሙ ምስጢራትን እንደሚገልጽ በልበዎ ይዘው ያንብቡ :: እስካሁን የተመለከትነው የማህተሙ ኾነ የመለከቱ ምስጥር አንድ ነገርን በተለያየ አቅጣጫ እንደሚያሳይ የተገነዘባችሁት ይመስለኛል :: ጆሮ ያለ ወደ ከፍታ መምጣቱ አይቀርም :: ከዮሐንስ ጋር እንቀጥል በወፍበረር ፍንጭ ለመስጠት ያህል እናያለን ::

"ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች::እርስዋም ፀንሳ ነበር፥ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች:: … አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ:: ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች::" ራእ 12፥1-6::

አንባቢ ኾይ ይኽ መጽሐፍ ዮሐንስ ራእዩን ከተመለከተ በኋላ የሚፈጸሙ ነገሮችን እንደሚይዝ በመገንዘብ ትንቢታዊ መጽሐፍ መኾኑን አምነው ያንብቡ:: የታየው ታላቅ ምልክት ከዚህ በፊት ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ አዲስ ነገር ነው:: ፀሐይን ተጐናጽፋ ጽድቅን ለብሳ ፤ ያውም ብርሃን የኾነውን የእግዚአብሔር ባሕርይ ይዛ ተሞልታ፤ ደግሞም ጨረቃ የራሱ ብርሃን ሳይኾን ከሌላው በወሰደው የሚያበራውን ረግጣ ማለትም ሃሰተኛውን ብርሃን መላአክ የመሰለውን ረግጣ የታየችው ሴት ፣የፊት መጨማደድ ሳይኖርባት በቅድስና በጉን ለመቀበል የተዘጋጀችው የክርስቶስ እስራኤል ቤተክርስቲያን ናት:: ይህች በ12ቱ ሐዋርያት መሠረት በክርስቶስ እንደራሴዎች

ተውባ በዚያ ጊዜ በመጨረሻው ሰዓት የተገኘች ፣ ዘመኑን ያወቀች፣ የተዘጋጀች ሙሽሪት የበጉ ሚስት ናት። ቤተክርስቲያን በክብሯ በውበቷ በሙላቷ በመገለጧ በምዕራፍ 9 እንደተመለከትነው ሰይጣን ወደ ምድር ይጣላል ። በዚህም ይህቺን ቤተክርስቲያን ያስጨንቃታል ። ሰይጣን ወደ ምድር ወርዶ በሃያላን ሃገራት እና በሐሰተኛው ሃይማኖት ይሠራል ።በዚህም ቤተክርስቲያንን ለመዋጥ ለማጥፋት ይተጋል ። ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው። ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ። ራእ12፥ 3-4።ዲያብሎስ ወደ ምድር ስጣል ከራሱ ጋር ከመላእክት ⅓ኛውን ወደ ምድር እንደሚጥል፣በዚህ ሃይል እንዳለው እንገነዘባለን ።የክርስቶስ ደም ባይሸፍነንና ስሙ ባይኖረን እንዴት ይጫወተብን ይኹን ? ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና ተጠብቀናል።

ሰይጣን ከሰማያዊ ስፍራ ወደ ምድር የተጣለው በቤተክርስቲያን ሙላት መኾኑን እንገነዘባለን ።ያውም ታትመው ሳይጨረሱ መቅሰፍቱ አይውረድ የተባሉት ታትመው ስላለቁ ።ልብ በል 144,000 እየታተሙ ያሉ የእግዚአብሔር እስራኤላውያን እስራኤል ዘነፍስ ናቸው እያልሁ ነው። በሰፊው በቀጣይ ክፍል እንመለከታለን ።

ሰይጣን ወደ ምድር መውረዱ ቤተክርስቲያንን አስጨንቋታል። የፖለቲካ መሪዎች እና ሃሰተኛ መምህራን ይዞ ስለሚሠራ በመቃተት ላይ ትገኛለች ሃይልን ለመታጠቅ ።ጌታም እንዲታደጋት። የቤተክርስቲያን ጭንቀት ከፅንሰት ጋር ተመስሎ መገለጡ ታላቁን መከራ ውስጥ ታምና መቋሟን ያሳየናል ። በዚህ ጭንቀቷም የወለደችው ወንድ ልጅ አሕዛብን ያስጨንቃትን ሚገዛ ፣ ደግሞም ከፍ ብሎ የሚነጥቅ ነው። አስተውሉ ሴቱት ልጁን ከወለደች በኋላ 1260 ቀን ወደ በረሃ ብቻዋን ስትሸሽ፣ልጇ ደግሞ አሕዛብን ገዝቶ ፣በመጨረሻም ወደ ሰማይ ይነጠቃል ። መጽሐፉን በትንቢት መንፈስ አንብቡ። ልጁ ኢየሱስ አይደለም ።ኢየሱስ ገና የሚወለድ አይደለም በዚያን ሰዓት ግና የሚገኝ አይደለም ። እርሱ የቤተክርስቲያን ራስ ነው። የእስራኤል አምላክ ነው።ሴትቱ እስራኤልም ማርያምም አይደለችም ። የትንቢቱን መንፈስ አስተውሉ። ሴትቱ ወሌዳ ትሰደዳለች። ልጇም አሕዛብን ቀጥቅጦ ገዝቶ ይነጠቃል ። ይኽ በምዕራፍ ዘጠኝ የተመለከትነው ማብራሪያ ።ሰይጣን ከሰማይ ስወድቅ፣ መቅደሱ ቤተክርስቲያን እንዳይነካ ስለካ ፣ የቀሩት ከተማው ያልተለኩ የእግዚአብሔር መኖሪያ ቅዱሳን ስረገጡ ፣ በዚያ ሰዓት እንደ ወይራ እንደ መቅረዝ ኾነው ፣ለአሕዛብ ጨንቀት የፈጠሩ የክርስቶስ ሠራውቶች፣ በዲያብሎስ ጥቅት ጊዜ ዲያብሎስን ያስጨነቁ ወንድ ልጆች፣ እንደ አምላክ መቅሰፍት እያመጡ ያሸበሩ አሕይዛብን የረገጡ ፣በመጨረሻም አገልግሎታቸውን ጨርሰው ወደ ሰማይ የሚነጠቁ ናቸው ፤ የሴትቱ ልጅ በዚያን ሰዓት የሚገኙት ። ጆሮ ያለው ይስማ።

"በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፥ አልቻላቸውምም፥ ከዚያም ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም።ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።" ራእ 12፥ 7-9።

ሰይጣን ወደ ምድር መጣል መውደቅ በተለያየ ካሜራ እንደተቀረጸ ምስል እየተመለከትን እንገኛለን ።ነገርግን ሰይጣን ወደ ምድር የሚጣለው ለዘላለምም በሰማይ ስፍራ የማይገኘው እንዴት ነው የሚለውን አልተመለከትንም ። ኢሳይያስ ተረድቶ ስለ ሰይጣን መውደቅ፣ በዚህ ስፍራ ዳግም ስለአመገኘት እንዲህ ብሎ ተናግሮ ነበር ፦ "አንተ የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ! አሕዛብንም ያዋረድህ አንተ ሆይ፥ እንዴት እስከ ምድር ድረስ ተቈረጥህ!አንተን በልብህ፦ ወደ ሰምይ ዐርጋለሁ፥ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፥ በሰሜንም ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ከዳመናዎች ከፍታ በላይ ዐርጋለሁ፥ በልዑልም እመሰላለሁ አልህ። ነገር ግን ወደ ሲኦል ወደ ጕድጓዱም ጥልቅ **ትወርዳለህ**።የሚያዩህ ይመለከቱሃልና፦ በውኑ ምድርን ያንቀጠቀጠ፥ መንግሥታትንም ያናወጠ፥ ዓለሙን ሁሉ ባድማ ያደረገ፥ ከተሞችንም ያፈረሰ፥ ምርከኞቹንም ወደ ቤታቸው ያልሰደደ ሰው ይህ ነውን? ብለው ያስተውሉሃል። ኢሳ 14፥ 12-17። ሐዋርያው ጳውሎስ ውጊያ እነዚህ በሰማይ ካሉት ሃይላት ጋር እንደኾነ መስክሮ ነበር፤ኤፌ 6፥12፤ መንፈሳዊ ነገር ተረድቶ። እነዚህ በሰማይ ያሉት ሃይላት የእግዚአብሔርን ሕዝብና መላእክቱን የሚያስጨንቁ የሚዋጉ ናቸው ። ወደ ዳንኤል መልእክት ይዞ የሚመጣው መልእክተኛ መላአክ፣ አየር ላይ በሰማይ እየተዋጉ በማቆየት የእግዚአብሔር መልእክት በጊዜው

እንዳይደርስ ያደናቅፉ፣ያዘገዩ ፣ በምድር ኾነው እየጸለዩ ያሉትን ቅዱሳንን የሚያስጨንቁ ናቸው ።ዳን 10። ወደ ምድር ስጣሉ ያላቸው ጊዜ 3 ዓመት ከ6 ወር ብቻ ነው።

አስተውሉ ሰይጣን ገና ወደ ምድር እንደሚጣል፣ የሰማይ መኖሪያ ለአንዴና ለዘላለም ስለቅ፣ በእርሱ መውረድ ሴትቱ ስትሰደድ ይኽ ገና የሚኾን ነው።ይህ ታዲያ የኾነ ያለፈ ታርክ ነው? ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ፤አይደለም ። ከሃሰተኛ አስተማሪዎች ተጠበቁ። ለራሳቸውም አይገቡም የሚገቡትን አይለቁም ፤ተለይዩ ። አልያ ከሚጠፉት መሃል ትኾናለህ።

“ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።” ራእይ 12፥13 ። ሴቱት ታትማ ተለይታ ተከልላ ፣ በጽድቅ ተሞላታ ሙላቷን ስትፈጽም ። እየመጣ ያለውን በመረዳት ብዙ በመቃተት ብርቱ ልጆቿን የመጨረሻው ዘመን አገልጋዮችን ስታዘጋጅ ፣ ሰይጣን ከሰማይ ወደ ምድር ተጣለ። ሴቱትንም በራሱ ግብረአበሮቹ የፖለቲካ ሃይላትና ሃሰተኛ አስተማሪዎች ተጠቅሞ አሳደዳት ።ንፅህት ቅድስት ሙሽሪት ኾና የተዘጋጀጅ ናትና ፣ጌታ ለዚህ ዓላማ ይኾን ዘንድ ወዳዘጋጀው ስፍራ ትሸሻላችሁ ። መከራው አያገኛትም ።1260 ቀን በሰይጣን ጥቅት ጊዜም አትጎዳም። “ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።”ራእይ 12፥13 ።ሰይጣን እናንተ ይኽንን እንዲታውቅ አይፈልግም ።ምክንያቱም እርሱ የሚያስጨንቁ ትውልድ ፣ልጆች የሚታዘጋጁ እናንተ ናችሁ ። ሴቱት የሥጋ እስራኤል ናት ወይም ማርያም ናት እያለ ብዙዎችን አስተኝቷል። ሃይልን ለመልበስ ለመምጣቱ መንገድ ለመጥረግ ተዘጋጅ።ጆሮ ያለው ይስማ። ሰይጣን አስቀድመህ ከመከራው በፊት ስለሚትነጠቁ በማለት ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ ሃይልን እንዳትለብስ ፣ እናንተ ከመከራው በፊት ትነጠቃላችሁ እያለ በመከራው ለመንጠቅ ብዙዎችን አስተኝቷል። ጆሮ ያለው ይስማ።

" ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን፥ ዘመናትም፥ የዘመንም እኵሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሀ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት።እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በስተ ኋላዋ አፈሰሰ። ምድሪቱም ሴቲቱን ረዳቻት፥ ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው።" ራእ 12፥14-16 ። ሴቱት የተዘጋጀችው ቤተክርስቲያን ለዚህ ጊዜ ይኾን ዘንድ ጌታ ወዳዘጋጀው ስፍራ ፣በረሃ መንፈሳዊ ስፍራ ትሸሻለች። በዚህም ታላቁ መከራ ሳያገኛት ታሳልፋለች። ከምድር ተነጥቃ ሳይኾን በምድር እያለች ። ሴትቱ አስተማማኝ ታላላቅ ንስር ክንፍ አላት፤ በመለኮታዊ ሃይል የተሞላች ማንም ልነካትና ልደፍራት የማትቻል ናት። ዘንዶው ልሞክራት ብወድም የራሱን ግብረአበሮቹ ወንዞችን ብያስነሳባትም ተፈጥሮ ራሷ በተለያየ ምድራዊ መቅሰፍት በማምጣት እነርሱን አሕዛብን ታደቅቃለች። ፍጥረት ራሱ ከጎኗ ኾኖ ውኃ እየተመረዘ በተለያየ ተፈጥሯዊ አደጋ አሕዛብ ይመታሉ።

ሴቱት ተለክተው የተለዩትን የእግዚአብሔር መቅደስ ፣ ታትመው የተለዩትን የእግዚአብሔር እስራኤል ሰይጣን በመከራው ውስጥም አንዳች ነገር ማድረግ አይችልም ።ሰይጣን ይኽንን እንዲታውቁ አይፈልግም ።ምክንያቱም የሰይጣን የመጥፋቱ አገልጋይ ትኾናለህ። በተለያየ እሳቤ ጠፍሮ ይዞ ፤ በተለያየ ዶክትሪን ስያነትርክ ለምድራዊ ተቋም ስትቀና ጊዜውን ይበላል ።ይኽንን አውቂ ስለዚህ ስለመምጣቱ ሃይልን ለመልበስ እሳት ነበልባል ለመኾን እንዲትጸልይ ፣ አይፈልግም ። በዚህ በምድራዊ ሃብት በትበለጽጋለህ ወንጌል በሃሰተኛ አስተማሪዎች መርዝ መንገድ ጠራጊዎች ልብህን በምድር ለማስቀረት ይሠራል ።አንተ ግን ጆሮ ካለ ስማ አሰማ። በመከራው ውስጥ መከራው የማያገኝህ ሙሽሪት ለመኾን ተዘጋጅ። ይኽንን ለመስማት እድል ማግኘት የጌታ ጥሪ ነው። እድለኛ ስለኾንክም ነው ።ለኢየሱስ መምጣት መንገድ ጠራጊ ጸሃይ ለበስ ኾነ ለመኖር የቅድስና የሃይል ሕይወት ለመለማመድ ተዘጋጅ። ጌታ ብዙዎችን ይኽ ከመከራ እንዳያገኝ እያዘጋጀ እያተመ ይገኛል። ከምጠፉት እንዳትሆን ጆሮ ካለህ ስማ ።ከሃሰተኛ ነቢያት ሰላም ይኾናል እድገት ይኾናል እያሉ ከሚያስተኙ ወንበዶች ተለይ።

ዘንዶው ፀሐይ ለበስ የኾነችውን ልይዛት አልቻለም ። በዚህም የእርሷ ዘር የኾኑትን ከእርሷ የተገኙትን ያልተሠወሩትን የቀሩትን ነገርግን ሃይልን ታጥቀው ለፍጻሜው ለማገልገል የተዘጋጁትን በነፍሳቸው ተወራርደው ያሉትን ለመዋጋት ዘወር ይላል። አያችሁ! ከመከራው ለመጠበቅ ከመከራው በፊት ትነጠቃላችኹ ብሎ ማስተማር ማሰብ ግዴታ እንዳይደለ? ይኽ አስተምህሮ በብልሃት የተፈጠረ ለሰው አዕምሮ ደስታን የሚሰጥ ነው።ነገርግን ከእግዚአብሔር አይደለም ።የእግዚአብሔር አይደለም ።ዋናው ዓላማው ከሴቷም ከዘሯ ከልጇም መሃል እንዳትኾኑ በማድረግ ማደንዘዝ ነው። ሴቱት ወደ ሰማይ ሳትነጠቅ በምድር ኾና ልክ እንደ ኤልያስ

ተጠብቃ ተሰውራ ያንን ታላቁን መከራ 3ዓመት ከ6ወር ታሳልፋለች ። የእርሷ ዘር ግን ለውጊያ ለጦርነት ይዘጋጃል ።"ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤" ራእይ 12፥17 ። እነዚህ የፍጻሜው ዘመን አገልጋዮች የሴቷ ዘር የኾኑ በዲያብሎስ ጥቅት ጊዜ መልሰው የሚገዙ ፣መቅሰፍትን የሚያመጡ በነፍሳቸው ተወራርደው የሚያገለግሉ እልፍ የኾኑ ናቸው ። ሰይጣን ይኽንን እንዲታውቅ አይፈልግም ።ምክንያቱም አንተ ሰይጣንን ለማደቀቅ መንግስቱን ለማሸበር ለማስጨነቅ ጌታ የጠራህ ነህ። ጥሪውን ተቀብለህ እንዲትመጣና እንድታዘጋጅ አይፈልግም ። ከሚጠፉት ነህ ወይስ ከሚድኑት ? ጆሮ ያለው ይስማ። ሰይጣንን ከእነዚህ ብርቱዎች በአሕዛብ ላይ እንደ አምላክ በሙሴና በኤልያስ መንፈስ ከሚያገለግሉ ጋር የሚዋጋው፣በሃይላን ሃገራት ላይ ኾኖ ነው።"በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ።" ራእይ 12፥18 ።

ከእነዚህ ቅዱሳን ጋር ለመዋጋት ባሕር ዳር [ሃያላን ሃገራት አጠገብ] የቆመው ዘንዶው በኹለት መንገድ ውጊያው ሃይሉን አሟጦ የመጨረሻ ጊዜው ስለኾነ፣ ቤተክርስቲያንም ሳትነካ ስለተረፈች በብስጭት እንደ ቆሰለ ውሻ ለመናከስ ይመጣል ።1ኛው መንገድ.ከባሕር የወጣ አውሬ መጠቀም ነው;ለሃያላን ሃገራት ሌላውን ማስገደድ በሚችሉት ጋር በግልጽ መሥራት ነው። "አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ።" ራእይ 13፥1። ብዙዎችን ይማርካሉ። የእግዚአብሔር ከተማ የነበሩ ሃይልን ያልታጠቁ ቅዱሳን ይጨፈለቃሉ። 2ኛው መንገድ. ከምድር የወጣ አውሬ መጠቀም ነው; "ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር።" ራእይ 13፥11 ። ከምድር የወጣው አውሬ ሃሰተኛ ነቢያት ስኾኑ የማይጎዱ የበግ ቀንድ ያላቸው ይመስላሉ ፣ ከአፋቸው የሚወጣው ግን ኑፋቄና መረን የኾነ እንደ ዘንዶ ያለ ነው። ለሃሰተኛ አስተማሪዎች ከባሕር የወጣው የመጀመሪያው አውሬ አቅሙ ነው። ብዙ ታላላቅ ምልክቶችን የሚያደርግ ስኾን ምልክት ፈላጊ ቅዠታም "አማኝ" ኹሉ ይጠፋል። ቊ.13። እነዚህ ምልክት ፈላጊ ልባቸው ያልሠሩትን ለማጨድ ገንዘብ አካውቷቸው ላይ ገባ ስባል የሚዘልሉ ይጠፋሉ፤ የሚሰብኩት ለሰይጣን መንገድ ጠራጊዎች ናቸው ።ጆሮ ያለው ይስማ። ይኽ ሃሰተኛው አስተማሪ የራሱ ተከታዮችን ለመለየት በሰውነታቸው ምልክት ማህተም ያደርጋ፤666 ።ሌላው እንዳይገዛ እንዳይጠቀም በማድረግ በማስጨነቅ ለመማረክ ።ጆሮ ያለው ይስማ።

በ3ዓመት ከ6ወር ሰይጣን ብዙዎችን እያንጨነቀ ሃይልን ያልታጠቁትን ስማርክ ፣ ስገዛ፣ የክርስቶስ ማህበረሰብ የኾነች ቤተክርስቲያን በተሸሸገችው ስፍራ በምድር ኾና፣ ከሰይጣን አቅምና እይታ በተሰወረችው ቦታ ኾኖ ፣ በጉ ስላተማቸው ስለተለዩ፣ በጽድቅ ክርስቶስን ለብሰው ፣ክብር ተሞልተው ፣ እነርሱ ሌላ ሕይወት ውስጥ ናቸው፤በምስጋና በአምልኮ ውስጥ ናቸው፤ከበጉ ጋር ናቸው።" አየሁም፥ እነሆም፥ በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር፥ ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም በግምባራቸው የተጻፈላቸው መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ።እንደ ብዙ ውኃም ድምፅና እንደ ታላቅ ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ፥ ደርዳሪዎችም በገና እንደሚደረድሩ ያለ ድምፅ ሰማሁ። በዙፋኑም ፊት በአራቱም እንስሶችና በሽማግሌዎቹ ፊት አዲስ ቅኔ ዘመሩ፤ ከምድርም ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራት ሺህ በቀር ያን ቅኔ ሊማር ለማንም አልተቻለውም።ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው፥ ድንግሎች ናቸውና። በጉ ወደሚሄድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው። ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኵራት እንዲሆኑ ከሰዎች የተዋጁ እነዚህ ናቸው።በአፋቸውም ውሸት አልተገኘም፤ ነውር የለባቸውም።" ራእ 14፥1- 5።

በዚህ ሰይጣን ስያስጨንቅ፣ በዚህ ቤተክርስቲያን ተጠብቃ ስታመሰግን፣ እንደገና እድል ለተሰጣቸው ወንጌልን እንዲሰሙ ጌታ በወንዶች ብርቱዎች ከዘሯ በቀሩት እንዲሰበክ ያሳስባል፥"በምድርም ለሚኖሩ ለሕዝብም ለነገድም ለቋንቋም ለወገንም ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ፤" ራእይ 14፥6 ። **አንደኛው ሰባኪ ፣ንስሐ እንዲገቡና ለእግዚአብሔር እንዲገዙ ያውጃል** ። "በታላቅ ድምፅም፦ የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት፤ ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም የውኃንም ምንጮች ለሠራው ስገዱለት አለ።" ራእይ 14፥7 ። **ሌላኛው ሰባኪ የነገሰችው ባቢሎን እንደሚትወድቅ ያውጃል።** "ሌላም ሁለተኛ መልአክ፦ አሕዛብን ሁሉ የዝሙትዋን ቍጣ ወይን ጠጅ ያጠጣች ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች እያለ ተከተለው።" ራእይ 14፥8 ። አስተውሉ እነዚህ የመጨረሻው ፍጻሜ ላይ ከሰይጣን መውደቅ ተከትሎ የሚኾኑ ናቸው ። **ሌላኛው ሦስተኛው ሰባኪ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል** ።የአውሬ ቊጥር እንዳይቀበሉ ፣ የተቀበሉት እረፍት እንደማይኖራቸው ፣ ቅዱሳን የኾኑት በመከራው በትዕግሥት የሚያልፉት ድል እንደሚነሱ ፥ ""ሦስተኛም መልአክ ተከተላቸው፥ በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያለ፦ ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግምባሩም

ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር፥"ራእይ 14፥9 "ራእይ 14፥8፤9-12:: አንባቢ ኾይ ጨኸተ ይሰማል:: በዚህ ስቃይ ውስጥ ከምማቁቅቱ እንዳትሆን ልክ እንዴ ሴቱት ሙሽሪት ቤተክርስቲያን ወይም እንደ ዘሯ ቅሬታዋ በስልጣን በአውሬው ላይ ከሚመላለሱት መሃል እንድትሆን እየነገርኩ ነው::የእግዚአብሔር ጥሪ ለኹሉ ነውና:: አውሬው ዲያቢሎስ ከምማርካቸው ከሚያስታቸው እንዳትኾን ከተያዝክበት ወጥመድ እንድትወጣ እያሳሰብኩ ነው::ጆሮ ካለህ አምልጥ:: ፈረሳዊ ግብዝ ከኾንክ ትጠፋለህ ፣ ዛሬ የተተማመንክባት እምነት ተቋም ሕዝብ መንጋ ማምለጫ አይኾንም:: ይኸንን እውነት ከተቀበልክ በሰማዩ አምላክ ፊት ኹን :: ተዘጋጅ የቅድስና ሕይወት ተለማመድ :: በእውቀት በጥበብ በመንፈሳዊ ነገር ዓይኖች ትላልቅ እስከሚኾኑ ድረስ በልግስና የሚሰጠውን ጌታ ተማጸን:: ጆሮ ያለው ይስማ::

እነዚህ ብርቱዎች የመጨረሻው ማስጠንቀቂያ ከሰጡ በኋላ ፣ አስቀድሞ ኢየሱስ እንደገለጠው ተቀላቅለው ያሉት ስንዴውና እንክርዳዱ ስለዩ፣ ወቅቱ ስደርስ ከዓለም አሰናብታለሁ፤ ፍርድን እሰጣለሁ ፤ አጭዳለሁ ደግሞም በእሳት አቃጥላለሁ እንዳለው ያደርጋል :: በመላእክቱም ያሳጭዳል ::ምድር ፍጻሜዋን ታገኛለች:: ተመሳስሎ ከቅዱሳን ጋር የኖሩትም በግልጽ የአውሬውን ቍጥር ተቀብለው ስያመልኩ፣ ታምነው ጨክነው የቆሙት ስሰው ፣ ኹሉም በግልጽ ጻድቁም ኃጢኡም ስለይ፣ ኢየሱስ ምድር እንዲታጨድ ይፈቅዳል ::ራእይ 14፥[14] አየሁም፥ እነሆም ነጭ ደመና፥ በደመናውም ላይ የሰውን ልጅ የሚመስል ተቀምጦአል፥ በራሱም ላይ የወርቅ አክሊል በእጁም ስለታም ማጭድ ነበረው:: ... [16] በደመናውም ላይ የተቀመጠው ማጭዱን ወደ ምድር ጣለው ምድርም ታጨደች:: ይህች ምድርም ተጠቅልላ ታልፋለች :: የትኛውም አስተማሪ ያከማቸኸው ልሸሽግህ የማይቻልበት ጊዜ ይመጣል ፤ ይህች ምድር ፍርዷን ትቀበላላችሁ ::ጆሮ ያለው ይስማ ::ይኸንን እንዲታነቡ እድል ያገኘህ አንተ እድለኛ ነህ:: ነፍስህን እንዲታተርፍ ከተያዝክበት ወጥመድ ፣ ከተጫነብህ ቀንበር ተላቀ ወደ እግዚአብሔር እንዲትጮህ አሳስባለሁ ::ጆሮ ያለው ይስማ:: በረከት ሰላም ብልጽግና በዚህ ምድር ላይ ይኾናል እያልኩ አላባብልም::በግልጽ በግልጥ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቃልን እናገራለሁ :: በእግዚአብሔር ፍርድ በመጨረሻው በተገለጠው ፊትህ ቅዱሳን በደስታ ይዘምራሉ ፦"ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው፤ የአሕዛብ ንጉሥ ሆይ፥ መንገድህ ጻድቅና እውነተኛ ነው፤ ጌታ ሆይ፥ የማይፈራህና ስምህን የማያከብር ማን ነው? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና፥ የጽድቅም ሥራህ ስለ ተገለጠ አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ በፊትህም ይሰግዳሉ እያሉ የእግዚአብሔርን ባሪያ የሙሴን ቅኔና የበጉን ቅኔ ይዘምራሉ::" ራእይ 15፥3-4::አሜን ሃሌ ሉያ::

***4ኛው መግለጫ**. .በዚህኛው ካሜራ የሚገለጸው መጀመሪያ በጨረፍታ በሌሎች ካሜራዎች የቀሩት ምስሎች ናቸው ::" ከምዕራፍ 15፥5 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 16" :: በመጨረሻው ዘመን ሰይጣንም በግልጽ ስሰራ፣በራሱ ሕብረተሰብ ስያሰራ፣ በጉ በቀሩት ዘሮች ስያናውጡ፣ መላእክቱም ስሳተፉ በሰፊው አይተናል ::በዚህ በመጨረሻ ፍርድ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያጭድ እንደሚያቃጥል ተገንዝበናል ::በዚህ የምንመለከተው የእግዚአብሔር ቍጣ ማጭድ በምድር ላይ የተገለጠውን ዝርዝር ሃሳቡን ነው:: "ከዚህ በኋላ አየሁ፥ የምስክርም ድንኳን መቅደስ በሰማይ ተከፈተ፥ሰባቱንም መቅሠፍት የያዙ ሰባቱ መላእክት ከመቅደሱ ወጡ፤ ከተልባ እግርም የተሠራ ጥሩ የጌጥ ልብስ ለበሱ ደረታቸውንም በወርቅ መታጠቂያ ታጠቁ::" ራእ 15 ፥5-6፣8:: የእግዚአብሔር መላእክት ከመቅደሱ የወጡት ለማዳን ሳይኾን ለፍርድ ለፍትህ ነው፤ቍጣውን እስከሚጨርሱ ድረስ ተመልሰው አልገቡም፤ቍ.8:: በዚህ ክፍል የምናየው በመጨረሻም ዘመን በእግዚአብሔር መላእክት ስለሚገለጡ ቍጣ፤ ምድር ከእግዚአብሔር ስለምትቀበለው ፍርድ ነው:: በሰይጣን ጥቅት ዘመን ለሰይጣን ማረፍያ መደሰቻ ሳይኾን፣ መጨነቅያ መጥፍያ ነው::በዚህ በብርቱዎች ሃይልን በታጠቁ ስያስቃያቸው በዚህ ደግሞ በቅዱሳን መላእክት ወደ ምድር ጥሎም ማሰቃየቱን ማሳደዱን ይቀጥላል ::መላእክቱ "ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ **መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ**::" ራእይ 12፥9 :: ቁጣዎችን በወፍ በረር እንመለከታለን ፦

ፙ 1ኛው ቍጣ; ምድር ተመታች ፤"ፊተኛውም ሄዶ ጽዋውን በምድር ውስጥ አፈሰሰ፤ የአውሬውም ምልክት ባለባቸው ለምስሉም በሚሰግዱ ሰዎች ክፉኛ የሚነዘንዝ ቍስል ሆነባቸው::" ራእይ 16፥2 :: በዚህ ፍርድ የሚሞቱት የአውሬውን ምልክት የተቀበሉ የካዱ ናቸው ::ብልጽግና ይኾናሉ ስሉ ስቃይ ይኾናል:: ይኽ ፍርድ ስለኾነ ቀጥታ የሰዎችን ሕይወት የሚጎዳ ነው::ከላይ እንዳየነው እንደ ማስጠንቀቂያ መለከቶች ተፈጥሮን ብቻ አይመታም::ደግሞም ⅓ኛውን ብቻ የሚመታ አይደለም :: በ3ዓመት 6ወር የሚገልጽ ፍርድ ነው::

፨ 2ኛው ቍጣ; ባሕር ተመታች፤"ሁለተኛውም ጽዋውን በባሕር ውስጥ አፈሰሰ፤ እንደ ሞተም ሰው ደም ሆነ፥ በባሕርም ከሚኖሩት ሕይወት ያለበት ነፍስ ሁሉ ሞተ።"ራእይ 16፥3 ። ባሕርይ መዝናኛና መንፈስ ማሪክያ ሳትኾን የሚትገማ ትኾናለች።

፨ 3ኛው ቍጣ;ወንዞች ተመቱ፤ "ሦስተኛውም ጽዋውን በወንዞችና በውኃ ምንጮች ውስጥ አፈሰሰ፤ እነርሱም ደም ሆኑ። ... የቅዱሳንና የነቢያትን ደም ስላፈሰሱ ደምን ደግሞ አጠጥተሃቸዋል፥ የሚገባቸው ነውና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።"ራእ 16፥4-6። ጌታ ፍርዱን በመግለጡ በመጀመሪያው ካሜራ የተመለከትናቸው ፍርድን ይጠይቁ የነበሩ ቅዱሳን ምላሽ በማግኘታቸው ደስታቸውን በምስጋና ይገልፃሉ ።የሞቱት የተሰዉት ቅዱሳን ስለ ደማቸው ፍርድን ይማጸናሉ ። "ከመሰዊያውም፦ አዎን፥ ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ ናቸው ብሎ ሲናገር ሰማሁ።" ራእይ 16፥7 ።

፨ 4ኛው ቍጣ; ፀሐይ ተመታች፤"አራተኛውም ጽዋውን በፀሐይ ላይ አፈሰሰ፤ ሰዎችንም በእሳት ልታቃጥል ተሰጣት።" ራእይ 16፥8 ።በዚህ ፍርድ ላይ ፀሐይ ጨለማ ሳትኾን የሚትኾነው ወይም ⅓ኛ ብቻ ሳይኾን የሚጠቃው እንደ ማስጠንቀቂያዎቹ፤ ሙሉ በሙሉ ፀሐይ ለሕይወት አስፈሪ በመኾን ታቃጥላለች ፤ ቤት ልከለክል አይችልም በሙቀት ትገድላለች።

፨ 5ኛው ቍጣ;ሃያሏ ከተማ ባቢሎን ትመታለች፤; "አምስተኛውም ጽዋውን በአውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ፤ መንግሥቱም ጨለማ ሆነች ከስቃይም የተነሳ መላሶቻቸውን ያኙኩ ነበር፥"ራእይ 16፥10 ። ከደረሰባቸው ስቃይ የተነሳ ጥርሳቸውን ያኙካሉ ማለትም ንስሐ አልገቡም ብቻል ምላሽ ለመስጠት ይዘጋጃሉ ። "ከስቃያቸውና ከቍስላቸውም የተነሳ የሰማይን አምላክ ተሳደቡ፥ ከስራቸውም ንስሐ አልገቡም።" ራእይ 16፥11

፨ 6ኛው ቍጣ የሚያርፈው በሰይጣን አገልጋዮች ነገስታት ሃያላን ሃገራት የዘንዶው ሥራ አስፈጻሚዎች ላይ ነው"ስድስተኛውም ጽዋውን በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ፤ ከፀሐይም መውጫ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲሰናዳላቸው ውኃው ደረቀ።" ራእይ 16፥12። እነዚህ የሃይል ምንጭ የኾኑ የፖለቲካ ሃያላን ሃገራት ስመቱ፣ ሰይጣን በግልጽ ጦርነት ለማድረግ ሃይልን ለመሰብሰብ ሌሎችን ሃገራት ነገስታትንም ይዞ ይወጣል፤፣"ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጕንቸሮች የሚመስሉ ሦስት ርኵሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤" ራእይ 16፥13 ። የርኩሳን መናፍስት ራሳ የኾኑና ቀንደቹ ሥራው አስፈፃሚ የፖለቲካ ሃያል ሃገራት በተደጋጋሚ ስለተመቱ፣ የመጨረሻውን ሃይሉን አሟጦ የመጨረሻውን ጦርነት ለማድረግ ወደ ዓለም ነገስታት ይወጣል ። "**ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና**፥ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲያስከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ።" ራእይ 16፥14 ። አንድ ላይ አንድ ኾነው የዓለም ነገስታት በጉን ለመዋጋት ይወጣሉ።"በዕብራይስጥም አርማጌዶን ወደሚባል ስፍራ አስከተቱአቸው።"ራእይ 16፥16 ።

ስለዚህም አንባቢ ያስተውል ፣"እነሆ፥ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው።" ራእይ 16፥15 ።

፨ በ7ኛው ቍጣ; የመጨረሻ ፍርድ በዓለም ላይ፣"ሰባተኛውም ጽዋውን በአየር ውስጥ አፈሰሰ፤ ከመቅደሱም ውስጥ፦ ተፈጽሞአል የሚል ታላቅ ድምጽ ከዙፋኑ ወጣ።"... ታላቂቱም ከተማ በሦስት ተከፋፈለች፥ የአሕዛብም ከተማዎች ወደቁ። ታላቂቱም ባቢሎን የብርቱ ቍጣው ወይን ጠጅ የሞላበትን ጽዋ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች። ደሴቶችም ሁሉ ሸሹ ተራራዎችም አልተገኙም። በሚዛንም አንድ ታላንት የሚያህል ታላቅ በረዶ በሰዎች ላይ ከሰማይ ወረደባቸው፤ ሰዎቹም ከበረዶው መቅሰፍት የተነሳ እግዚአብሔርን ተሳደቡ፥ መቅሰፍቱ እጅግ ታላቅ ነውና።" ራእ 16፥19-21 ። በዚህ ፍርድ ሰይጣን በጉን ለመውጋት የሰበሰባቸው እንዳልነበረ ስኾኑ ፣ ታላቅ የበረዶ ግግር ዝናብ ምድርን እንዳልነበረች ያደርጋል ።በዚህ 7ቱ ፍርዶች ይፈጸማሉ ።

ከላይ ወደታች በተቀረጸ ካሜራ ብለን በምሳሌ በተመለከትነው በቍ.3 እይታ ላይ ዮሐንስ በሰይጣን መውደቅ ፣በቤተክርስቲያን ሙላት ፍጹምነት ፣በብርቱዎች መወለድ እንደጀመረ አይተናል። ራእ12። እነዚህም ክስተቶች የመጨረሻው መጨረሻ ሰዓት የሚኾኑ ለዓለም ፍጻሜ 3ዓመት ከ6ወር ስቀር የሚኾኑ እንደኾነ ተገንዝበናል ።ይኸኛው ቍጣም በዚህ ጊዜ እንደሚጀመር የእግዚአብሔር ፍርድ ከቅዱሳን መታተም በኋላ እንደሚጀመር ፣

የምድር ማጭድ የተላከው ቅዱሳን የታመኑቱ ከተለዩ በኂላ እንደኾነ ከቃሉ መገንዘብ ይኖርብናል ። የታላቁ የምጥ ጣዕር ጅማሮ የሚኾኑ መከራና ስቃይ ማስጠንቀቂያ ፣ከፍጻሜ ቊጣ ጋር ደባልቀን መረዳት የለብንም ።

***5ኛው መግለጫ**. እስካሁን የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ቊጣ ፣ የታተሙ ቅዱሳን የሚያልፉበት ሁኔታ የሰይጣን መውደቅና መደፋፈቅ ተመልክተናል ። በዚህኛው እይታ ሰፊ ማብራሪያ የሚሰጠው የሰይጣን ሃሳብ አስፈፃሚ ከተማ ስለኾነች ስለ ሃያሏ ሃገር ነው። ስለምደርስባት ፍርድና ያቺን ከተማ ሃገር እንዲናስተውል መግለጫ ይሰጣል ። ከምዕራፍ 17 እስከ 19፥10 ድረስ በሰፊው ያትታል ። "ሰባቱንም ጽዋዎች ከያዙ ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፦ ና በብዙም ውኃዎች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ፤ … በመንፈስም ወደ በረሀ ወሰደኝ፤ የስድብም ስሞች በሞሉበት፥ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ። …    ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ ታላቂቱ ከተማ ናት።" ራእ 17። ይህቺ የሚትሠራው በአስማት ።ብዙዎችን ታስታለች።ትማርካለች። ይህቺ ከተማ በሴቷ ጋለሞታይቱ አስማት የሚትሠራ በጉን ለመዋጋት፣ ሌሎች ነገስታትን አሰባስባ ብትሰለፍም አርማጌዶን ፤ በእግዚአብሔር በሰባቱ ቊጣዎች እንደተመለከትን በጉ ያሸንፋል 17፥14። ከዚያን በመሸነፋቸው እርስ በእርስ ጦርነት ያደርጋሉ ። ያሸንፏታልም። ከዚያም ያቺ ከተማ የብዙዎችን ትኩረት የወሰደችው ትወድቃለች ።ራእ 18፥2። የብዙዎች የቅዱሳን ደም ስለፈሰሰባት በዚህች ከተማ፤ ቅዱሳን በመውደቋ ደስታቸውን ይገልፃሉ ።ራእ 19፥1-10። ከዚህ እርኩሰት ከተማ ውድቀት በኂላ ፣አምላካችን በክብር ስለነገሰ ምድር የመጨረሻውን ፍርዷን ስላገኘች፣ የደስታ የግንኙነት ታላቅ እራት ለሙሽሪት ቤተክርስቲያን ይደረጋል ፣"**ከዚህ በኂላ በሰማይ፦ ሃሌ ሉያ፤ በዝሙትዋ ምድርን ያጠፋችይቱን ታላቂቱን ጋለሞታ ስለ ፈረደባት፥ የባሪያዎቹንም ደም ከእጅዋ ስለ ተበቀለ፥ ፍርዶቹ እውነትና ጽድቅ ናቸውና ማዳንና ክብር ኃይልም የአምላካችን ነው ብሎ ሲናገር እንደ ብዙ ሕዝብ ታላቅ ድምፅ ያለ ድምፅን ሰማሁ።… የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ**።" ራእ 19፥1-7 ። እንግዲህ ይህ ሰርግ ከመከራው ከመጨረሻው ፍርድ በኂላ ከ1260 ቀን ስቃይ መከራ በኂላ ለቅዱሳን እንደሚደረግ ይረዷል። አስተውሉ ።የሰይጣንን ሃሳብ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከፍ ያለውን ነገር ኹሉን  እናፈራለን ።

***6ኛው መግለጫ**. *ከ3ኛው  እስከ 5ኛው እይታ ያሉቱ የሚያሳዩት ትኩረት ያደረጉት ታላቁን መከራ ጊዜ ስኾን የ1ኛውና የ2ኛው ያለው ግን ዮሐንስ ራዕዩን  ካየበት ጊዜ አንስቶ ያለው ክስተት የሚያሳይ ነው፤ትኩረታቸውን የተለያየ ብኾንም ይኾን ያለውን ዮሐንስ ራእይ ከተመለከተበት ጊዜ አንስቶ ያለውን የሚገልጹ መኾናቸውን መገንዘብ እንችላለን ። በዚህኛው እይታ ጠቅለል ያለ አጠቃላይ እይታ ስለ መጨረሻው ዘመን እንደሚሰጥ የምንመለከት ይኾናል፦

⁘  ሰማይ ተከፍቶ ዮሐንስ አየሁ ስል አንደኛው እይታ ጨርሶ፣ በልዩ መንገድ ሌላ ማየት እንደጀመረ እናስተውላለን ፣ደግሞም ከምስጋናዎች ከማብቅያዎች በኂላ መጀመሩ ዮሐንስ በሚያይበት እንድናይ ይረዳናል ፣"ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፥ እነሆም አምባላይ ፈረስ፥ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፥ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም።"  ራእይ 19፥11። በዚህ ሰማይ መከፈት ከአጠቃላይ መግለጫ የሚመለከተው አንደኛው ስለ፣ ክርስቶስ ነው።ስለ ማንነቱ ነው። እስካሁንም ወደፊትም ድል አድራጊ ነውና በነጭ ፈረስ ተቀምጧል ፤ በሕዛብ ላይ ይፈርዳል ፤ ከእይታውም የተሰውረ ነገር የለም። ኹሉንም ያውቃል ። በማንነቱም ከአብ ጋር እኩል የኾነ መለኮት ነው፥"በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት፦ የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ስም አለው።"ራእይ 19፥16 ። በአምላክነቱ እርግጠኛ ኹን።

⁘ ሌላኛው መልእክት ከአጠቃላዩ እይታ፣ የዘንደው ሕብረተሰብ የተዘጋጀ እራት ነው፤"አንድም መልአክ በፀሐይ ውስጥ ቆሞ አየሁ፥ በሰማይም መካከል ለሚበሩ ወፎች ሁሉ፦ መጥታችሁ የነገሥታትን ሥጋና የሻለቃዎችን ሥጋ የብርቱዎችንም ሥጋ የፈረሶችንም በእነርሱም የተቀመጡትን ሥጋ የጌታዎችንና የባሪያዎችንም የታናናሾችንና የታላላቆችንም ሁሉ ሥጋ እንድትበሉ ወደ ታላቁ ወደ **እግዚአብሔር እራት ተከማቹ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ።"ራእይ 19፥17-18** ። በአሰቃቂ ፍርዱ እርግጠኛ ኹን።

⁘ ሌላኛው መልእክት ከአጠቃላዩ እስካሁን ካየነሁ፣ በጉን ለመውጋት በሰይጣን ሕብረተሰብ የተዘጋጀው የተሰለፈው ሰልፍ መሸነፍ ነው፣ "በፈረሱም የተቀመጠውን ጭፍራዎቹንም ይወጉ ዘንድ አውሬውና የምድር

ነገሥታት ጭፍራዎቻቸውም ተከማችተው አየሁ።" ራእይ 19፥19 ።መጀመሪያ በተለይ መንገድ ያሳወቀው እንደገና የሚያሳየው መልእክት ግልጽ እንዲኾንና የተነገረው እርግጠኛነት የማጽደቅ ፤ ራዕዩን የሚያነቡት እንዲጽናኑ ነው። አውሬውም ተያዘ በእርሱም ፊት ተአምራትን እያደረገ የአውሬውን ምልክት የተቀበሉትን ለምስሉም የሰገዱትን ያሳተ ሐሰተኛው ነቢይ ከእርሱ ጋር ተያዘ፤ ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ።የቀሩትም በፈረስ ላይ ከተቀመጠው ከአፉ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ፤ ወፎችም ሁሉ ከሥጋቸው ጠገቡ። በአሸናፊነቱ እርግጠኛ ኹን።

፨ ሌላኛው መግለጫ ዮሐንስ ራእዩን ከተመለከተበት ጊዜ አንስቶ የሚኾነው ፣ የሰይጣን ታስሮ መቆየት ነው።"[1] የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፥ሺህ ዓመትም አሰረው፥ ወደ ጥልቅም ጣለው **አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማኅተም አደረገበት**፤ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።" ራእ 20፥1-3። ኢየሱስ ገና አገልግሎት ስጀምር የሰይጣን ስራ በማፍረስ ከሰዎች ልብ በማውጣት ፣በማሰር ነው።" ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች። ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል።ማቴ12፥28- 29።" ወንጌልም ኢየሱስ በከፈተው በርና መንገድ ለሺህ ዓመት [ለብዙ ዓመት] እስካሁን ሰይጣንን እንደፈለገ እንዳይቀሳቀስ ጠፍሮ በመያዝ የብዙዎችን ልብ ወርሷል፤በኢየሱስ ስም ስልጣን እንደፈለገ እንዳይንቀሳቀስ ስወጣ ስባረር ስሸሽ ኖሯል፤በኢየሱስ መምጣት የሰይጣን እንደፈለገ መንቀሳቀስ አለመቻል መታሰሩን ይገልጻል ፤ባይታሠር ኢየሱስ እንዴት ይገባል ? ስለታሰረ እንጂ ። ሰይጣን የታሠረው አሕዛብን እንዳያስት ነው እንደተባለው፣ የሚታተሙት ሙላት ስፈጸም ፣ ለጥቅት ጊዜ 1260 ቀናት ይፈታል፤ ይሠራል።

ሺህ ዓመት ቍጥር በሒሳብ አሃዝ ሳይኾን በምሳሌያዊ ገለጻ እንደቀረበ ከተረዳነው የመልእክቱን ጭብጥ እንይዛለን ።በመጽሐፍ ቅዱስ ሺህ ዓመት በጌታ አንድ ቀን ነው እንደሚል በመጽሐፍ ቅዱስ ፣በመጽሐፉ ሃሳብና አውድ ልንፈታ ይገባናል ። የሰይጣንን መፈታት መታሠር በአውድ ልክ ልንመለከተው ይገባናል ። መታሠሩ እንደ ፈቃዱ እንዳይሠራ በጌታችን መወለድ የጀመረ ስኾን፣ እስካሁን የሚታተሙት እስከሚሞሉ ድረስ አይሰለጠንም፤መፈታቱ ከታተሙት ቅዱሳን ሙላት በኋላ የሚጀምር የ3ዓመት ከ6ወር ዕድሜ ነው። ይኽንን በቀላሉ ከአውዱ እንረዳለን ፣ ሰይጣን እንደተፈታ በተለያየ መገለጦች የተመለከትነው ፣የመጨረሻው ጦርነት መጀመሩ አኹን ሰይጣን ታስሮ ያለ እንደኾነ እንዲንገነዘብ ያደርገናል ።ራእይ 20 … **ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፥** በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን፥ እንዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል፤ ቍጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው። ወደ ምድርም ስፋት ወጡ የቅዱሳንንም ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ፤ እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው። ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ። ሰይጣን ለጥቅት ጊዜ ተፈትቶ የመጨረሻው ውጊያ ሃይሉን አሟጦ ለማድረግ ብሰለፍም፣ እግዚአብሔር በሃይሉ አጠፋቸው የዘላለም ፍርድንም ሰጣቸው ። የሰይጣን መፈታት የሚያመለክተው 1260 ቀን፣ ከቤተክርስቲያን መሸሽግ በኋላ የሚኾነው ነው።ስለዚህም ሰይጣን አኹን ታስሮ ነው ያለው ። ኢየሱስ እያሰረው ቤቱን እየገባ ብዙዎችን ነፃ እያወጣ ነው። ሌላ ሺህ ዓመት የለምና፤አትቦዝኑ።ጆሮ ያለው ይስማ። ሰይጣን ታስሮ ያለው ክርስቶስ ወደ ምድር ከመጣበት አገልግሎት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው፤ቤተክርስቲያንንም እንደታሰረ እንዲቆይ ምክንያት የኾነች ከክርስቶስ ጋር የነገሰች የኖረች ናት፤ ይኽ ስፈጸም ሰይጣን ለጥቅት ጊዜ ይፈታል ፤ በክርስቶስ ፍርድ ይጠፋል፤ የክርስቶስ ዳግም ምጽአትም ይኾናል ።ይኽ ዕሳቤ አይደለም ።የነጠረ እውነት እንጂ። ጆሮ ያለው ይስማ ።

፨ ሌላኛው መልእክት ዮሐንስ ራእዩን ከሚያይበት ጊዜ አንስቶ ቶሎ እየኾነ ያለው ፣ የፊተኛው ትንሳኤ ነው። እነዚህ እግዚአብሔር ባዘጋጀው ዙፋን የተቀመጡ ፣በክብር ለስሙ ታምነው የሞቱ ፣ ቅዱሳን ናቸው ። "ዙፋኖችንም አየሁ፥ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቈረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፥ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ።"ራእ 20፥4። በዙፋኑ ላይ ከክርስቶስ ጋር መቀመጥ ብቻ ሳይኾን[ኤፌ1] ይፈርዳሉ ፣ ዳኝነት አላቸው ። ከክርስቶስ ጋር ይኖራሉ ይነግሣሉ

:: እነዚህ በፊተኛው ትንሳኤ የተነሱ ናቸው :: "**በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው**፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።" ራእይ 20፥6 :: እነዚህ የክርስቶስ ካህናት የተመረጡ ትውልድ ፣ ሰይጣን የማይሰልጥንባቸው፣ ፊተኛው ትንሳኤ ያገኙ ናቸው ::ፊተኛው ትንሳኤ ማለት በክርስቶስ ከፍርድ ያመለጡ ወደ ሕይወት የገቡ፤ ራሱ ክርስቶስ ያላቸው ማለት ነው::እኔ ትንሳኤ ነኝ እንደሚል:: እነዚህ ክርስቶስ ትንሳኤ ኾኖላቸው የትንሳኤ ሕይወት በምድር የሚኖሩ ፣የሚነግሱ ቅዱሳን ናቸው :: ብዙዎች ወደ ዚህ ሕይወት ክርስቶስን በማመን ብቻ እየተቀላቀሉ ይገኛሉ:: ከብዙዎች ሰይጣን እየወጣ ክርስቶስ እየከበረ እየነገሰ ይገኛል :: የሰይጣን መታሰሩና የፊተኛው ትንሳኤ እስካሁን እየኾነ ያለ ነው::

፨ሌላኛው መልእክት የመጨረሻው የፍርድ ሁናቴ የሚገልጽ ነው፣ "ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም።... ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፥ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ **እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ**።"ራእ 20፥11-13፣14፣15:: በየትኛውም ሁኔታ የሞቱ ሰዎች ነፍስ መቃብር ብኖርም ባይኖርም ይነሳል:: ለመጨረሻ ፍርድ:: እዚህ ጋር ከሞት የሚነሱት ኃጢአንና ጻድቃን ኹሉ እንደኾኑ እንረዳለን :: ኹሉም በእግዚአብሔር ልጅ ፊት ይቆማሉ እንደ የሥራቸው ይቀበላሉ ::ልክ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ለፍርድ በቀኝና በግራ እንደሚቆሙ እንዳመለከተ፣"በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።" ማቴዎስ 25፥33:: ይኽም ክፍል በመጨረሻው ፍርድ ላይ እንዲያ እንደሚኾን ያሳስባል :: አጠቃላይ ጠቅለል ያለ መልእክት ነው በዚህ ቊጥር ስር የተመለከትነው ::

፨ በኹሉም ካሜራዎች በኩል የተመለከትናቸው ክስተቶች በፍርድና በአሸናፊነት የሚጨርሱ ናቸው ::በዚህ ክፍል ላይም እስካሁን ያልታየ ነገርንም በተጨማሪ ይሰጠናል ፤ ኹሉም ዐድስ ስለመኾን::" አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።:ታላቅም ድምፅ ከሰማይ፦ እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ። በዙፋንም የተቀመጠው፦ እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም፦ እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞች ናቸውና ጻፍ አለኝ። አለኝም፦ ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞችም የአስማተኞችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።" ራእ 21፥1- 8::

***7ኛው መግለጫ**. በዚህ ክፍል የምናየሁ በጥቅሉ ፀሐይ የለበሰች፣ነጭ የለበሰች፣ሙሽሪት የበጉ ሚስት ተብላ በሌሎች መግለጫዎች የተገለጠችኹን ቤተክርስቲያንን ነው፤ በዝርዝር :: ከምዕራፍ 21፥9 እስከ 22፥6 ያለው ለዚህ ዝርዝር መግለጫ ይሰጣል :: "ሰባቱም ኂለኛዎች መቅሠፍቶች የሞሉባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ፦ ወደዚህ ና፥ **የበጉንም ሚስት ሙሽራይቱን አሳይሃለሁ ብሎ ተናገረኝ**።" ራእይ 21፥9 :: ይቺ የበጉ ሚስት ሙሽራይቱ ከሰማይ የወረደችው፣ የእግዚአብሔር መኖሪያ የኾነችው ቤተክርስቲያን ናት፤"በመንፈስም ወደ ታላቅና ወደ ረጅም ተራራ ወሰደኝ፥ የእግዚአብሔርም ክብር ያለባትን ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ፤ ብርሃንዋም እጅግ እንደ ከበረ ድንጋይ እንደ ኢያስጲድ ድንጋይ ሆኖ እንደ ብርሌ የጠራ ነበረ፤"ራእይ 21፥10-11 ::አንባቢ ቅድስ ከተማ ኢየሩሳሌም ተብላ በምሳሌ የተገለጠችኹ ሕንፃ ወይም ከተማ አይደለችም :: በሕንፃ ተመስላ የተገለጠችኹ ከሰማይ የምትወርደው የእግዚአብሔር ከተማ[መኖሪያ ]ሙሽሪት ቤተክርስቲያን ናት::

መጽሐፉን በሐዲስ ኪዳን መንፈስ ካለነበብን ልናስተውል ልንረዳ አንችልም :: እስራኤል የተባለችው በዚህ መጽሐፍ ሙሽሪት ቤተክርስቲያን ናት:: በዚህ ተመስላ የተነገረችው ጌታ የመረጣት ለዚህ ስለኾነ ነው:: ይቺ

እስራኤል ዘሥጋ የኾኑት አትወክልም ኹሉንም የሰውን ዘር ያለ ልዩነት በደሙ የፀደቁትን እንጂ። መጽሐፉ ለእስራኤል ዘሥጋ ይናገራል ሃሰተኞች ብሉም የእውነት ቃል እንዲህ ተገልጦ ስፈርድ ማመካኛ ስያሳጣ ይኖራል ። ቅጥሯ የተጠበቀ ታላቅም የኾነ፣ ብዙዎችን ከነገድ ከቋንቋ የተዋጁትን የያዘች፣ መሠረቷም በሐዋርያት ስም ትምህርት የቆመች ፣በእምነት ከኢየሱስ የተወለዱ የእግዚአብሔር እስራኤል የአብርሃም የእምነት ልጆች ናቸው ።144,000 የታተሙትም የእግዚአብሔር እስራኤሎች እኚህ ቅዱሳን ናቸው እንጂ የያዕቆብ እስራኤሎች አይደሉም ። ከተማይቱ የተለካች የሚገበባት በእሳት ተፈትነው ድል ነስተው ያለፉት ናቸው ።"የተናገረኝም ከተማይቱንና ደጆችዋን ቅጥርዋንም ይለካ ዘንድ የወርቅ ዘንግ ነበረው።" ራእይ 21፥15 ።እነዚህ የእግዚአብሔር እስራኤሎች የእፉኝት ልጆች የተባሉት ሳይኾኑ፣ ከያዕቆብ የተወለዱ የያዕቆብ ስም መሠረት የኾናቸው ሳይኾኑ፣ በበጉ ሐዋርያት ማንነት የተተከለች ቤተክርስቲያን ናት።ሰይጣን ይኽንን እንዲታውቁ አይፈልግም ።ጆሮ ያለው ይስማ። [አንዳንዶቹ በሞኝነት እንደሚሉት ታቦትና መቅደስ በሰማይ የለም]። መቅደሱ ራሱ እግዚአብሔር ነው።"ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርስዋ ዘንድ አላየሁም።" ራእይ 21፥22 ። እርሱ በመካከላቸው ያለ መጋረጃ ፊት ለፊት እያዩ ያመልኩታል ፤ ለዘላለም የሕይወት ውኃ ወንዝ ከውስጣቸው እየፈለቀ ሳይጠሙ ይኖራሉ። ራእ 22፥1-5።

***የራእይ ማጠቃላያ ከዚህ በኋላ ያለው ዮሐንስ** እስካሁን ለተመለከተውና[በተለይ በዚህ በመጨረሻው መግለጫ ስለተመለከተው የሚሰጥ አጠቃላይ መልእክት ነው። ሌሎችን መልእክቶችን ስዘጉ ፍርድን ይገለጻሉ ።በዚህ ግን ስለ ቤተክርስቲያን የተነገረ ስለኾነ ለዚህ ክብር እንዲበቁ ጥብቅ ማሳሰቢያ በምድር ለሚኖሩት ይሰጣል ። "እነሆም፥ በቶሎ እመጣለሁ። የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው አለኝ። ... ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው።" ራእ22፥7-14። ሰዎች ኹሉ የትንቢቱን ቃል ጠብቀው መዳንን እንዲወርሱ ያሳስባል ፤ ይኽ መጽሐፍ ሃሰተኞች እንደሚሉት ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው ቤተክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ ያለውን የሚናገር አይደለም ። በግልጽ እንደተመለከትነው በዚህ አመጽ ሳይሳተፉ ታምነው ስሙን ይዘው የሚኖሩ የሚገቡባት ሕብረት ናት። በቶሎ እመጣለሁ ጌታም ያለው ምድር ላይ ላለች ቤተክርስቲያን እንጂ ከሰማይ ስለወረደች 'ቤተክርስቲያን' ስለተነጠቀችኹ አይደለም ። መምጣቱን አውቀው በመምጣቱ እንዲኖሩ ጌታ የሚሰጠው መልእክት ትውልዱ እንዳይቀበል፣ በጅምላ በድፍኑ የተጻፈው ለእስራኤል ዘሥጋ ነው ፣የሚያመለክትውም ቤተክርስቲያንን አይደለም እያሉ የእግዚአብሔርን መልእክት ለገዛ ሃሳባቸውን እየተረጎሙ ይኖራሉ ። ፍርዳቸውም የተገለጠ ነው፥ " በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።" ራእ22፥18-19። ለሚሰማ ለኹሉ የተነገረው ለገዛ ፍላጎታቸው እየተረጎሙ ሰዎችን እያሳቱ ለጥፋት ልጅ ትውልዱን በመበረዝ መንገድ የሚጠርጉ እነዚህ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ሃሰተኛ አስተማሪዎች ናቸው ።

በዚህ መጽሐፍ ላይ የተጻፈውን በረከት ለመቀበል ጌታ የሰጠውን ግልጽ መልእክት የሚጻረር እስከዛሬ የሚያስተምሩ ዋጋቸውን ይቀበላሉ። ሰዎች መዳንን ያለ ሥራ በእምነት እንዲያው በነፃ ወርሰው ሕይወትን እንዲቀበሉና፣ ለተቀበሉት እውነት እንዲታመኑ የሚያስተምረውን የእግዚአብሔርን ቃልን በመጻረር ፣ መዳንን በብዙ መንገድና በብዙዎች በኩል በቀላሉ ማግኘት እንደሚችሉ በማስተማር ትውልዱን በጉን የሚዎጉ እነዚህ የዲያብሎስ ማህበረሰቦች ፍርድን ይቀበላሉ ። መጽሐፍ በግልጽ የሕይወት ውኃ መዳንን የዘላለም ሕይወት ያለ ዋጋ እንደሚቀበሉ ይመሰክራል ፣ አለኝም፦ ተፈጽሞአል። አልፋና ያሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ **እንዲያው** እኔ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።ራእ 21፥6-8። የዛሬዎቹ ከመበረዛቸው በፊት የጥንት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮም እንዲያ ነው፣ "..ሃይማኖታችን ክርስቶስ ብቻ ነው።""..ሰው ሥራ ሳይሠራ በሃይማኖት ብቻ እንዲጸድቅ እናውቃለን ።""በሃይማኖት ብቻ እንጸድቃለን ስላልን የታዘዝነውን በጎ ሥራ አንሠራም ማለት አይደለም "ሃይማኖት ለመጽደቅያ፤ መልካም ሥራ የሃይማኖት መግለጫ ነው። *[የቤተክርስቲያን ጸሎት ገጽ93-94፤ በኢኦተቤክ ሊቃውንት በ1935ዓ.ም በአ.አ የታተመ]። ድንቅ ነው።ያስደነቀኝ ይኽ የአባቶች የሊቃውንት ትምህርት፣ባልተማሩት ተምረውም በማያስተውሉት አዝም በተደረገባቸው ፈረሳውያን

## የቤተክርስቲያን ቅድሜ መከራ መነጠቅና ትርክቱ

ደብዛው ዛሬ ላይ  በመጥፋቱ ነው። ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስም ሙሽሪት ቤተክርስቲያንም "ና"ይሉኛልና፣ አልቆይም በቶሎ እመጣለሁ ፤የተጠማም የሕይወት ውኃ ይጠጣ ይምጣ ወደራሱ በማለት ያሳስባል ።ይኸንን ናልን ጥሪ ያቀረቡት ምድር ላይ ያለች ቤተክርስቲያን እንጂ የተነጠቀችው ቤተክርስቲያን ወይም እስራኤል ዘሥጋ አይደለችም ። ዮሐንስ ከሙሽሪት ቤተክርስቲያን አንዱ ነውና ለእግዚአብሔር ቃል ፈጣን ምላሽ ይሰጣል ፣“ይህን የሚመሰክር፦ አዎን፥ በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና።”ራእይ 22፥20። ይላል። ስለዚህም ወንድሞቼ በመጠን ኑሩ፤ እንዲንጠብቀው የተሰጠን ታላቅ የትንቢቱ ቃል አለንና ዐዲስ የግል የትንቢት ቃል አውጣብኝ እያልን ከሰው በሰው የኾነውን መልእክት ለመስማት ባንረባረብ መልካም ነው።አርፈን የተሰጠውን የተስፋ ቃል እንጠብቅ ። እየኾነ ያለውን እያስተዋልን በመጠን እንኑር ። “የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።” ራእይ 22፥21።

**ማጣቀሻ**

[1]የመጽሐፍ ቅዱስ መደበኛ ትርጉም ማጥኛ

[2] መጋቢ ተኩ ከበደ፣ የቅዱሳን በአየር ላይ መነጠቅ፣የመጀመሪያው ዕትም 1999ዓ.ም ፣ገጽ12

[3] ዝኒከማሁ  ገጽ29፤[4]ዝኒከማሁ ገጽ 30፤[5] ዝኒከማሁ ገጽ፤ 33 [7] ገጽ 37

[6]የራዕይ ዮሐንስ ጥናት መጽሐፍ፣ 2013ዓ.ም አ.አ

## 2. ለንጥቀት አስተምህሮ ስባል የተጨነገፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

መነጠቅ ማለት ወደላይ መወሰድ ማለት ስኾን በዚህ ሃሳብ ላይ ከሞት ተነስተው በትንሣኤ አካል ከመከራው በኋላ ወደላይ የሚወሰዱትን ሳይኾን፣ ከመከራው በፊት ከመቅጽበት እየተለወጡ ቅዱሳን ይነጠቃሉ ስለሚለው ሃሳብ ነው የሚወክለው። ለዚህ አስተምህሮ ይኾናሉ ብለው እያጣመሙ በድፍረትና በግምት የሚጠቅሷቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በጥልቀት አንድ በአንድ እንመለከታለን ።

*1ኛ. "እንግዲህ ሊመጣ ካለው <u>ከዚህ ሁሉ</u> **ለማምለጥ፥** በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ።"ሉቃስ 21፥36። **ማምለጥ የሚለው ቃል መነጠቅን ያመለክታል።** [1] "ሊመጣ ካለው ከዚህ ኹሉ" ማለት ሊመጣ ያለው አንድ ብቻ እንዳደለ እጅግም ብዙ ብዙ መቅሰፍት እንደኾነ እንረዳለን ። "በፀሐይና በጨረቃም በከዋክብትም ምልክት ይሆናል፤ በምድር ላይም አሕዛብ ከባሕሩና ከሞገዱም ድምፅ የተነሣ እያመነቱ ይጨነቃሉ፤<u>ሰዎችም ከፍርሃትና በዓለም የሚመጣበትን ከመጠበቅ የተነሣ ይደክማሉ</u>፤ የሰማያት ኃይላት ይናወጣሉና።በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል።ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቦአልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ።"ሉቃ 21፥25-28። አኹን አስተውሉ። እነዚህ ታላላቅ መቅሰፍቶች ስኾኑ ዓለማዊያን ምን እየመጣ ነው ብለው በመከራ ውስጥ ኾነው ያስባሉ፤ይጨነቃሉ፤ እናንተ ግን የኢየሱስ መምጫ እንደኾነ አውቃችሁ ነቅታችሁ ጠብቁ የሚል ነው። አስተውሉ ። እየኾነ ያለውን ታላላቅ መቅሰፍቶች የእግዚአብሔር ቍጣዎችን ቅዱሳንም በዓለም ስላሉ እየተመለከቱ ይገኛሉ። ስለዚህ አትሸበሩ እየመጣ ያለው ክርስቶስ እንደኾነ አውቃችሁ በእምነት ቁሙ የሚል ነው።ምክንያቱም እየመጣ ያለው መቅሰፍት ብቻ ሳይኾን የመጨረሻ ፍርድን ያደርጋል ።ስለዚህ በሰው ልጅ ፊት ለመቆም በክብር ለመኾን ከፈለጋችሁ ተግታችሁ ጠብቁ። የሚል ነው። ይኽ የሚያሳየው ቅዱሳን በመላው ምድር በሚደርሰው በመጨረሻው በጌታ ፍርድ ሳይጠፉ፣ ምልክቶቹን አይተው በትጋት እንድገኙ ነው። እንጂ ከመከራው በፊት በመነጠቅ ስለ ማምለጥ አይደለም ።ከጌታ ከኢየሱስ ጽድቅ ፍርድ ስለማምለጥ እንጂ። ቅዱሳን ሊመጣ ካለው መቅሰፍቶች የሚያመልጡት በምድር ኾነው በጌታ ተጠብቀው እንጂ ወደ ሰማይ ተነጥቀው አይደለም ።ምክንያቱም ይኽንን ኹሉ የመጨረሻው የፍጻሜ መቅሰፍት ይመለከታሉ ። ቃሉ በግልጽ ይኽንን ስያስቀምጥ አንዷን ቃል ከአውዷ እያፋቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለየ ልዩ ወንጌል ያስተምራሉ ። ጆሮ ያለው ይስማ። ተግቶ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከሚመጣ ድረስ መጠበቅ በግልጽ በመከራው ሴለማለፍ ያስተምራል ። የሰው ልጅ ፊት ለመቆም በማለት የሰው ልጅ የሚመጣው ለፍርድ እንደኾነ ያመለክታል ።ለፍርድ የሚመጣው ከታላላቅ የምድር መናወጦችና ቍጣዎች በኋላ እንደኾነ የተገለጠ ነው።

2ኛ. "ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ። በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ **ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ**።" ዮሐ 14፥1-3። "እወስዳችኋለሁ ማለቱ ከዚህ ዓለም መሄድን መነጠቅን ያመለክታል ።"[2] ወድ አንባቢ ቅዱሳን በመጨረሻው ዳግም ምጽአቱ እንደሚወሰዱ እንደማምን ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት እንደኾነ መስክርያለሁ። ነገርግን መሄድን መወሰድን ኹሉንም ጠቅልሎ ለቅድሜ መከራ መነጠቅ ማስረጃ አድርጎ መጠቀም ግን ትክክል እንዳልኾነ እያሳየሁ ነው። በዚህ ክፍል ላይ **ሁለተኛ እመጣለሁ** ኢየሱስ ማለቱ; መጀመሪያ በሥጋ እንደመጣ ቀጥሎም ልወስደን እንደሚመጣ የሚያረጋግጥ ስኾን፣ የክርስቶስ መምጣት ቅድሜ መከራ መምጣትና ከመከራው በኋላ መምጣት በመኾን ሦስት መምጣት እንዳልኾነ ልንገነዘብ ይገባናል ።የኹለተኛው መምጣት ዳግም ምጽአት የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው። በመምጣቱም በክፍሉ አውድ እንደተገለጸው በመኖሪያው ያኖረናል እንጂ ከመኖሪያው ወርዶ በአየር ላይ የሚያቆየን አይደለም ።አስተውሉ ።**ጌታ ያዘጋጀው መኖሪያ እንጂ ማረፊያ[ለጥቅት ጊዜ ለ7ዓመት የሚያቆይ ማረፊያ] አይደለም ።ማደሪያ ቋም መኖሪያ ስኾን፣ ማረፊያ ጊዜያዊ እንደ በርጎ ያለ መቆያ ስፍራ ነው**። ከቃሉ ጋር በፍጹም የማይሄደውን ለአስተምህሮአቸው ይኾን ዘንድ ብለው ከመሠረታዊ መልእክቱ የተፋቱትን የሚያስተምሩ እነዚህ ሃሰተኛ አስተማሪዎች ፣ በግ የሚመስሉ[ የማይጎዱ] ነገርግን ከአፋቸው በሚወጣው ቃል መርዘው የሚገድሉ ከሕይወት አክሊል የሚያጎድሉ ተንኮለኞች ናቸው ። ብዙ አስተማሪዎችን ዓለም በሰጠችው ዝና ጠፍረው ስለያዙ ፣እንደ ተራ አመለካከት ፥መረዳት እየቆጠሩ ፣መቃወም በሚገባ ልክ እንዳይቃወሙ በማድረግ አኮላሽተዋል ።ማንም ልቋቋመኝ የማይችል አንደበት በክርስቶስ አለኝ።ይኽንን እውነት ትውልድ እንዲነቃ እዚህ ግባ የማይባል ከትልም የማንስ ፣በሰዎችም ዓይን እምንት ያህል ቦታ የሌለኝ ገልጬ፣ከብርቱዎች ጋር ተሰልፌ እናገራለሁ ።ጆሮ ያለው ይስማ ።

3ኛ. "ጳውሎስ ለኤፌሶን ቅዱሳን ስጽፍ ጌታ ኢየሱስ ያለ ነውር የኾነችው ቤተክርስቲያን ለራሱ የሚያቀርበው በመነጠቅ እንደኾነ ያመለክታል።እንዲያቀርብ የሚለው ቃል በምድር ያሉትን ቅዱሳንን ወደ ሰማይ ማጓጓዝን ያመለክታል፤ይህም መነጠቅን ይጠቍማል።"[3] በዚህ ክፍል ላይ ጳውሎስ ስለመነጠቅ ያወራል ? የክፍሉ አውድ የሚለው እንደ በሪያ ሰዎች እንመለከታለን ፣"ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ **በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት** ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤""እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ **እንዲያቀርብ** ፈለገ።" ኤፌሶን 5፥26-27 ። ክርስቶስ ዳግም ለኹለተኛ ጊዜ ስመጣ በሕይወት ያሉት ከመቅጽበት ይለወጣሉ ፤ የትንሳኤ አካል ይለብሳሉ ፤ የሞቱት ይነሳሉ የትንሳኤ አካልንም ይለብሳሉ ። ይኽ ክፍል ግን ስለትንሳኤ ኾነ ስለመነጠቅ አይናገርም ። ክርስቶስ የራሱን ቤተክርስቲያን እንደዋጃት፤ ከዓለም ለይቶ በቅድስና እንዲትኾን ለራሱ እንድትኖር ለዘለዓለሙ እንደለያት ይገልጻል ።ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን ቀድሶ አንጽቶ ለራሱ አቅርቧል እንጂ ገና በመነጠቅ የሚያቀርብ አይደለም ። የእርሱ የኾነች ንፅህት ቤተክርስቲያን ለርሱ ኾና ትኖራለች ። በዚህ ክፍል ላይ ቤተክርስቲያንን በመነጠቅ ለማጓጓዝ ለማለት የሚያስችል ቃል የለም። ያውም ከመከራ በፊት መነጠቅ። ቤተክርስቲያን በምድር ሳለችም የእርሱ ናት።አካሉ ናት። ለእርሱ የተለየችና የቀረበች ናት።ፍጻሜው በሌላው ግንኙነት ፣ በደሙ ቀድሶ አስጀምሯታል። እንዲያቀርብ የሚለው ቃል ወደፊታዊ ብቻ አይደለም ። አኹናዊ ማቅረቧንና ቀጣይነት ያለውን ማቅረብን የሚያመለክት ነው። የሚያቀርበው ወደፊት ነው ብንል እንኳን የሚያቀርበው በመነጥቅና በማጓጓዝ ነው አውዱ አይልም፤ በቃሉ ቀድሶ በውኃ አጥቦ ያቀርባታል ይላል። ስለዚህም የክፍሉ አውድ የማይለውን የማያስተምረውን እየተራቀቁ በቃሉ እየሰለጠኑ እየተፈላሰፉ ያልተጻፈውን የሚያነቡ የክርስቶስ ካህናት አይደሉም ። ቤተክርስቲያን ላይ ተመሳስለው የተሰኩ መርዘኛ መርፌዎች እንጂ። ጆሮ ያለው ይስማ።

4ኛ. "እነሆ፥ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን **እንለወጣለን**፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን።ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።" 1ቆሮ 15፥51-53። እንለወጣለን የሚለው ቃል መነጠቅን ያመለክታል [4]። በዚህ ክፍል ላይ ጳውሎስ ስለ ትንሳኤ ያስተምራል ።"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤"1ኛ ቆሮንቶስ 15፥42 ። አስተውሉ። ትንሳኤ ከሞት ስለ መነሳት ነው። በአዲስ አካል በትንሳኤ አካል ስለመነሳታችን ጳውሎስ ያስተምራል ። የትንሳኤ አካልም የማይበሰብስ ዘላለማዊ መኾኑን ይገልጻል ። ክፍሉ ስለ ትንሳኤ ስለመኖር እንጂ ከትንሳኤው በኋላ ስለ መነጠቅ አይገልጽም ። ከትንሳኤ በኋላ መነጠቅ መኖሩ እሙን ብኾንም የክፍሉን አውድ መሠረታዊ መልእክቱን መያዝ አግባብ ነው። ጳውሎስ የኋለኛው መለከት ስነፋ፣ የሞቱ በትንሳኤ አካል የሚነሱ ከኾኑ፣ በሕይወት ሥጋ ያሉት ምን ይኾናሉ የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል ። በሕይወት ሥጋ ያሉት ከመቅጽበት የትንሳኤ አካል ይለብሳሉ ይለወጣሉ ። በማለት ይመልሳል ። በዚህ ሃሳብ ላይ መያዝ ያለብን፣ እነርሱ እንደሚሉት ከመከራው በፊት በስውር መነጠቅ እንደማይኾን ነው።አንድ ጊዜ ይኾናል የመጨረሻው መለከት ስነፋ። የሞቱት ይነሳሉ በሕይወቴ ሥጋ ያሉት ይለወጣሉ። ይኽ የኢየሱስ የመጨረሻው ሁለተኛ መምጣትን እንጂ ስውር ዳግም ምጽአት አያመለከትም ። በሕይወት ሥጋ ያሉ ቅዱሳን መለወጥና የሞቱት መነሳት አንድ ላይ መኾኑ ይኽንን ያረጋግጣል ።ከንቱ ሃሳባቸውን አፈር ከድመ ያለብሳል። ሌላኛው መረዳት የሚገባን ነገር የኋለኛው [የመጨረሻው] መለከት ማለት ምን ማለት እንደኾነና መቼ ይነፋል የሚለውን ነው፤ የመጨረሻ መለከት ምን ማለት እንደኾነ ወደ ራእይ መጽሐፍ በመጨረሻ መለከቶች የሚኾኑት ክስተቶች የተገለጡ እውነቶችና መገለጦች፣የተሰጡ መግለጫዎች እናያለን ፦

፤ እነሆ፥ ሦስተኛው **ወዮ** በቶሎ ይመጣል።ሰባተኛው መልአክ ነፋ፤ በሰማይም፦ የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ።በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው የተቀመጡ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ፦ ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ **ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ** ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን፤ አሕዛብም ተቈጡ፥ ቍጣህም መጣ፥ በሙታንም **ትፈርድ** ዘንድ ዘመን መጣ፥ ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም **ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ**፥ ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ።በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ።" ራእ 11፥14-18። ይኼኛው መግለጫ በኹተኛው መግለጫ አይተናል ። ወዮታ አለበት፤ የትልቁን ሃይል ይይዛል፤በአሕዛብ ላይ ይፈርዳል ፤ዋጋቸውን ይሰጣል፤ብቻውም ይነግሣል ። ስለዚህም የመጨረሻው መለከት የሚያመለክተው የመጨረሻውን ወዮ ፍርድን፤ የክርስቶስ መንገሥን፤ በሙታንም ላይ የሚሰጠው ፍርድ ነው። ሙታን ፍርድን የሚቀበሉት ከሞት ተነስተው በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ነው።ቅዱሳንም የሥራቸውን የሚቀበሉት በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ነው።ይኽ ኹሉ የሚኾነው በክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው። የኋለኛው መለከት ስነፋ የሞቱት ቅዱሳን በትንሳኤ አካል ይነሳሉ፤ በሕይወት ያሉት ይለወጣሉ፤ ሙታንም ይነሳሉ የመጨረሻው ፍርድ ይኾናል ።ይኽ ብቸኛው ዳግም ምጽአት ነው።

ስለዚህም እነዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ፤ከአዲስ ኪዳንም መንፈስ በራቀ መንገድ ከራሳቸው ከአዕምሮአቸው ተነሳስተው እንደሚተረጎሙት፣ከመከራ በፊት መነጠቅ የለም። ከመከራው በፊት የክርስቶስ መምጣትም የለም።

5ኛ."ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፥ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ **ሕንጻ** እንዳለን እናውቃለንና።በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃተታለንና፥ ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም።በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ የማንወድ ስለ ሆነ፥ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብደን እንቃተታለን።ነገር ግን ለዚሁ የሠራን እግዚአብሔር ነው እርሱም የመንፈሱን መያዣ ሰጠን። እንግዲህ ሁልጊዜ ታምነን፥ በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና በሥጋ ስናድር ከጌታ ተለይተን በስደት እንዳለን የምናውቅ ከሆንን፥ታምነናል ይልቁንም ከሥጋ ተለይተን በስደት መኖር በጌታም ዘንድ ማደር ደስ ይለናል።ስለዚህ ደግሞ ብናድር ወይም ተለይተን ብንሆን እርሱን ደስ የምናሰኝ ልንሆን እንቀናለን። መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ **እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና**። " 2ቆሮ 5፥1-10። የሚበሰብሰው ሥጋ የማይበሰብሰውን እስከ ሚለብስ ድረስ የሚቆይ ጊዜያዊ አካል ነው፤ ስለዚህም ከዚህ ጊዜያዊ አካል በመላቀቅ ድካም የሌለበት ዘላለማዊ የትንሣኤ አካል እስከምንለብስ ድረስ በመጓጓት እንኖራለን ፤ በጊዜያዊ ደካማ ሥጋችን ስላደረግነው ሥራ ኹሉ የሚገባንን ፍርድ እንቀበላለን ። ታዲያ ይኽ ክፍል የትንሣኤ አካል ስለመልበስ ከመናገር ውጪ ከመከራው በፊት ንጥቀት እንዳለው ይገልጻል ? አይገልጽም ።እንድሁም በመቃተት ከብዶ የሚኖረው በመከራው ውስጥ መኾኑን ያሳየናል ። ከአዲስ ከዘላለማዊ ፍጹም አካል ከለበስን በኂላ ንጥቀት አለ፤ ይኸም ከመከራው በኂላ ከመጨረሻው መለከት መንፋት በኂላ የሚፈጸም ነው። ለቤተክርስቲያን ቅድሚ መከራ ንጥቀትና ስለኢየሱስ ዳግም በአየር ላይ ስለመምጣት የሚናገር አይደለም ።

6ኛ. "**የጌታ ቀን**፥ ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፥ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኂልና።**ሰላምና ደኅንነት ነው** ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም።እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ቀኑ እንደ ሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም፥ ... እግዚአብሔር ለቊጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ። "1ተሰ 5፥1 - 9። ጳውሎስ የተሰሎንቄ ቅዱሳንን የኢየሱስ መምጫ ቀን አውቃችኂል ይላቸዋል ። ምክንያቱም አማኞች በተደጋጋሚ የሚደረጉ መቅሰፍቶች ስመለከቱ ምን ልመጣ ነው ብለው እንደ ዓለማዊያን የሚጠብቁ ሳይኾን፣ ኢየሱስ ልፈርድ ይመጣ እንደኾነ ያውቃል ። ስለዚህም ለአማኞች ተዘጋጅተው ለሚጠብቁ እንደ ሌባ ሳይኾን የሰጠው ቀን ቀጠሮ ደርሶ እንደሚመጣ ስኾን፣ ድንገተኛ አይደለም ።ለአሕዛብ ግን ድንገት የወረደባቸው ዱብዳ ነው። ምክንያቱም አሕዛብ እና ሃሰተኛው አስተማሪ ሰላም ነው፣ብልጽግና ነው፣ማደግን፣መንገሥ ነው፣መውረስ ነው ምድርን ስሉ፣ ኹሉንም እንዳልነበረ የሚያደርግ የጌታ ቀን ይመጣል ። በጨለማ ስላይደልን እንደ ሌባ ሳይኾን፣ ለመጓዝ ለመሄድ እንደተዘጋጅን ሰው ስንጠብቅ መጥቶ ይወስደናል ። የጌታ ቀን ታላቅ ፍርድ የሚደረግበት ፣ዲያቢሎስ ተይዞ ከነጭፍሮቹ ወደ እሳት ባሕር የሚጣሉበት ፣ አሕዛብ የፍርድ የተነሳ የሚያለቅሱበት መሸሸጊያ የለሌበት ቀን ነው። ለጌታ ምርጦች ደግሞ የምስጋና የንግሥና የክብር ቀን ነው።ቊጣው በእኛ ላይ አይደለም ። በመጨረሻው መለከት ለእኛ የዘላለም ሕይወት ፤ለአሕዛብና ለሰይጣን የዘላለም ሞት ይኾናል ። ስለዚህም ለቊጣ አልመረጥንም ማለት ከታላቁ መከራ በፊት ወደ ሰማይ እንነጠቃለን ማለቱ አይደለም ። ከአውዱም ከአጠቃላዩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሃሳብ የተፋታውን ልዩ ወንጌል ያስተምራሉ ። የጌታ ቀን ለአሕዛብ ቊጣ የሚኾንበት ያ የመጨረሻው ፍርድ እንጂ ከመከራው ዘመን በፊት ስለመነጠቅ የሚናገር አይደለም ። አንዷን ጥቅስ ከተመለከትን እውነት ልመስል ይችላል እንጂ እውነቱ በመጻሕፍት የተገለጠ ነው።ከፍም ዝቅም ብለን ማንበብ አለብን፤መጽሐፍ ቅዱስ በግላችን ኾነኔን ይኽ ጸሐፊው የሚለውንም ትተን ቃሉ መሠረታዊ ትርጓሜ ምን ይላል የሚለውን ማጥናት አለብን። እስከዛሬ የተሸወድነው ልቆጨን ይገባል ፤ መንከራተት ልያበቃ ይገባል ።

7ኛ. "በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ።የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ **ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ**። በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል። "2ተሰ 2፥6-12 ።አውሬው በግልጽ እንዳይሠራ የሚትከለክለው ቤተክርስቲያን ስላልተነጠቀች ነው፤መንገድ እስኪትወገድ የሚለው ቤተክርስቲያን መነጠቅን የመለክታል [5]የሚለው ሃሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ መልእክት ጋር ይቃረናል ።በእርግጥም በግልጽ እንዳይሠራ የምትከለክለው ቤተክርስቲያን ናት፤የሚትወገደው ደግሞ ግን ቤተክርስቲያን አይደለችም ። የቤተክርስቲያን መነጠቅ ለአውሬው ነፃነት አይሰጥም የሚለውን ለማስገንዘብ እወዳለሁ ። [በዚህ ክፍል ላይ አውረው በግልጽ እንዳይሠራ ቤተክርስቲያን መከልከሏ፤የቤተክርስቲያን ንግሥና የሰይጣን መታሠር ጊዜ እንደኾነ ከላይ የተመለከትነው ሃሳብ ስያጸድቅ እናያለን ]። ክርስቶስ የአመጽ ሰው ሃሰተኛው ነቢይ ከመገለጡ በፊት

አስቀድሞ አይመጣም ።አውሬውም ቤተክርስቲያን ታትማ ሙላቷ ሳይፈጸም ፤ሴቷ ጸሃይ ሳትለብስ ፤ ብርቱዎችን ሳትወልድ፤ የእግዚአብሔር እስራኤሎች 144,000 ተብሎ በቊጥር አሃዝ የተመሰሉትን ተቈጥረው የማያልቁ ታትተመው ሳያልቁ፣ መለኮታዊ ሃይል ተሟልታ እንዲትበር እንዲታመልጥ በክብር እውቀት ሳትሞላ፣ አውሬው በግልጽ አይመጣም። አውሬው በግልጽ የሚመጣው ቤተክርስቲያን ዝግጅቷን ስትጨርስ ስኾን፣ መጀመሪያ ከሰማይ ወደ ምድር ይጣላል ።ከዚያም የሰማይ መኖሪያውን ይለቃል። ከዚህ በኋላ በቊጣ በግልጽ ይሠራል።ቤተክርስቲያን በአውሬው ላይ ነግሳ በኢየሱስ ስም ስልጣን ሠልጥና ጠፍራ ከያዘችበት ፣መንገዱን ከዘጋችበት ፣ ዝግጅቷን ስትጨርስ ወደ ሰማይ ሳይኾን በምድር ከእይታው ትሠወራለች ። በዚህ ክፍል ላይ ጳውሎስ የዓመፃ ሰው ከመገለጡ በፊት ቤተክርስቲያን መከልከሏን እንጂ ስትነጠቅ ወደ ሰማይ ስትሰበሰብ ለሰይጣን መግቢያ እንደሚኾን አያስረዳም።እንዲሁም የመጨረሻው የአመጸ ሰው የሚገለጠው ለ3ዓመት 6ወር ታላቅ መከራ ስለኾነ ቤተክርስቲያን ነበረች።ምክንያቱም ወንድ ልጅ እንደተወለደ ነው ሰይጣን ወደ ምድር የተጣለው ። አንባቢ ያስተውል ። ከመንገድ እስኪወገድ የተባለችው ቤተክርስቲያን አይደለችም ። የሚወገደው ሰይጣን ነው።ለዘላለም እስከሚወገድ ድረስ ለጥቅት ጊዜ ከቤተክርስቲያን ሙላት በኋላ ይፈታል ።የተሰጠውን ጊዜ ስያበቃ ወደ እሳት ባሕርይ ውስጥ ይጣላል ።

8ኛ. " ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ **አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን**።ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር **ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል**ና።በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤**ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳል**ና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።" 1ተሰ 4፥15- 18። በዚህ ክፍል ላይ በግልጽ በሕይወት ስላሉት ቅዱሳን መነጠቅ ተጽፏል ።ሌሎች ክፍሎች ከመቅጽበት መለወጥ እንዳለ ብልጭታ ብሰጡም፣ ይኸኛው ክፍል በግልጽ በሕይወት ስላሉት መነጠቅ ያስረዳል ።የጳውሎስ ትኩረት በጌታ ኾነው ስለሞቱ ቅዱሳን መጨረሻ ማስረዳት ነው። አሕዛብ እንደሚያስቡት ስሞቱ ሕይወት መጨረሻ ሳትኾን ለአዲስ ሕይወት ጅማሮ እንደኾነ ያስረዳል ።በዚህ ከክፍሉ ሃሳቦች ትንሽ ጠጠር ያለች "ያንቀላፉቱን ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል "የሚለው ይገኛል ።ይኽንን ለመረዳት የጳውሎስ ትኩረት መያዝ አለብን፤ ስለሞቱት ቅዱሳን እንደሚያስረዳ ። የሃሳቡ ቅደም ተከተል እንዲህ ነው፣ **፩ኛ.** ክርስቶስ ሞቷል ተነስቷል ይኽንን እወቁ፣ **፪ኛ.** በክርስቶስ ኾነው የሞቱትን ጳውሎስ አንቀላፍተዋል በማለት ነገሩን ለማስረዳት ያመቻቻል፣ ያንቀላፋ ይነሳል የሞተ ግን አይነሳም የሚል ዕሳቤ ስለነበራቸው ፣ በክርስቶስ ኾነው የሞቱትን አንቀላፍተዋል ይለናል ፣ **፫ኛ.** ክርስቶስ ዳግም ስመጣ የሞቱት ይነሳሉ፣ **፬ኛ.**ክርስቶስ ዳግም ስመጣ ያልሞቱት ቅዱሳን ይለወጣሉ ፣ **፭ኛ.** ክርስቶስ በቅዱሳን መላእክት ታጅቦ ይመጣል፣ ስለዚህ ስለሞቱት ቅዱሳን የሚሰጠው ግንዛቤ ፣አስቀድመው የትንሣኤ አካል ስለሚለብሱ አስቀድመው ከጌታ ጋር ይኾናሉ፤ማለትም ተነጥቀው አይደለም ፤ባሉበት በለበሱት አካል።**ስለዚህም የሞቱት ክርስቶስ ስመጣ የሞቱትን ከነበሩበት ከተጣሉበት፣ ከወደቁበት፣ከተቃጠሉበት፣ከተሰጡበት ያመጣል፤ያነሳል።** በሕይወት ካሉት ቅዱሳን ቀድመው በአዲስ ማንነት ይገኛሉ ።ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ክርስቶስ ስመጣ ከእርሱ ጋር በሕይወት ወዳሉት ያመጣል ፤ ያመጣል የተባለው ከሰማይ ወደምድር መጀመሪያ ከተነጠቁበት ሳይኾን በሕይወት ካሉት ቅዱሳን በሞት ከተለዩበት ስፍራ ያመጣል ማለት ነው።በክርስቶስ መምጣት ያልነበሩ ቅዱሳን ወደ መኖር ይመጣሉ ።ይኽም ቀድመው መነሳቸውን፣ ክርስቶስ በባሕር ፣በእሳት ፣ለአውሬ እራት የኾኑትን ፣የሉም ጠፍተዋል፣ሕይወታቸው አልቀዋል የተባሉትን፥ ክርስቶስ ስመጣ እግዚአብሔር ለሞቱት ሕይወት በመስጠት ያስነሳቸዋል ፤ ያመጣቸዋል ማለት ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ስመጣ በቅዱሳን መላእክት እንደታጀበ ብቻ ክፍሉ ያስረዳል ። ጳውሎስም ለማስተማር የፈለገውን ሃሳብ በሚገባ አሳይቷል ። ይመጣሉ።እንደ ሞቱ ጠፍተው አይቀሩም ። በዚህ ክፍል ላይ; በመጨረሻው ፍርድ በጉ ሠራዊቱን እያስከተለ በመለከት በመላእክት ድምጽ በግልጽ ታጅበው ስለመምጣት እንጂ ቅድሜ መከራ ይነጠቃሉ የሚል ሃሳብ የለም። ይኽ ቅድሜ መከራ መነጠቅ ከኾነ; የሞቱት የሚነሱት ስንት ግዜ ነው? በሕይወት ያሉት የሚለወጡት ስንት ግዜ ነው ? መጽሐፉን ለጸሐፊው መንፈስ ቅዱስ በገለጠበት መንፈስ ማንበብ አስፈላጊ ነው። ከመሃል እየመዠግን ቃሉ ማለት የፈለገውን ትተን የራሳችን ትርጓሜ ለመስጠት መድፈር በነፍስ ላይ መቀለድ ነው። ጳውሎስ ይኽንን ስገልጽ ይመስለኛል አላለም፤ ታላቁን እውነት ከራሱ ሃሳብ ዕሳቤ ተነሳስቶ ስላልተናገረ፣ በጌታ ቃል እላለሁ በማለት አመላክቷል ።ባዶ ደመና የኾኑት መምህራን ትክክል? ወይስ የጳውሎስ? ኹሉም ትክክል የሚመስላቸው በፍደል በቀልም ጥበብ በቃላት ስንጠቃ ቅመራ እየተመጻደቁ፣ ኹሉም ትክክል ነው እያሉ፣ እውነተኛውን መልእክት ትውልዱን ማሳየት አልቻሉም ። መጋቢ በሥልጣን እንደ እግዚአብሔር መጋቢ በትህትና የቃሉን እውነት ምስጢሩን መግለጥ አለበት ፤ ማንም በቃዡው በተፈላሰፈው እየተወዛገበ ልኖር አይገባም ። እነኚህ ውኃ ወደ መቋጠር ካልገቡ በሚመጣው ንፋስ ከመጥፋትና ከመወሰድ ሌላ ምርጫ የላቸውም ።ጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው።ጆሮ ያለው ይስማ።ምስክርነቱ ከቃሉ ኹሉ ጋር የተስማማ ስሙር የኾነ ነው።

9ኛ. "የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ **አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች በወፍጮ**

**ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች**::" ማቴ 24፥39-41:: ይኽንን ሃሳብ ኢየሱስ ስለመጨረሻው ዘመን ከተናገረበት ከምዕራፍ 24 ጀምረው ያለውን በዝርዝር እንመለከታለን :: ሙሉ መረዳት እንዲኖረን ::ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወደ መቅደሱ ጅራፍ ይዞ የገባውን ክስተት ከም.21-23 ያለው ቃል ያስረዳል :: ከመቅደስ ወጥቶ ስሄድ በም.24 ላይ ደቀመዛሙርቱ ጥያቄ አቀረቡ፦ "ኢየሱስም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ። እርሱ ግን መልሶ፦ ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ፥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው።" ማቴ 24፥1-2። የኢየሱስ መልስ አስደንጋጭ ነበር፤ ደቀመዛሙርቱ በሚያሳዩት ሕንፃ ከመደነቅ ይልቅ፣ እንዲህ እንዳማረበት እንደማይቀር እንደሚፈርስ ነገራቸው :: በዚህ ደቀመዛሙርቱ በይበልጥ ስለዚህ ነገር ስለ ቤተመቅደስ መፍረስ ማወቅ ፈልገው ጥያቄ አቀረቡ፦

“እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፦ ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት።”ማቴዎስ 24፥3 ::ከደቀመዛሙርቱ ጥያቄዎች ፣ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ዳግም እንደሚመጣ እንደሚያምኑና እንደሚያውቁ ደግሞም በመጪው ዘመን የሚኾን ስለኾነ፣ የኢየሱስን መምጣት ከመቅደሱ መፍረስ ጋር በአንድ ጊዜ እንደሚኾን ማሰባቸውን እንረዳለን። ጥያቄአቸውን ፩ኛው. ስለ ኢየሩሳሌም መቅደስ መፍረስ ስኾን፣ ፪ኛው. የኢየሱስ መምጣትና ምልክቱ ምንድነው የሚል ነው። ኢየሱስ ለጥያቄአቸው [የቤተመቅደስ መፍረስና ስለመምጣቱ] የሰጠው ምላሽ አጠቃላይ ማስጠንቀቂያና ምልክት ነው ፦

"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ማንም እንዳያስታችሁ **ተጠንቀቁ**።ብዙዎች፦ እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ።ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ፤ **ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው**።ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤**እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ** ናቸው።በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፥ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤ብዙ **ሐሰተኞች ነቢያትም** ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ **የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል**፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል። " ቍ.4-14። ማስጠንቀቂያው ሃሰተኞች ክርስቶሶች እንደሚነሱ፣ ጦርነት እንደሚኖር፣ የአንድ ወገንና የመንግስታት ጦርነት እንደሚካሄድ ፣ ይኽ ኹሉ ስኾንም መጨረሻ ገና እንደኾነ አስረዳቸው :: ስለዚህም አንባቢ እነኚህ ክስተቶች ከታርክና አኹን አየኾነ ያለውን በመመልከት ወደ መጨረሻ እየሄድን እንደኾነ ፣የትንቢቱ ቃሉ እየተፈጸመ እንደኾነ መረዳት ይችላል ::ይኽ ከራእይ ምዕራፍ ስድስት ከአንደኛው እስከ አምስተኛው ማህተም ጋር ካለው ስሙም እንደኾነ አንባቢ ማስተዋል ይችላል :: በዚህ ላይ የሐሰተኛ ትምህርት ጥቃት ፣ብዙዎችንም ማሸነፍ፣ የእርስበርስ የአንድ ወገኖች ጦርነትና የዓለምአቀፋዊ ጦርነቶች [በመንግስታት] እንደሚካሄዱ ተመልክተናል :: ይኽ የትንቢት ቃል ኢየሱስ የገለጠው ከተገለጠበት ጊዜ ጀምሮ እየኾነ ያለው ስኾን፣ መጨረሻው ገና መኾኑን ፣መምጣቱ የዓለም ፍጻሜ ገና መኾኑን ያመለክታል ::ብዙዎች ሳይረዱ በእነዚህ ክስተቶች የመጨረሻው እንደኾነ ተረድተው ስስቱና እስካሁን ጌታ አልመጣም በማለት እንደማይመጣ በማሰብ ሰነፎች ኾነዋል፤ ተኝተዋል ::እነኚህ ምልክቶች መጨረሻው ገና መኾኑን የሚገልጹ እንደኾኑ ልናስተውሉ ይገባናል :: እነዚህ የመጨረሻው እንደ ቀረቤ ጠቋሚ የምጥ ጣር መጀመሪያዎቹ ናቸው :: የምጥ ጣር መጀመሪያ የሰይጣንን ወደ ምድር መውደቅ ፣የአውሬውን መነሳት የሚያመለክት ነው። ታላቁን ምጥ መግቢያ የሚገልጽ እንጂ ::ሃሰተኞች እንደሚሉት አይደለም ::

የጌታ መምጣት የመጨረሻው ከመኾኑ በፊት፣ የሐሰተኞች ነቢያት መነሳት ብዙዎችንም ማሳት እስካሁን እየበዛ የመጣ ነው፤የብዙዎች ሃሰተኞች መነሳት ይኽንን ቃል አረጋግጧል ::እነዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው ሸቃቅጠው ለገዛ ፍላጎታቸው ይኾን ዘንድ አጣመው የሚሰብኩ እንደሚሉት አይደለም። አሕዛብ ይድኑ ዘንድ የወንጌል እድል ስለተሰጣቸው ፣ የመንግሥቱ ወንጌል እስካሁን እየተሰበከ ይገኛል :: ሰዎች ይድኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር አገዛዙ ይገቡ ዘንድ፣ ከሰይጣን እስራት ይፈቱ ዘንድ የመንግስቱ ወንጌል ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት፣ ከመጨረሻው በፊት ይሰበካል ፤እየተሰበከ ይገኛል ::ሃሰተኞች እንደሚሉት ወንጌልን እንደሚሸቃቀጡት አይደለም :: የጸጋ ወንጌል እንጂ አኹን የመንግሥቱ ወንጌል የለም፤አይሰበክም በማለት ብዙዎችን አንደ አዋቂ ስያምታቱ ቆይተዋል። ጆሮ ያለው ይስማ :: አዕምሮ በሰይጣን ካልተያዘ በስተቀር የመንግሥቱን ወንጌል በክርስቶስ ሥራ እንዲያ በጸጋ በእምነት እንዲድኑ ጌታ ያዘጋጀውን የምስራች ፣ በዘንደው መንፈስ እየተመሩ[በስውር]ለዓላማቸው አልመች ስላለ እያጣመሙ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በድፍረት ይናገራሉ ፤ያስተምራሉ ::ብዙዎችን ያስታሉ። ብዙዎችን በቃላቸው ጠፍረው ይዘው እንደ መረዳት ነው እያስባሉ አሸሽገዳመ እያሉ እየተሻሹ እየተሞጋገሱ ይኖራሉ :: እንዲያ የሚኾኑትም ልሰቱ የደረሱ ናቸው :: የእግዚአብሔርን እውነት በእግዚአብሔር እውቀት እናገራለሁ :: የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው። ይኽ የመጣው ከፍደል ቅመራ ከብዙ ትምህርት አይደለም ::ጌታ እንደ አገልጋይ[ እኔን ከሁሉም በምንም የማንስ] ስለቆጠረኝ እንጂ። ጆሮ ያለው ይስማ ::እውነት ከሚመስል ከውሸት [ትምህርት] ተጠበቁ። የተኛውንም ሃሳብ ቃሉ መግልጽ ያልፈለገውን መናገር

ከእግዚአብሔር የመጣ አይደለም ። ከእግዚአብሔር ያልኾኑት ምሩቃን የመብዛታቸው የአንድ ልብና የአንድ መንፈስ የአማኞች ሥላሴያው ሕብረት እንዲጠፋ አድርጓል ። [መማር ሳይኾን ችግሩ መንፈስ ቅዱስ አልባ መኾን ነው እያልሁ ነው] ።ኢየሱስ ለኹለቱ ጥያቄዎች አንድ ላይ ከመለሰው እየለይን እናያለን ።ከዚህ ቀጥሎ ኢየሱስ የሚሰጠው መልሽ ግሪታን የሚያጠራውን፣ በሰፊው የቀረበውን እንመለከታለን ፦

[1]"**እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኵሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥** በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ፥ በሰገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ፥በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ።በዚያችም ወራት ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው።ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ፤በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና።እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ።በዚያን ጊዜ ማንም፦ እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም፦ ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ። እነሆ፥ አስቀድሜ ነገርኋችሁ። እንግዲህ፦ እነሆ፥ በበረሀ ነው ቢሉአችሁ፥ አትውጡ፤ እነሆ፥ በእልፍኝ ነው ቢሉአችሁ፥ አትመኑ፤መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤በድን ወዳለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ።" ቊ.15-28።  ይኽንን መልስ ደቀመዛሙርቱ ካቀረቡት ከኹለቱ ጥያቄዎች አንፃር እንረዳለን ፤ስለ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ መፍረስና ስለ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት ።

ስለ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ መፍረስ አንፃር ፣ ትንቢቱ በ70 ዓ.ም ተፈጽሟል ። የጥፋት እርኩሰት የተባለው በተቀደሰችው ስፍራ መቅድስ ላይ የቆመው ፣ መቅደሱን እንዳልነበረ ለማድረግ የመጣ የሮም ቄሳር ነው። ይኽ ጊዜያዊ በ70ዓ.ም የተፈጸመ ስኾን ታርክም ስለ ኢየሩሳሌም መቅደስ መፍረስ በ70 ዓ.ም እንደኾነ ይመሰክራል ። ስለዚህ መቅደሱ ከመፍረሱ በፊት ከዚያች ከተማ ሽሹ የሚል መልእክት አስቀምጧል ።ይኽ ትንቢት በኢየሩሳሌም ላይ ብቻ የሚደረግ ስለኾነ የሽሽታውን ሁኔታ ፣ እርጉዞችን የሚያጠቃ ነው።ምክንያቱም በዚህ የሚያመልጡት የሮጡት ብቻ እንጂ ያመኑቱ ብቻ አይደሉም ።ስለዚህም ያመኑትም ወደ ሌላ ከተማ  መሮጥ አለባቸው ። መከራው በኢየሩሳሌም ብቻ ስለኾነ ለሽሽት አመቺ ወቅት እንዲኾን ፣ ለሞት አሳልፎ እንዳያሰጥ ፤ ማምለጥ ስችሉ ወደኃላ እየተመለሱ እንዳይወሰዱ፣ ከመከራው እንዲቀሩ እንዲተርፉ ፣ በመከራው እንዳይነጠቁ ያሳስባል ። ከጥያቄዎቹ እና ከመልሱ አንፃር ስንመለከት በአንድ በኢየሩሳሌም ላይ ብቻ የተወሰነ ስለኾነ ስለ ቤተመቅደስ መፍረስ እንደተነገረ እንደኾነ እንረዳለን ።

ስለ ዓለም መጨረሻው ከመቅደስ መፍረስ ጋር ተያይዞ የተነገረውን ወቅቱን ለይተን ለመረዳት  የክፍሉን አውድ በትህትናና በተፅግሥት ልንመለከተው  ይገባናል ። የጥፋት እርኩሰት መቅደስ ላይ መቆም ፣የአውሬው ዋነኛው መዲና ኢየሩሳሌም መኾኑን ያመለክታል “በድናቸውም በታላቂቱ ከተማ አደባባይ ይተኛል እርስዋም በመንፈሳዊ ምሳሌ ሰዶምና ግብጽ የተባለች ደግሞ **ጌታቸው የተሰቀለባት ናት**።” ራእይ 11፥8 ፣  የጥፋት እርኩሰት በኢየሩሳሌም ስነግሥ በግልጽ ስመለክ፣ መሥራት ስጀምር፣ ወደ ምድር ሰይጣን ወርዷል ማለት ነው። ይኽ ስኾን ታላቁ መከራ 1260 ቀን ስቃይ በምድራዊያን ላይ ይጀመራል ማለት ነው። እነዚህ የመከራ ቀኖች ጥቅት ናቸው ፤እንዲያ ባይኾን ብዙዎችን ያስት ነበር ማለት ነው። በዚህም ሃሰተኛው አውሬው መገለጥ [ከምድር የወጣው አውሬ ሃሰተኛው ነቢይ ፤የጥፋት ልጅ] ክርስቶስ በሰማይ ነው፣በምድር ነው፣ በተራራ ነው፣ .ወዘተ. እያሉ በዚያ ጊዜ ልያስቱ ይሞክራሉ ።እናንተ ግን አትከተሉት ፤ እወቁ የሚል ነው። ይኽ የአውሬው መገለጥ በመቅደስ መቆም የምጥ ወቅት መኾኑን አንባቢው ያስተውል ።ስለዚህም ኢየሱስ በዚያን ጊዜ በስውር እንዳለና ፣እንደሚገኝ ብናገሩም አትመኑ።ምክንያቱም የኢየሱስ መምጣት ግልጽና ግልጥ ነው። መብረቅ ቦግ ብሎ በዓለም ኹሉም እንደሚታይ የኢየሱስ መምጫ መገኛ መኖሪያ ስመጣ በግልጥ ይታያል ። እነዚህ ሃሰተኞች የዘንዶው መንገድ ጠራጊዎች በዚህ ሰዓት ኢየሱስ በስውር እንዳለ ያስተምራሉ ፣ስርግ በስውር እንደሚኾን ያስተምራሉ ፣ እናንተ ግን እወቁ አትመኑ ፤አትከተሏቸው። ስለዚህ ከኢየሱስ መልስ የቤተመቅደስ መፍረስ እና ስለመምጣቱ የነገረው ምልክቱ ተመሳሳይ እንደኾነ እንረዳለን ። ይኹን እንጂ በኢየሱስ መምጣት ማንም የትም መሸሽ አይችልም ።ምክንያቱም ሙሉ ምድር የሚያጠፋ ቊጣ ስለሚገለጥ ። የወቅቱ ቀረምት መኾን አለመኾን ለውጥ አያመጣም ። እንዲሁም ማንም ወደሌላው ሃገር ከተማ ተራራ በመሸሽ ልያመልጥ  አይችልም  ።

 ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ። ማቴ 24፥29-31 ።  ከዚያች ወራት መከራ በኋላ [አውሬው በነገሠበት ከ42 ወራት ታላቁ መከራ በኋላ ] ኢየሱስ ይመጣል ። ኢየሱስ ስመጣ ምልክት በሰማይ ይታያል ። ምድር ላይ የሚኖሩ ያዩታል ። የመላእክት መለከትም ያስተጋባል ። ጌታ በግልጽ እንዳስተማረው ፣ ከአውሬ በኢየሩሳሌም መዲናነት ፣በግልጽ በምድር ላይ ስገለጥ ታላቅ መከራ ይኾናል ።ከዚያም በኋላ የተሰጠው ጥቅት ጊዜ ስያበቃ የኢየሱስ

መምጣት ይኾናል ::ስለ መምጣትህ ንገረን ያሉት በዝርዝር አስረድቷል ::ጌታ ኹለት ጊዜ እንደሚመጣ ፣በስውር እንደሚመጣ ፣ አልገለጸም :: የኢየሱስ መምጣት የዓለም መጨረሻ ነው:: ታዲያ ስለመጨረሻው ዘመን ስያስተምር ቅዱሳን ቀድመው እንደሚነጠቁ እንደማይገኙ አልገለጸም ፤ ይኽ ትውልድ አያልፍም በማለት በመከራው ማለፋቸውን አስረድተዋል ::ደግሞም በዚያ መከራ ሰዓት ሳይታለሉ ጸንተው እንዲቆሙ አስጠንቅቋል :: ኢየሱስ ስለ መምጣቱ ኾነ ስለ መጨረሻው ዘመን ስለ ታላቁ መከራ ስያስተምር ኹለቴ እንደሚመጣ አላስተማረም ::አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚመጣ እንጂ ::

"ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም:: **የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና::በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥ የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል:: በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች::" ማቴ 24፥36-41::**

በዚህ ክፍል ላይ በኢየሱስ መምጣት በዚህ ምድር ላይ በኖኅ ጊዜ እንደኾነው እንደሚኾን ተገልጿል፤ ይወሰዳል ይቀራል፤ትወሰዳለች ትቀራለች :: እነዚህ ቃላቶች ለቅድሜ መከራ መነጠቅ አስተምህሮ የሚጠቀሱ አይደሉም :: አንባቢ ያስተውል:: በኖኅ ጊዜ የጥፋት ውኃ ልመጣ ስል የሰው ልጆች አላወቁም ነበር፤ ኢየሱስ ስመጣም ምድራዊያን አያውቁም ::ቤተክርስቲያን እንደ ኖኅ ስትዘጋጅ ፤ዓለማውያን ደግሞ በጥፋታቸውም ይቀጥላሉ ::ምልክቶችን ስመለከቱም አያስተውሉም :: ስለዚህም መርከቡ ተሰርቶ እንዳለቀ ፣የጥፋት ውኃ መጥቶ ይወስዳል ፤ የሚመጣው ውኃ የጥፋት ውኃ ነው::የሚወስደውም ይኽ የጥፋት ውኃ ነው:: ከዚህ ጥፋት ውኃ ሳይወሰዱ መቅረት መትረፍ ነው:: ልክ እንደዚህ እንደ ጥፋት ውኃ ኢየሱስም በታላቅ ቊጣ ይመጣል ፤ በቊጣው ስገለጥ በቊጣው የምወሰዱት ምድራዊውን ናቸው :: የሚቀሩት የሚተርፉት አስተውለው ተዘጋጅተው የኖሩ ናቸው :: የጌታ መምጣት በጥፋት ውኃ መመሰሉን ካስተዋሉ ይኽን መረዳት አያስቸግርም :: ይኽ ለቅድመ መከራ መነጠቅ የሚጠቀስ ሳይኾን ከመከራው ከአውሬው ከጥፋት ልጅ ከታላቁ ስቃይ በኊላ የሚመጣውን የሚያሳስብ ነው:: የኢየሱስ መምጣትም በመከራው ያለፉትን በእርሱ ኾነው የሞቱትና በሕይወት ጸንተው ቆመው ያሉትን ለመቀበል ነው:: ቅድሜ መከራ መነጠቅ የሰይጣንን ስውር ሥራ ነው፤ ሃይልን ቅዱሳን እንዳይለብሱ በማድረግ በቀላሉ አውሬው ስገለጥ ለማድቀቅ የሠራው የውሸት ትርክት ነው::

*በእግረመንገዴ ኢየሱስ ስለመምጣቱ ቅን ኢያስተማረ ቀኑን አላውቅም ማለቱ ምን ማለት እንደኾነ መረዳት ጥሩ ይመስለኛል ::

ስለ ኢየሱስ ሙሉእ ሰው|| መኾን ብናምንም እንኳን ቃሉ የሚለውን መቀበል ግን ይከብደናል፤ ይጎረብጠናል:: በመጀሪያ ቃል [መለኮት] ብቻ ነበር:: [የሐ1]:: ሰውን ለማዳን; መለኮት ሰው[ም] ኾነ:: መለኮት ሰውነትን ለራሱ ገንዘብ አደረገው :: እንደ መከራየት ወይም ለጊዜው እንደመጠቀም በሰው ላይ አላደረም :: ሰዎች የእግዚአብሔር ማደሪያዎች ናቸው፤ መለኮት ሰው ላይ እንዲያ አላደረገም፤ራሱ ሰው ኾነ እንጂ:: በመለኮት ማንነቱ ላይ ሰውነትን ያዘ:: ለዚህም ነው መጽሐፍ "እግዚአብሔር በገዛ ደሙ ዋጀ" የሚለው ::ሐዋ 20፥28::

ሰው ለማዳን መለኮት ሰው መኾን ስለ አስፈለገው ሰውነትን ማጥፋት ፣ መዋጥ ፣ መቀነስ፣ መቀላቀል አላስፈለገውም ::ምክንያቱም ሰው ስኾን; ለሥራው ንፁህ ሰው መኾን ተገብቶአልናል :: ደግሞም አምላክነቱንም አልጣለም :: ምክንያቱም አምላክነቱን ከጣለ "የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ" አይባልምና፤ ማንነትም አይጣልም አይቀየርምና፤ ቋሚ ባሕርይ ነውና:: ስለዚህም መለኮት ከክብሩ እንጂ ከማንነቱ አልወረደም :: ይኽንን እንዲህ የቀደሙት አመሳጥረውታል ፦

በክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርያት አሉ:: ሰውነት እና መለኮትነት :: ያለመጠፋፋት፤ ያለመዋዋጥ፤ በመጠባበቅ፤ያለመቀላቀል ይኖራሉ :: ምንም እንኳን ሰውነት በግዝፈት ብታይም ከመለኮት ተልቆ መለኮትን ውጦ አይኖርም፤ አይታይም :: ምንም እንኳን መለኮት አምላክ ብኾንም ሰውነትን አልቀነሰም፤አላጠፋም :: ስለዚህም ምክንያት በአንድ አካል ሙሉእ መለኮት እና ሙሉእ ሰውነት ይኖራል እንላለን :: ግሩም ነው:: ምስጢርም ነው::

ይኽንን እንዲህ ካልን እንደ ሃገር በቀል እሳቤው እንደ "ካራዎች"ወገን ፥ ወልድ የራሱ መለኮት ስላለው መንፈስ ቅዱስ አላስፈለገውም፤ አልተቀባም[6] አንልም :: መንፈስ ቅዱስ ከፅንሰት[ሉቃ1] እስከ መቃብር [ሮሜ8፥11] አልፎም መስዋዕትን እስከማቅረብ ከእርሱ ጋር ነበር :: ዕብ9፥14:: በምድር ስመላለስ መንፈስ ቅዱስ ያግዘው ነበር:: ቃሉም በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ [የተሞላ የተቆጣጠረው] ነው ይላልና ::[ሉቃ4፥17] :: ክርስቶስ በአምላክነቱ; ሰውነቱ ላይ ተጽዕኖ አላደረገም ፣መንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልገውን ኹሉንም ያደርግ ነበር:: ለእኛ እንዳስፈለገ ኹሉ;ለክርስቶስ ሰውነትም አስፈልጓል ::

የኢየሱስ ሰውነት አስተዳደግ ምትሀታዊ አይደለም ። እንደ እኛ ነው እንጂ ፤ የእግዚአብሔር ልዩ ግቡኘት የነበረው ። "ሕፃኑም አደገ በመንፈስም ጠነከረ፥" ሉቃስ 1፥80። በመንፈስ በጉልበት [በዕድሜ] ከመጠንከር እስከ በጥበብ እየተሞላ እስከ ማደግ እንደኾነ ይገልጻል ። "ሕፃኑም አደገ፥ ጥበብም ሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ።" [ሉቃ 2፥40]። ከሕፃኑ ዕድሜ መጨመር; አስተዳደግ ጋር ጥበብም እየተጨመረ እየሞላው እንደሄደ እንረዳለን ። ይኽ እውነት ነው።

እንዲህ ከኾነ; ሰውነቱ [በቃል] በአምላክነቱ ተጽዕኖ ስር ሳይኾን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መኾኑን እንረዳለን ። ስለዚህም ለክርስቶስ ሰውነት ጥበብ [ዕውቀትና ማስተዋል] ከአብ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥና የሚጨምር ነው። በመንፈስ ቅዱስ መቀባቱን ካመንን ይኽንን አለመቀበል ግማሽ እምነት ወይም ክህደት ይኾናል ።

ኢየሱስ በሰውነቱ በመንፈስ ቅዱስ እገዛ [ማስተዋልና መረዳት] ለአብ በሚገባ መታዘዙ ፣ ቃሉ እንዲህ ይገልጻል "ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤" [ዕብ5፥8] ፣ ይለናል ። እኛ እያመጽን ከስህተታችን ስንማር፣ ክርስቶስ ግን በመታዘዝ እየታዘዘ እየተማረ እየተማረ ሄደ፤ አገለገለ። ፈተናው እየጨመረ እየበዛ ስመጣ ፣ከእያንዳንዱ ፈተና በመታዘዝ ብቻ መማሩ #የማስተዋል እድገት ተደርጎ ልቆጠር የሚችል ነው። መለኮታዊ ፈተና በራሱ አስተማሪና አሳዳጊ ነውና ። ሰውነቱ እንደተማረ ልንክደው አይገባንም ።

መንፈስ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ሰውነቱን መርዳቱንና መቆጣጠሩን ከተረዳን፥ መላእክት እንኳን ኢየሱስን [ለሥጋው] እርዳታ አስፈልጎት እንዳገለገሉት መመልከት እይታችንን ያግዛል ። ማቴ4፤ ኢየሱስ ከሚቀበለው መከራ ጭንቀት የተነሳ በፍራት ስጣጣር መጥተው ያገለግሉት ነበር። ሉቃ22፥ 43። ይኽ እውነት ነው። መራቡ፣መጠማቱ፣ ከሕመሙ የተነሳ መጮኹ፣ ማልቀሱ ፣ማዘኑ የእውነት እና ጥልቅም ነበር፤ ነው።

የመለኮት ሙሉአት በክርስቶስ ሰውነት ተገልጦ ይኖራል ማለት ፣ የአብ መለኮት በሰውነቱ ስላለው፥ የሰውነትን ባሕርይውን ውጥዋል ወይም ሰውነትን አዳፍኗል ማለት አይደለም ።ከላይ እያየን የመጣነው የወልድ መለኮት ሰውነቱን እንዳልዋጠ እና ለሰውነቱ መንፈስ ቅዱስ መሪ እንደኾነ ነው። በዚህም ይኽ ቃል የቃሉን እውነት ከላይ ያለውን ሃቅ የሚጣረስ እንዳይደለ መመልከት ተገቢ ነው። "በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና፤" ቆላ 2፥9። ማለት የአብ መለኮታዊ ባሕርይን የኢየሱስ ሥጋ አሳይቷል ወይም የማይታየውን የአብን ማንነት በሚሉአት ሰውነቱ ገልጿል ፤ተርኳል ማለት ነው።ይኽ "ኢየሱስ የአብ እውነተኛ ነፀብራቅ ነው" [ዕቤ1]፣ የሚለውን የሚገልጽ ነው።

የአብን ትክክለኛ ባሕርይን ሰውነቱ በመለኮት፥ ተለውጦ ወይም ተቀይጦ ወይም ተዳፍኖ ሳይኾን፣ ክርስቶስ በሰውነቱ ለሰዎች ልገባ በሚችል መልኩ አሳይቷል ማለት ነው። "ተረከው" ማለትም ሰውነቱ መለኮቱን ተረከው፤ገለጠው ፤ እንጂ መለኮት ሰውነትን አላሳየም አልተረከም። ቃል ሰው የኾነው ሰውነትን ለማሳየት ሳይኾን፣ መለኮትን ለመግለጥ ነው። [በባሪያ መልክ የአምላክን ባሕርይ ገለጠ እንጂ በመለኮት የሥጋን ባሕሪይ አላሳየም]

ስለዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ የመምጫውን ቀኑንና ሰዓቱን አላውቅም ማለቱ እውነት ነው። "ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ #ልጅም ቢሆን #የሚያውቅ የለም።"[ማቴ 24፥36]። ምክንያቱም #1ኛ. ሰው ስለኾነ መንፈስ ቅዱስ ስላልገለጠው #2ኛ.የራሱ የቃል መለኮት ሰውነቱ ላይ ተጽዕኖ ስለማያደርግ፣ አላውቅም ማለቱ ትክክልና ልናምነው የተገባ ነው። ይኹን እንጂ ይኽ በሥጋው ወራት እንጂ አኹን የሚሠራ አይደለም ። ምክንያቱም፦

አኹን ክርስቶስን በሥጋ በድካም ሰውነቱ [በውስንነቱ] አናውቀውም ።በትንሳኤው አካሉ በማንነቱ በክብሩ እንጂ። "..፤ ክርስቶስንም በሥጋ እንደ ሆነ ያወቅነው ብንሆን እንኳ፥ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም።" [2ኛ ቆሮ 5፥16]። ስለዚህም በሥጋው ወራት ስለተራብ አኹንም መብልን ይራባል፣ መጠጥን ይጠማል ብለን አናምንም ። ልክ እንደዚሁ በሰውነቱ በሥጋው ወራት "አላውቅም" ብልም፣ በአምላክነቱ በሥጋው ወራት እንኳን እያለ ፥ የሰው ልብን ሁሉንም መርምሮ የሚያውቅ ጌታ ነው[ዮሐ2]፤ ከእርሱ ፊት የተሠወረ ነገር አኹን የለምና ፤ በክብሩ ፊት ችሎና ቆሞ ተቋቁሞ መመልከት የሚቻለውም አኹን የለም።መጽሐፍ "ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥" [ራእይ 1፥17]፤ይላልና ክብር ኹሉ ለእርሱ ይኹን፤ አሜን ።

**ማጣቀሻ**

[1] [2] [3] [4] [5] መጋቢ ተኩ ከበደ፣ የቅዱሳን በአየር ላይ መነጠቅ፣የመጀመሪያው ዕትም 1999ዓ.ም

[6] ትምህርተ ክርስቶስ ቁስ ኮሊን፣ ገጽ 272

### 3.የክርስቶስ ስውር ዳግም መምጣትና ስውር ንጥቀት

ክርስቶስ ወደ ምድር ሰው ኾኖ ለማዳን ስመጣ በግልጥ ነበር የመጣው ፣ ለመፍረድ ዳግመኛ ስመጣ በግልጥ ይመጣል ። ኢየሱስ ከእርገቱ በኋላ ዳግመኛ ለመፍረድ አንድ ጊዜ ብቻ ይመጣል ። ይኽ እውነት ከላይ በተመለከትናቸው ርዕሶች በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠ በብልጭታ አይተናል ። ሃሰተኞች; ክርስቶስ በስውር ይመጣል በስውርም መጥቶ ቤተክርስቲያንን ወደ ራሱ በስውር ይወስዳል የሚሉት ውሸት እንደኾነ አንባቢ ልያስተውል ይገባል ። ቅድሜ መከራ ንጥቀት የሚያስተምሩት የሕያውን በሕይወት ሥጋ የነበሩ ቅዱሳን መነጠቅና የሞቱ ሰዎች ትንሣኤ ኹለቴ በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስ የማያውቀውን የዲያብሎስን ትምህርት ያስተምራሉ ።የትምህርቱ ዓለማም ቅዱሳንን ማኮላሸት ነው። ይገርማል ኢየሱስ ስመጣ በሕይወት ያሉ ይነጠቃሉ ፤ የሞቱትም ይነሳሉ ።አንድ ላይ ወደ ሰማይ ያርጋሉ እንጂ ኢየሱስ ስመጣ በሕይወት ያሉት ተነስተው ፣የሞቱት ሳይነሱ ቀርተው ወይም ግማሹ ተነስተው የሚል አስተምህሮ በመጽሐፍ የለም። ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማቅረብ የማያስችል ግራየገባው ግራየተጋባውን ትምህርት ያስተምራሉ ። አንባቢ እንደ በሪያ ሰዎች እንዲመራመሩ አበረታታለሁ ። ለራስዋ እድል ይስጡ። በዚህ እንዲያ ነው እንዲህ ነው  ከሚል ዝባዝንኬ ከፍደል ጨዋታ ከቃላት መራቀቅ ፈቀቅ ብለው በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊያን ላይ አድሮ የገለጠው መንፈስ ቅዱስ፣ ያንኑ እንድገልጽ ይጸልዩ ። መንፈስ ቅዱስ የሰው ደቀመዛሙርት አያደርግም ። የክርስቶስ ተከታይ የቃሉ ኗር፤ ቃሉን ጠባቂ፤ የሥጋዊ አዕምሮ ለወለደው ትርክት መንፈስ ቅዱስ አሳልፎ አይሰጥም ። ስለዚህም ለራስዋ ጊዜ ይስጡ። ያሰላስሉ፤ይጸልዩ ። እግዚአብሔር በጎደለው በባዶው ከትምህርት እውቀት ውጪ እንደሚሠራ የተገለጠ ነው። እግዚአብሔርን ለመሥራት የሰው ሽምግልና አይገድበውም፤ የሰው ጉብዝና አያግዘውም። እርሱ ብቻ ይሠራል ።በባዶ ጋን ቃሉን ያሞላል።  ስለዚህም በክርስቶስ መንፈስ ይኽንን እውነት በመስማት ከሚጠፉት ጋር እንዳይጠፉ አሳስባለሁ ።ጆሮ ላለው ።

ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ **ያዩታል**፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ **ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ**። ማቴ 24፥29-31።  ይኽንን ክፍል ከፍ ባለው ክፍል የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ስንመለከት ለማየት ሞክረናል ። ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ጥያቄ መልስ እየሰጠ ነበር።ደቀመዛሙርቱ ስለመምጣቱ ምልክት ለጠየቁት ኢየሱስ የሰጠው መልስ ነው። አንባቢ ያስተውል ።ኢየሱስ ስለመምጣቱ ስጠየቅ ኹሌቴ እንደሚመጣና በስውር እንደሚመጣ ሃሰተኞች እንደሚሉት አልገለጸም ። አንድ ጊዜ ብቻ የሚኾን ነውና መምጣቱ አንድ ጊዜ ብቻ እንደኾነና ግልጥ እንደኾነ አመላክቷል ። የሰው ልጅ ስመጣ ፦ ፀሐይና ጨረቃ መጨለሙ ፣ከዋክብት መውደቁ ፥ የሰማይ መናወጥ ለኹሉም ግልጽ የሚታይ ክስተት ነው። የምድር ወገኖች ይኽንን ክስተት ተመልክተው ዋይ ዋይ ይላሉ።ደግሞም የሚመጣው አምላክ ያዩታል ። መጽሐፍ እንዲህ በግልጽ እየመሰከረ ደፍረው በግምት ኢአማኞች  አያዩትም በማለት ውሸትን ይናገራሉ ። ኢየሱስ ስለመምጣቱ ስጠየቅ ፣የሰጠው ምላሽ ይኽ ነው። ይኽንን እውነት በመምጣቱ እንደሚኾን ከመቀበል ውጪ በሰይጣን መንፈስ እየተመራን ያወቅን የላቅን የመጠቅን እየመሰለን፣ በፍልስፍና ካለ መንፈስ ቅዱስ ምሪት ፣ በቃሉ ላይ መሰልጠን አግባብ አይደለም ። ድሮም ሰይጣን ሥራው ኢአግባቢነት ያለውን ማድረግና ማስደረግ ነው። እንዲያ ባይኾን ስለመምጣቱ ኢየሱስ በነገረው ባረፍን ነበር። ኢየሱስ ስለመምጣቱ ስናገር ለጥያቄአቸው አንድ ጊዜ ብቻና በግልጥ እንደሚመጣ ብቻ ባልነገረ ነበር፣ መምጣቱ ኹሌተ ብኾን እንዴት ይኽንን ሳይገልጽ ያልፋል ብላችኹ ታስባላችኹ? ያልተጻፈውን እየፈጠሩ ማንበብና ማስነበብ ስለለመዱ እንጂ የኢየሱስ መምጣት አንድ ጊዜ ብቻ የሚኾን ነው።

ኢየሱስ ዳግመኛ ስመጣ;በታላቅ መለከት መላእክት እየነፋ ታጅቦ ይመጣል፤ "መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ"። መላእክቱ እንዲህ በታላቅ ድምጽ እየነፋ ስመጣ እንዴት በስውር ይመጣል እንላለን ? በዚህ ክፍል ላይ ብቻ አይደለም በሌሎች ክፍሎችም ይኽ እውነት ተቀምጧል ። “ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤” 1ኛ ተሰ 4፥16 ።ኢየሱስ በእግዚአብሔር መለከት በታላቅ ድምጽ በመላእክት አለቃ ታጅበው መምጣቱ ፣ በመምጣቱ ብዙዎች እንድሸበሩ ዋይ ዋይ እንዲሉ ከሚያደርጉ ትይንቶች  አንዱ ነው።  ታዲያ ይኽ መምጣቱ ስውር ነው ለማለት ያስችላል ? ውኃውን ወተት ነው የማለት ድፈረት ካልኾነ በስተቀር ። ደግሞም በዚህ መምጣት የተመረጡት የጌታ ምርጦች ይሰበሰባሉ ፤ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ።

የቅድመ መከራ ንጥቀት አስተማሪዎች ውሸት አያልቅም ።ዮሐንስ ራዕዩን ስመለከት ፣ራእዩን ከተመለከተበት ጊዜ አንስቶ የሚኾነውን፣ ልኾን ያለውን፣ ገና ልኾን የሚገባውን የተመለከተውን በመዋሸት ፣ለአስተምህሮአቸው ይመች ዘንድ ውሸታቸውን ከዚህ ይጀምራሉ፦ ቅዱሳን ስለተነጠቃችኹ ከዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ አራት ጀምሮ

ያለው አይመለከታችሁም ይላሉ፣ ራእዩ ለኢየሩሳሌም ዘሥጋ እና ላልተዘጋጁት አሕዛብ ብቻ ነው ይላሉ ። ጌታ ስለመጨረሻው ዘመን ስናገር የገለጠው መጨረሻው ከመምጣቱ በፊት ሰይጣን እንደሚሰራ በመጨረሻም ወራትም በግልጽ ቆሞ እንደሚሠራ ገልጿል ።በዚህም ምክንያት ቅዱሳን እንዳይስቱ ከደቀመዛሙርቱ ጀምሮ ኢየሱስ ስያስጠነቅቅ እናያለን ። ዮሐንስ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ የገለጠው ራእዩ ፣ ራእዩ ከታየበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ያለውን ነው። በዚህም የሚመጣውን አውቀው በመምጣቱ እንዲኖሩ ሙሉና ዝርዝር መግለጫ ይሰጣል ። ይኽ የሚያሳየው አውሬው በመቅደሱ ተገልጦ በግልጥ መሥራት ከመጀመሩ በፊትም፣በስውር እንደሚሠራ ነው። አማኞች ሰይጣን በስውር ስሰራ እስካሁን ደግሞም ለጥቂት ጊዜ ወደ ምድር ተጥሎ በግልጥ ሥሠራም አማኞች በምድር ላይ መኾናቸውን ። አማኞች በምድር ላይ ስለሚኾኑ በስውር ስሰራ ኾነ በግልጥ ሥሠራ ሳይስቱ፣ ታምነው ለስሙ እንዲኖሩ ያሳስባል ። ሰይጣን በስውር ስሰራ ያልተነጠቀችው ቤተክርስቲያን ሰይጣን በግልጥ ስሰራ ትነጠቃላች ማለት ምን ማለት ነው? ሰይጣን የጨለማው ሃይል ይለያያል ።በታላቅ ቊጣ ወደ ምድር ከመምጣቱ ከመውረዱ በስተቀር ሌላ ነገር የለም። ዮሐንስ በራእዩ ልክ እንደ ኢየሱስ ፣መምጣቱን ኾነ የቅዱሳን ከመከራው በኋላ መነጠቅን በግልጽ ያስረዳል ። ዮሐንስ ራእዩን ካየበት ጊዜ ጀምሮ የሚኾነው የተመለከተውን በማዳፌን ከቅዱሳን መነጠቅ በኋላ ያለው ይገልጻል በማለታቸው ራእዩ ከምዕራፍ አራት ጀምሮ ያለው በ7ዓመታት ውስጥ ያለውን ያመለክታል ማለታቸው እንደኾነ ሳስተውል ይደንቀኛል ። ራእይ የተመለከትናቸው መገለጫዎችን ይመልከቱ ።

**4.ከመከራው በስውር የተነጠቁ ቅዱሳን ሰርግ**

እነዚህ ሃሰተኞች እረኞች በስውር እየሰራ ላለው አውሬ መንገድ ጠራጊዎች፣ በውሸታቸው ይቀጥላሉ እንጂ አይመለሱም ። ንስሐም አይገቡም ። እስካሁን በተመለከትነው አንባቢ ያስተዋለ ይመስለኛል ፤ከሚጠፉት ካልኾነ። ጌታ እንዴ ሌባ እመጣለሁ ያለውን ቀኑን አላሳውቃቸውም ለማለት እንጂ በስውር መጥቶ በስውር ቅዱሳንን ለመንጠቅ አይደለም ። ጌታ በስውር የሚወስደው ማንን ስለፈራ? ወይም በግልጥ ብመጣ ማንስ ልቋቋመኝ ይችላል ብሎ? ለእግዚአብሔር አብ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስልጣን ክብር ይኹንና፣ አይደለም ኢየሱስ ስሙን የሚጠሩት እንኳን ሰይጣንን ጠፍረው አስረው ሰልጥነው ይይዛሉ ።

በውሸት የተንኮለኛውን የእባቡን ትምህርት የሚያስተምሩ ፣ በምድር ላይ ያሉት ስሞቱ ፣ስረሸኑ፣ደማቸው ስፈስ፣ ስሰቃዩ፣ስንገላቱ ፤ ጌታ ከሌሎች ጋር ሰርግ ያደርጋል ይላሉ ፤ ሙሽሪት ሳትሰበሰብ ፤ ሰርግ የደስታ የድል ድግስ ነው። ሌሎች በጨኳኙ አውሬ እየተገነጠሉ ስሞቱ ፣ ጌታ ከሌሎች ጋር በድግስ በደስታ በሰርግ እንደተቀመጠ ማስተማር በራሱ ፣ስበዛ ራስ ወዳድነት ነው። እግዚአብሔርን አለማወቅ ነው።

በጉ ሰርግ የሚደረገው ባቢሎን ወድቃ፣ አውሬው ታስሮ ፣ የእግዚአብሔር ፊትህ በአሕዛብ ላይ ከተገለጠ ከፍርድ በኂላ እንጂ ግማሹ ስሰቃይ ከግማሹ ጋር ጌታ ድግስ አይደግስም። ሰይጣን እንዲታሰር እንዲፈረድበት የሚጮኹ ቅዱሳን፣ ፍርድን ሳይቀበል እንዴት ይደሰታሉ ?በመጽሐፍ በግልጽ የተቀመጠው የበጉ ሠርግ ፣ ከኢየሱስ ዳግመኛ መምጣት ከፍርድ በኂላ ነው። "የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ ሚስቱም ራስዋን ስላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።" ራእይ 19፥7 ።

ሰርግ የሚደረጉ የተመረጡት ኹሉ በክርስቶስ ስጠቀለሉ ፣ ቤተክርስቲያን የበጉ ሚስት ራሳቸውን ስያዘጋጁ ነው። አንደኛው ተዘጋጅቶ አንደኛው ሳይዘጋጅ፣ ኹሉም የተመረጡት ሳይታተሙ ከከፍሎቹ ጋር ጌታ ሰርግ አያደርግም ። ሰርግ ደስታ ሰላም ያለበት ነውና የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው፥ "መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች። የታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ ባሮቹን ላከ ሊመጡም አልወደዱም። ደግሞ ሌሎችን ባሮች ልኮ፦ የታደሙትን፦ እነሆ፥ ድግሴን አዘጋጀሁ፥ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፥ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ። እነርሱ ግን ቸል ብለው አንዱ ወደ እርሻው፥ ሌላውም ወደ ንግዱ ሄደ፤ የቀሩትም ባሮቹን ይዘው አንገላቱአቸው ገደሉአቸውም። ንጉሡም ተቈጣ፥ ጭፍሮቹንም ልኮ እነዚያን ገዳዮች አጠፋ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ። በዚያን ጊዜ ባሮቹን፦ ሰርጉስ ተዘጋጅቶአል፥ ነገር ግን የታደሙት የማይገባቸው ሆኑ፤ እንግዲህ ወደ መንገድ መተላለፊያ ሄዳችሁ ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ጥሩ አለ። እነዚያም ባሮች ወደ መንገድ ወጥተው ያገኙትን ሁሉ ክፉዎችንም በጎዎችንም ሰበሰቡ፤ የሰርጉንም ቤት ተቀማጮች ሞሉት። ንጉሡም የተቀመጡትን ለማየት በገባ ጊዜ በዚያ የሰርግ ልብስ ያለበሰ አንድ ሰው አየና፦ ወዳጄ ሆይ፥ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው እርሱም ዝም አለ።በዚያን ጊዜ ንጉሡ አገልጋዮቹን፦ እጁንና እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ።የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና። ማቴ 22፥2-14።

ሰርግ በጠላቶቹ ፊት በድል የሚገለጥ እንጂ ተደብቀው እንደ ሌባ እንደ አመንዝራ ሕጋዊ እንዳልኾነ ግንኙነት የሚገረግ አይደለም ። ሰርጉ ኹሉም የተመረጡት በተገኙበት የሚደረግ እንደ ሌባ ሳይታሰብ በስውር የሚደረግ አይደለም ። በመጽሐፍ ወደፊት ሰርግ የሚኖሩን ዮሐንስ በራእዩ የገለጠው ፣ከባቢሎን መውደቅ መፍረስ ከበጉ ቁጣ በኂላ ነው። መጽሐፍ ይኽንን እውነት እያስተማረ ሳለ፣ ያልተጻፈ የሚያነቡ የበጉ ሰርግ ከክፍሎቹ ጋር ብቻ እንደሚደረግ ምንዝርና ያስተምራሉ ።አያፍሩም ።አንባቢ ያስተውል ።

# የቤተክርስቲያን  ቅድሜ መከራ መነጠቅና ትርክቱ

**ማጠቃለያ**

እነዚህ ሃሰተኞች ወደ መንግስቱ ለራሳቸውም አይገቡም፣የተመረጡትንም አያስገቡም። “እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ፥ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።” ማቴ 23፥13 ። ትውልድን እያወዛገቡ ይኖራሉ፤ ስያስቱ ይኖራሉ ። አይመለሱም ። ይኽንን የጻፍኩት ለሚሰሙት ጆሮ ላላቸው ብቻ ነው። መልካም መሬት ኾኖ እያሉ ሰይጣን በመካከላቸው እንክርዳድ በመዝራት ስያወዛግብ በመኖሩ እንዲያመልጡ ነው፤ ከሐሰተኞች እጅ በመናጠቅ ለማትረፍ ነው።

ሰይጣን በስውር ሥሠራም ኾነ በግልጽ ሥሠራ ያው ነው። ቀድሞም የእግዚአብሔር ልጆች ስሰደዱ ስረሹ ነበር ። በዚህም መሃል ቤተክርስቲያን በድል አድራጊነት አልፋለች ።በግልጽ ተገልጾ ሥሠራ ደግሞ በመለኮታዊ ሃይሏ ከሃሳቡና ከአቅሙ በላይ ትኾናለች ። የሃሰተኛው መብዛት ነፃነት ማጣትና በዘንደው ማህበረሰብ መገለል፣ መሰደድ፣ መገደል፣ እንጂ ሌላ አይደለም ። ምክንያቱም በዚያ በታላቁ መከራ ሰዓት ወደዚያ የዘንደውን ማህበረሰብ የሚያስጨንቁ ብርቶዎች ወይራዎች እንደሚነሱ ተመልክተናል ።እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ በክፍል ኹለት በደንብ ስለ ሴትቷ ፣ስለ ታተሙት ቅዱሳን ፣ስለ እስራኤል መንፈሳዊ ትርጓሜ እንመለከታለን ።

በመጨረሻው ሰዓት ሰይጣን መላኩ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዲያብሎስና ግብረአበሮቹን ከመንገድ ለማስወገድ ነው። ጌታ እንክርዳዱን ከስንዴው በመለየት ፣ እንክርዳዱን ኾነ ፍሬ ያላፈሩ ቅዱሳንን ለማስወገድ ይኽንን አድርጓል፣" ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው።ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ፥ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።" 2 ተሴ 2፥9-12። ስለዚህ ባለማመናቸው ምክንያት ፍርድን እንዲቀበሉ ጌታ ይኽንን አድርጓል ።

ታዲያ የስውር ንጥቀት አስተምህሮና ትርኩቱ ዓላማው ምንድነው ? በስውር የሚሠራው አውሬ በግልጥ ለመሥራት ስመጣ አኹን ያለንበት ጊዜ በግልጽ እየመጣ መኾኑን አብስሯል፤አመላክቷል ። ታላቁ መከራ ለመጀመር ትንሽ ጊዜ ነው የሚቀረው ። ታላቁ መከራ መጀመሩን የእምነት ነፃነታችንን ስናጣ፣ የመብት ሃገር ናት የተባለችው ባቢሎን ስታስገድድና ስትገድል ፣ሰው አባል ካልኾነ ምልክቱን ካልተቀበለ መግዛትና መሸመት ሳይችል ስቀር ፣ መጀመሩን በታላላቅ የምድር መናወጦችና መቅሰፍቶች እናውቃለን ። አኹን እርስበርስ እየተነታረክን በከንቱ መለፍለፍ ክርክር በማሳለፍ ጊዜው የሚናጠፋበት ጊዜ አይደለም ።መዳናችን ቀርቧልና ሃይልን ለመቀበል የትንቢቱን መልእክት እያስተዋልን ወደ ጎዳ የምንገባበት ሰዓት ነው። ስለዚህም የስውር ንጥቀት ኑፋቄ በስውር ለሚሠራው ደግሞም ለሚገለጠው ሃሰተኛው ነቢይ መንገድ ጠራጊ ነው።

መንገድን የሚጠርገው በዚህ በታላቁ መከራ ሰዓት ሃይልን ያልለበሱ አማኞችን ያደቅቃቸዋል፤ ያሸንፋቸዋል ።ስለዚህ ከሚታተሙት መሃል እንዳትኾኑ ተግቶ ይሠራል ። በዚያ ሰዓት የተዘጋጁቱ በሙሴና በኤልያስ መንፈስ በአሕዛብ ላይ ሰልጥነው ፣በአፋቸው ቃል መቅሰፍትን እያመጡ ያገለግላሉ ።ይኽን አውቃችሁ ወደዚህ እንዳትደርሱ ለእኛ የተጻፈው ራእዩ ለእስራኤል ነው በማለት አስተኝቷል። አንባቢ ሴትቱ የተባለችው የክርስቶስ እስራኤል እንደኾነች አውቃችሁ መለኮታዊ ባሕሪ ፀሐይን ጽድቅን እንዳትለብሱ በተለያየ ውሸት አስተምህሮ ጠፍሮ ይዞዋል ። አንባቢ ከተመረጡት ወገን ከኾኑ ወደ ጎዳ ይገባሉ ።ከሚጠፉት መሃል ከኾኑ በእግዚአብሔር እውነት ላይ የራስዎ ኾነ የሰይጣንን ሃሳብ ስናገሩ ይውላሉ ።ይኽ የመጨረሻው ዘመን ነውና አንለምን አንለማመጥም። የበጉ ፍርድ ቀን ደርሷል ። ስለዚህም መጽሐፍ “ዓመፀኛው ወደ ፊት ያምፅ፥ ርኵሱም ወደ ፊት ይርከስ፥ ጻድቁም ወደ ፊት ጽድቅ ያድርግ፥ ቅዱሱም ወደፊት ይቀደስ አለ።” ራእይ 22፥11 ፣ እንደሚል እላለሁ ። ድል ነሽ ለመኾን ሃይልን ለመታጠቅ ከተያዙበት አብዘኛውን ጊዜ ከሚያጠፉበት ነገር በአስቸኳይ ይለዩ።ወደ ጓዳም ይግቡ። የእግዚአብሔር ጸጋ ይብዛላችሁ ።